# የአማራ ህዝብ ጥያቄዎች



በመስከረም አበራ

መጋቢት፣ 2016

# ይዘት


የምስጋና እና የዝክር ገፅ................ i

## ክፍል አንድ................................ 1

መነሻ................................................................ 2

ሰነዱ የተተነተነበት የእሳቤ መነፅር.................................. 10

## ክፍል ሁለት................................ 14

የአማራ ህዝብ ጥያቄዎች.................................................. 15

- የህልዉና ጥያቄዎች ................................................ 15
- የፍትህ ርትዕ ጥያቄዎች.............................................. 15

## ክፍል ሦስት................................ 78

የአማራ ህዝብ ጥያቄዎች እና "ህብረ-ብሔራዊ አንድነት"........ 79

መቋጫ............................................................... 87

# የምስጋና እና የዝክር ገጽ



ክብር እና ምስጋና ለአማራ ህዝብ ጠበቃ ታላቁ አባት
ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ

# ክፍል አንድ

## መነሻ

## ሰነዱ የተተነተነበት የእሳቤ መነፅር

## 1.1 መነሻ

የሃገራችን ፖለቲካ በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ቀዉስ ዉስጥ ይገኛል፡፡ ቀዉሱ መንግስትን ጨምሮ በርካታ የፖለቲካ ሃይሎችን፣የዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡን እና ሰፊዉን የኢትዮጵያ ህዝብ በእጅጉ እያሳሰበ ይገኛል፡፡ የፖለቲካ ንጠቱ የፈጠረዉ ቀዉስ ከመቸዉም በላይ አሳሳቢ እንዲሆን ያደረገዉ የኢትዮጵያን የሃገረ መንግስትነት ህልዉና ሊያሳጣ ይችላል የሚል ስጋት በማየሉ ነዉ፡፡ ይህን ስጋት ያባባሰዉ ደግሞ ለወትሮዉ የኢትዮጵያን ሃገረ መንግስትነት ህልዉና የማስጠበቁን ሚና ላቅ ባለ ሁኔታ የመሸከም እዳ እንዳለበት ይቆጠር የነበረዉ የአማራ ልሂቅ/ህዝብ/ ዛሬ ላይ ባልተለመደ መልኩ በብሄር ማንነቱ ተደራጅቶ መታገል በመጀመሩ ነዉ፡፡

ያልተጠበቀዉ የአማራ ህዝብ ብሄር ተኮር ትግል የተለመደዉን የሃገራችንን የፖለቲካ አሰላለፍ በእጅጉ ቀይሮታል፡፡ ይኸዉም ለወትሮዉ የኢትዮጵያን ሃገረ መንግስት አፍርሰን ከፍርስርሷ ዉስጥ የኦሮሚያ ሪፐብሊክን እንመሰርታለን በሚለዉ አዉዳሚነት በማያጣዉ የፖለቲካ ዘይቤያቸዉ ይታወቁ የነበሩት የኦሮሞ ፖለቲካ ልሂቃን ዛሬ ላይ የኢትዮጵያ ሃገረ መንግስት ቀጣይነት ያሳስበናል ሲሉ አሰላለፍ ቀይረዋል፡፡ በአንፃሩ የኢትዮጵያን ቀጣይነት አጥብቆ በመሻቱ ሳቢያ "ትምክህተኛ"፣ "ተስፋፊ"፣ "ቅኝ-ገዥ" እያሉ ሲያብጠለጥሉት የነበረዉን የአማራ ልሂቅ/ህዝብ/ ዛሬ ላይ በጠባብ ብሄርተኝነት፣በሃገር አፍራሽነትና በጠረኝነት እየከሰሱት ይገኛሉ፡፡

ለወትሮዉ በአክራሪ የኢትዮጵያ ብሄርተኝነትና ጨፍላቂነት ሲከሰስ የነበረዉ የአማራ ልሂቅ የዘዉግ ፖለቲካን መልመድ ያልቻለ፣የድሮዋ አንዲት ኢትዮጵያ ርዕዮት ናፋቂ ተደርጎ ለለዉጥ ባለመመቸት ጭምር ይብጠለጠል ነበር፡፡አማራዉ የብሄር ፖለቲካን መልመድ ባለመቻሉ "ትምክህተኛ" የሚል ታርጋ ተለጥፎለት ኖሯል፡፡

አማራዉ ለብሄር ፖለቲካ ዝግጅት ያላደረገ በመሆኑ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ የተመሰረተዉ የብሄር ፖለቲካ መሃንዲሶቹ ህወሃት እና ኦነግ የፖለቲካ ብልጫ እንደተወሰደበት፣ለሩብ ምዕተ-ዓመት በግራ መጋባት ዉስጥ እንደኖረ የብሄር ፖለቲካዉ ደጋፊ ምሁራን እና ልሂቃን በፅሁፍም በቃልም የሚናገሩት ነገር ነበር፡፡ ከዓመታት በፊት "አዲስ ስታንዳርድ" በሚባል ድረ-ገጽ ላይ አሁን ስማቸዉን የማላስታዉሳቸዉ የኦሮሞ ምሁር ይህንን ጉዳይ በተመለከተ አንድ ፅሁፍ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጽፈዉ ማንበቤን አስታዉሳለሁ፡፡

የጸሃፊዉ ሃሳብ በኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ስም የራሱን ባህል በሌሎች ላይ ሲጭን የኖረዉ የአማራ ልሂቅ የብሄር ፖለቲካዉን መልመድ ባለመቻሉ የኦሮሞ፣የትግሬ፣የሱማሌ፣የአደሬ ወዘተ የብሄር ፖለቲካ ልሂቃን የፖለቲካ ብልጫ ወስደዉበት ለእሩብ ምእተ አመት በመደናገሩ ቀጥሏል የሚል ነዉ፡፡ ፀሃፊዉ ሲቀጥሉም ይህ የአማራ ልሂቃን በረዥም የመደናበር ዘመን መቆየት የብሄር ፖለቲካዉ ልሂቃን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ የልባቸዉን እንዲሰሩ እንዳገዛቸዉ ይገልጻሉ፡፡ ከጸሃፊዉ ሃሳብ በርካታ ሃቆችን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ዋነኛዉ ቁም ነገር ግን የአማራዉ ልሂቅ የብሄር ፖለቲካዉን መልመድ ሳይችል ብዙ ዘመናትን በማሳለፉ የብሄር ፖለቲካዉ የሚፈልገዉ የመገበያያ ምንዛሬ የሌለዉ(በዶላር በሚደረግ ግብይት አሞሌ ጨዉ ይዞ እንደተገኘ ሰዉ የሆነ)፣በፖለቲካ ገበያዉ ለመሸጥም ሆነ ለመግዛት የማይችል፣ ፖለቲካዊም ሆነ ዘዉጋዊ ማንነቱን የተነጠቀ፤ስለመነጠቁም እምብዛም የማይጨነቅ፣በአጠቃላይ ከፖለቲካ ጨዋታዉ ዉጭ (Depoliticize) የሆነ ሆኖ ዘመናት አልፈዋል፡፡ ይህ መልካም ነገር ባይሆንም ሃሰት የሚባል ነገር ግን አይደለም፡፡

ህወሃት እና ኦነግ በመሰረቱት የብሄር ፖለቲካ ዉስጥ አማራዉ ግራ ተጋብቶ የኖረ መሆኑ የሚንፀባረቅባቸዉ በርካታ ገሃድ ማሳያዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ በግሌ የሚገርመኝን ለማንሳት ያህል በኦነግ/ህወሃት የዘዉግ ፖለቲካ ስርዓት ዉስጥ በተለይ በሽግግር ዘመኑ ወቅት አማራዉ በመገለሉ ምክንያት ጥብቅና የሚቆምለት ወኪል በማጣቱ ሳቢያ በየጥጋጥጉ እያለቀ፣አማራ ተብሎ በተከለለዉ ግዛት ዉስጥ ሊከለሉ ይገባቸዉ የነበሩ ግዛቶች(መተከል፣ ወልቃይት ጠገዴ፣ ራያ፣ ደራ) ለተለያዩ ክልሎች በገፀ-በረከትነት እየተሰጡ ባሉበት ሁኔታ ዉስጥ ተቀምጦ አብዛሃኛዉ የአማራ ልሂቅ ይቆጭ የነበረዉ ኢትዮጵያ ሁለቱንም የባህር በሮቿን አጥታ የባህር በር የሌላት ሃገር በመሆኗ ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአማራው ልሂቅ የብሄር ፖለቲከኞች አንቀጽ 39ን ተጠቅመዉ ኢትዮጵያን እንደ ዩጎዝላቪያ ታሪክ እንዳያደርጓት የብሄር ብሄርተኛን ሁሉ በማባበል ላይ ተጠምዶ ነበር። ከዚህ ሁሉ ነባራዊ ሃቅ የምንረዳዉ በአዲስ ስታንዳርድ ላይ የጻፉት ጸሃፊ አማራዉ የብሄር ፖለቲካን መልመድ ባለመቻሉ በብሄር ፖለቲከኞች ብልጫ ተወስዶበታል ማለታቸዉ ሃቅ መሆኑን ነዉ።

የአማራ ልሂቅ የዘዉግ ፖለቲካዉን መልመድ አለመቻሉ በርካታ ጉዳቶችን አምጥቶበታል። የመጣበትን ጉዳት ለመረዳት በርካታ ዘመናትን ማስቆጠሩ ደግሞ "በእንቅርት ላይ……." የሚሉት አይነት ነገር ነዉ።የአማራዉ ልሂቅ የብሄር ፖለቲካዉን ሊለምድ ያልቻለዉ የብሄር ፖለቲካ ከሰዉ አእምሮ በላይ የሆነ ዉስብስብ ነገር በመሆኑ አማራዉ መረዳት አቅቶት አይደለም። ይልቅስ አማራዉ የብሄር ፖለቲካን መልመድ ያልቻለዉ የብሄር ፖለቲካዉ በዉጤት ደረጃ ከኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ፖለቲካ የተሻለ አትራፊነትና ምርታማነት የሌለዉ እንደሆነ ስለሚረዳ ነበር። ይህ የአማራዉ ልሂቅ ፖለቲካዊ መረዳት ስህተት የሌለበት አረዳድ ነዉ። ለዚህ ማስረጃዉ በአሁኑ ጊዜ የብሄር ፖለቲካዉ ቀሳዉስት ራሳቸዉ አዋጪ መንገድ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት እንደሆነ ለአማራዉ ለእራሱ ለማስረዳት ለእናቷ ምጥ እንደማስተማር ባለ ድካም ዉስጥ የሚገኙ መሆናቸዉ ነዉ። ሆኖም በአሁኑ ወቅት በየመንግስት ሚዲያዉ ስለ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት የሚሰብኩ የብሄር ፖለቲካዉ ቀሳዉስት ኢትዮጵያን የሚወዷት ስልጣን ላይ ተቀምጠዉ ሲያዩዋት ብቻ መሆኑ አማራዉ የተረዳዉ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ማማ ላይ ለመድረስ እንዳልቻሉ ማሣያ ነዉ።

አማራዉ የተረዳዉ የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ርዕዮት ስልጣን ላይ ሲቀመጡ የሚያጠልቁት፣ከስልጣን ሲወርዱ ደግሞ አዉልቀዉ ጥለዉ የሚያበሻቅጡት አይነቱን አይደለም። አማራዉ የተረዳዉ የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት እሳቤ ከስልጣን ወርደዉ ብቻ ሳይሆን በማንንቱ ተነጥሎ እየተገደለ ሳይቀር "ኢትዮጵያ የምትፀና ከሆነ ይሁን" የሚል ጥብቅ እምነት ነዉ። አማራዉ የተረዳዉ የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት እሳቤ አማራ ያልሆነ ጠቅላይ ሚኒስቴር ስልጣን ላይ ሲወጣ የኢትዮጵያን ስም እስከጠራና ለኢትዮጵያዉያን ሁሉ ፍትሃዊ ስርዓት ማምጣት ከቻለ የኔዉ ወገን ነዉ ብሎ መቀበል ነዉ።

ጠ/ሚ አብይ ወደ ስልጣን እንደመጡ በአማራ ክልል የተደረጉ ትላልቅ የፌሽታ ሰልፎች የአማራን ህዝብን ፖለቲካዊ ስነልቦና ግልጽ ያደረጉ ነበሩ። ሆኖም በአማራዉ ልቦና የታሰበችዉ ኢትዮጵያ ልትመጣ አልቻለችም። ይልቅስ በብሄርተኞቹ አፍ የምትንቆለጳጰሰዋ ኢትዮጵያ ለአማራዉ ይዛ የምትመጣዉ ነገር ከጀኖሳይድ እስከ አፓርታይድ የዘለቀ፣የበደል ድግስ እንደሆነ ዘግይቶም ቢሆን ተረድቶታል። ስለሆነም የብሄር ፖለቲካዉን ምንዛሬ ይዞ ወደ ፖለቲካዉ መግባት አማራጭ የሌለዉ ነገር እንደሆነ አዉቆ በዘመኑ ቋንቋ እየተናገረ ይገኛል።

አሁን የአማራዉ ልሂቅ/ህዝብ/ እጅግ ዘግይቶም ቢሆን በብሄር ፖለቲካዉ ዉስጥ ከጨዋታ ዉጭ የመሆኑ ነገር ያመጣበትን ጉዳት አጢኗል። በመሆኑም ወቅቱ የሚፈልገዉን የፖለቲካ ምንዛሬ (በብሄር ተደራጅቶ መጫወት)ይዞ ለመገኘት ችሏል። አማራዉ የብሄር ፖለቲካዉን ባልታሰበ ፍጥነት ተረድቶ፣ባልተጠበቀ መናበብ እያከናወነ ይገኛል። ይህ በአማራዉ ልሂቅ/ህዝብ በኩል የታየዉ ድንገተኛ የሚመስል የአማራ ብሄርተኝነት ንቃት፣መደራጀትና ፈጣን እርምጃ ለወትሮዉ "አማራዉን በማያዉቀዉ የብሄር ፖለቲካ መስመር ወስደን ግራ አጋባነዉ" ሲሉ የኖሩ የብሄር ፖለቲካ ልሂቃንን ግራ አጋብቷል፤አሁን የግራ አጋቢና የግራ ተጋቢ መስመር ተቀያይሯል። አሁን በተራቸዉ የአማራዉን ብሄርተኝነት መልመድ ያልቻሉት የአማራ-ጠሉ የብሄር ፖለቲካ ቀሳዉስት ሆነዋል። የብሄር ፖለቲካዉን እስከወዲያኛዉ አይለምድም ተብሎ የነበረዉ የአማራ ልሂቅ/ህዝብ/ በሚገርም ብቃት የብሄር ፖለቲካዉን ማስኬድ መቻሉ፣ከጥግ እስከ ጥግ መብቱን ለማስከበር ሞትን ሳይፈራ መነሳቱ ማንንም ግራ የሚያጋባ፣ተአምር የሚመስል ነገር ነዉ።

የአማራዉ ብሄርተኝነት አይመጣም በሚል እርግጠኝነት ላይ የነበሩት የአማራ-ጠሉ ስርዓት አቋቋሚዎች፣ደጋፊዎችና ባለሟሎች የአማራ ብሄርተኝነት በአጭር ጊዜ ያስመዘገበዉ ዉጤት በእጅጉ አስደንግጧቸዋል። በመሆኑም አማራዉ በማንነቱ ምክንያት የደረሱበት/እየደረሱበት ያሉ በደሎች እንዲቆሙ የሚያነሳቸዉን ጥያቄዎች መረዳት የሚችሉበትን የፖለቲካ ቀልብ አጥተዋል። የአማራ ህዝብ የሚያነሳቸዉን ጥያቄዎች በርጋታ ሰምቶ ለመመለስና ችግሩን ለማስቆም በመምከር ፋንታ መፍትሄ የሌለዉ መንገድ መንዝን መርጠዋል። ይህ መፍትሄ አልባ መንገድ የአማራ ህዝብ የሚያነሳቸዉን ጥያቄዎች በመካድ፣በማጣጣልና በማራከስ ይገለጣል።

አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራ ህዝብን ጥያቄዎች ከማዳመጥ እና መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ የህዝቡ ትግል ምክንያት አልቦ፤ዝም ብሎ የመተኮስ አምሮት ያመጣዉ የአመፀኝነት አባዜ አድርጎ መፈረጁን ተያይዞታል፡፡ እዉነቱ ግን ሌላ ነዉ፡፡

የአማራ ህዝብ በብሄር ተደራጅቶ ሲታገል ትግሉን ግድ ያደረጉ በርካታ የትግል ምክንያቶችን( Causes ) አንግቦ ነዉ እንጂ ሰላም ጠልቶ፣ የጦረኝነት መንፈስ ተጠናዉቶት ወይም የሚወዳትን ሃገር የማፍረስ አዉዳሚነት ተቆራኝቶት አይደለም፡፡ የኦሮሞ ብልጽግና መራሹ መንግስትም የሚያወራዉን ያህል ሰላም ወዳድነት ካለዉና ኢትዮጵያን ማትረፍ ከፈለገ በቅድሚያ ሊወሰደዉ የሚገባዉ እርምጃ የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች በእርጋታ ለማዳመጥ የሚያስችል የፖለቲካ ስክነትን መላበስ ነዉ፡፡ አሁን መንግስት የያዘዉ ግን ሌላ ነዉ፡፡ በአንድ በኩል ለሰላም ዘብ ቆሜያለሁ ይላል፣በሌላ በኩል የአማራ ህዝብ እየሞተለት ያለዉን ጥያቄዉን በማጣጣል በተለመደዉ መፍትሄ አልቦ ጉዞ እየነጎደ ነዉ፡፡ የኦሮሞ ብልጽግና መራሹ መንግስት የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች ለማዳፈን፣ ለማጣጣል እና ለማራከስ የሚያደርገዉን መሟሟት ለመረዳት በቅርቡ የሃገራችን ኤታማዦር ሹም ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ታህሳስ 01/2016ዓ.ም ለመከላከያ ቴሌቭዥን እና ለሌሎች የመንግስት ሚዲያዎች የሰጡትን ቃለመጠይቅ ማየቱ ብቻ በቂ ነዉ፡፡ ይህ የኤታማዦር ሹሙ ንግግርም አሁን ስልጣን ላይ ያለዉ አማራ-ጠል ስርዓት የአማራን ህዝብ ለማዳመጥ ተፈጥሮዉ የማይፈቅድለት እንደሆነ የሚያሳይ ነዉ፡፡

በሃገራችን ሰላም እንዲሰፍን ከተፈለገ መንግስት ቢያንስ የህዝብን ጥያቄዎች በትህትና የማዳመጥ ስክነት መላበስ አለበት፡፡ የህዝብን ጥያቄዎች በማጣጣልና በማራከስ የሚጸና ወንበር የለም! ስልጣን ላይ ያለዉ የኦሮሞ ብልጽግና መራሹ መንግስት የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች የሚያጣጥለዉ ከአማራ ጠል ተፈጥሮዉ የተነሳ እንደሆነ ግልፅ ነዉ፡፡ ሆኖም በአማራ ልሂቅ በኩልም ህዝቡን ጥያቄዎች ደርዝ ባለዉ ሁኔታ በፅሁፍ ሰንዶ ማቅረብ አለመቻሉ መንግስት የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች ለማዳፈን፣ለማጣጣል፣ለማራከስና ለመካድ እንዲመቸዉ በር ከፍቷል፡፡ ይህን ሰነድ አስፈላጊና አንገብጋቢ ያደረገዉም ይህን በአማራዉ ልሂቅ በኩል ያለዉን ክፍተት በመጠኑም ቢሆን የመሙላት ምኞት ነዉ፡፡

ከላይ በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ ካለፉት አመታት ይልቅ ዛሬ ላይ አማራዉ የብሄር ፖለቲካዉ የሚፈልገዉን የፖለቲካ ዘይቤ ተላብሶ መብቱን ለማስከበር የሚችልበት የፖለቲካ ንቃትና የትግል ቁርጠኝነት ላይ ደርሷል። ይህ እጅግ ተስፋ ሰጭ እምርታ ነዉ። ሆኖም ለአማራ ህዝብ ስኬት በትግሉ ሜዳ ከሚደረገዉ የከበረ መስዋዕትነት ጎን ለጎን የትግሉን ፖለቲካዊ መሰረት ማፅናት በእጅጉ አስፈላጊ ነዉ። የአንድ ህዝብ ትግል ፖለቲካዊ መሰረት ከሚጸናበት መንገድ ቀዳሚዉ ህዝቡን ለትግል ያስነሱትን ጥያቄዎች ግልጽ በሆነ መንገድ ሰንዶ በማቅረብ፣ ህዝቡ ስለትግሉ ምክንያቶች(Causes) ተቀራራቢ መረዳት እንዲኖረዉ ማስቻል ነዉ።

የህዝብን ጥያቄዎች ደርዝ ባለዉ መንገድ ሰንዶ ማቅረብ ሲቻል ተገዳዳሪም ብድግ ብሎ የህዝብን ጥያቄዎች ማጣጣል እንዳይችል ይከለክለዋል።በአሁኑ ወቅት የአማራ ህዝብ ትግል በአመርቂ ሁኔታ እየተፋፋመ ቢሆንም ትግሉን አስፈላጊ ያደረጉ ምክንያቶችን ሰንዶ የማቅረቡ ነገር ግን እስከዛሬ ድረስ እዉን አልሆነም። እያንዳንዱ የአማራ ህዝብ በአሁኑ ወቅት ለትግል መነሳት እንዳለበት የሚያስገድድ በደል እና መጠቃት እንደ ደረሰበት ልቦናዉ ቢነግረዉም ጥያቄዎቹን አብጠርጥሮ በማወቅ ረገድ ተቀራራቢ መረዳት ላይ ተደርሷል ለማለት አያስደፍርም። አንድ ህዝብ የሚያደርገዉ ትግል ዉጤታማ እንዲሆን ደግሞ የትግሉ ምክንያት የሆኑ ጥያቄዎችን ወጥ በሆነ ሁኔታ ተረድቶ በአንድ ቋንቋ ማስረዳት መቻሉ ነዉ።

የትግሉ ምክንያቶች በልሂቃን/ምሁራን ተሰንደዉ ሳይቀርቡለት አሁን እያደረገ ያለዉን የመሰለ አመርቂ ትግል በማድረጉ ረገድ የአማራ ህዝብ ቀዳሚዉ ህዝብ ሳይሆን አይቀርም። በአለማችን የተደረጉ ስኬታማ ትግሎች አመርቂ ዉጤት የሚያስመዘግቡት በመጀመሪያ የትግሉ ምክንያቶች በልሂቃን/ምሁራን ተብጠርጥረዉ ተተንትነዉ ቀርበዉ፣ቀጥሎም በቀረቡት የትግል ምክንያቶች ላይ በመመርኮዝ ህዝብን ለትግል የማነሳሳት የቅስቀሳ ስራ በልሂቃን አማካኝነት ተሰርቶ ነዉ። የአማራ ህዝብ ግን የበደሉ ብዛትና ርዝመት ልቦናዉን ለትግል አነሳስቶት እንጅ ማንም የትግሉን ምክንያት በሰነድ ሰንዶ አቅርቦለት አይደለም ለትግል የተነሳዉ። ይህ የአማራ ልሂቃንን በእጅጉ የሚያስወቅስ ክፍተት ነዉ። ሆኖም ክፍተቱን ለመድፈን አሁንም አልረፈደም።

የአማራ ህዝብ ለሶስት አስርት አመታት የኑሮዉ አካል ሆኖ የዘለቀዉ የማንነት ተኮር በደል ለትግል አነሳስቶት አሁን ላይ የተፋፋመ ትግል በማድረግ ላይ ነዉ፡፡ ሆኖም የህዝቡን ጥያቄዎች ሰንዶ ማቅረቡ የህዝቡ ትግል መነሻዉና መድረሻዉ በሁሉም ህዝብ ዘንድ የታወቀ መግባባት ላይ የተደረሰበት እንዲሆን ያስችላል፡፡ የህዝቡን ጥያቄዎች በዉል ሰንዶ ለማቅረብ የሚደረገዉ ጥረት የአማራ ህዝብ እያለፈበት ያለዉን በደል ምንነት፣ጥልቀት፣ስፋት እና መገለጫ በተመለከተ በህዝቡ ዘንድ ተቀራራቢ መረዳት እንዲኖር ያስችላል፡፡ ይህን የማድረጉ ስራ ቀደም ተብሎ ተሰርቶ ቢሆን ኖሮ በህዝቡ ላይ ያንዣበበዉ አደጋ ነፍስ ዘርቶ እየተራመደ አማራ የተባለ ሰዉ ሁሉ ቤት ከመግባቱ በፊት መግታት ይቻል ነበር፡፡ ይህ ባለመሆኑ የአማራ ህዝብ በአማራ ጠሉ ስርዓት የተደገሰለትን የመከራ ፅዋ መራራነት ተጎንጭቶ፣ በአሰቃቂ የሞት ጥላ ስር አልፎ፣በአሳፋሪ የዉርደት መንገድ ተጉዞ ብቻ እንዲረዳዉ ግድ ብሏል፡፡

ከመከራዉ ብቻ እንዲማር የተፈረደበት የአማራ ህዝብ የበደሉን ናዳ በየተራ ካስተናገደና በቃኝ ብሎ ለትግል ከተነሳ በኋላም ቢሆን የአደጋዉን አይነት፣ጥልቀትና ስፋት በእኩል ደረጃ ተገንዝቧል ለማለት ያዳግታል፡፡  ማንኛዉም ህዝብ የሚታገለዉ ባወቀዉ ልክ ነዉ፡፡ በአማራ ህዝብ ትግል ዉስጥ በህዝቡ ዘንድ የትግል ምክንያቶችን የመረዳቱ ነገር ዉስን ከመሆኑ የተነሳ የአማራ ህዝብ ትግል ወልቃይትን፣ራያን፣መተከልን እና ደራን ለማስመለስ ብቻ የሚደረግ የሚመስለዉ ሰዉ ቁጥሩ ቀላል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአማራን ህዝብ ትግል ያነሳሳዉ በወለጋና በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በአማራ ህዝብ ላይ የሚደረገዉ ግድያ ብቻ እንደሆነ የሚያስበዉ ሰዉም እንዲሁም በርካታ ነዉ፡፡ የአማራ ህዝብ ትግል ምክንያቶችና ጥያቄዎች ግን እነዚህን ጉዳዮችንም ጭመር ያጠቃልላሉ እንጂ እነዚህ ብቻ አይደሉም፡፡

የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች ከግዛት ጥያቄዎች፣ከማንነት ተኮር ጭፍጨፋዎች እና መፈናቀሎች ጋር ብቻ አያይዞ የማየቱ ዝንባሌ ለአማራ-ጠሉ ስርዓት ጥሩ የማጭበርበሪያ መንገድ የሚከፍት ነዉ፡፡ ይህም ማለት አማራ ጠሉ ስርዓት የግዛቶቹን ጥያቄ "በህገ-መንግስታዊ መንገድ እልባት ያገኛሉ" በማለት እና ያፈናቀላቸዉን አማሮች "ወደ ቀያቸዉ እመልሳለሁ" በማለት የህዝቡን ትግል ሊያዳፍን ይሞክራል ማለት ነዉ፡፡ የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች በተገቢዉ ሁኔታ ተንትኖ ለህዝቡ ማስረጹ ጠቃሚ የሚሆነዉ ለዚህ ነዉ፡፡

በማንነት ላይ መሰረት ባደረገ መልኩም ሆነ በሌላ መንገድ ተደራጅቶ በሚደረግ ትግል የህዝብን በደሎች እና ጥያቄዎች ነቅሶ አዉጥቶ በሆኑት ልክ በመተንተን ለህዝብ ማቅረብ ዋነኛዉ የትግሉ ምዕራፍ ነዉ። በሃገራችን ስኬታማ ትግል ያደረገዉ ህወሃትም ሆነ የትግል አጋሩ ኦነግ ይህን ምዕራፍ በአመርቂ ሁኔታ አልፈዉታል። እነዚህ የፖለቲካ ቡድኖች የትግላችን ምክንያት ነዉ ብለዉ በተነተኑት የማታገያ ማኒፌስቶ እና የተለያዩ የትግል ሰነዶች ሃሰተኛ ትርክቶችን ያለምንም የሃላፊነት ስሜት እዉነት አስመስለዉ እስከማቅረብ ሄደዋል። ኦነግ፣ህወሃት እና የሌሎች የብሄር(ዘዉግ) ድርጅቶች ልሂቃን ሃሰተኛ ትርክትን የትግል ምክንያት አድርገዉ ማቅረባቸዉ ከሞራልም ከህግም አንጻር የሚያስጠይቃቸዉ ነዉ። ሆኖም ህዝባቸዉን ለትግል ለማነሳሳት ሲሉ የትግል ምክንያት ያሉትን (ሃሰቱ ቢበዛም) በወግ ሰንደዉ ያቀረቡበት እጅግ የታሰበበት እና የተቀናጀ አካሄድ ግን ከአማራ ልሂቃን ጋር ለዉድድር እንኳን የማይቀርብ ነዉ።

እነዚህ ልሂቃን ሃሰተኛ ትርክትን እንኳን ያለምንም ሃፍረትና ማቅማማት እዉነት አስመስለዉ አቅርበዉ፣ ህዝባቸዉን አታግለዉ፣መንበረ ስልጣን ለመያዝ ሲበቁ እጅግ ግልጽ የሆነዉን በአማራ ህዝብ ላይ የሚደረገዉን ማንነት ተኮር በደል ሰንዶ አቅርቦ ማታገያ ማድረግ ያቃተዉ የአማራ ልሂቅ ከእራሱ በቀር ማንንም መዉቀስ አይችልም። ለረዥም ዘመናት የዘለቀዉን በአማራ ህዝብ ላይ የተደረገና እየተደረገ ያለ በደል ተንትኖ ወደ ህዝቡ ማስረጽ ሳይችል የኖረዉ የአማራ ልሂቅ ከአሁን በኋላ የሚያደርገዉ አስተዋጽኦ የቀደመ ዳተኝነቱን የሚያካክስ፣ ርብርብ በሚመስል ሁኔታ የሚደረግ መሆን አለበት። የአማራን ህዝብ ትግል አይቀሬ ያደረጉ ጥያቄዎችን ምንነት፣ ስፋትና ጥልቀት በአመርቂ ሁኔታ የማቅረቡ ስራ የበርካታ ምሁራንን የተባበረ አስተዋጽኦ የሚጠይቅ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ለመነሻ ያህል የሚሆኑ ሃሳቦችን በዚህ ሰነድ ለማንሳት ይሞከራል።

ይህን የመነሻ ሃሳብ ሰነድ ለመጻፍ አስፈላጊ ያደረገዉ የኦሮሞ ብልጽግና መራሹ መንግስት የአማራን ህዝብ ትግል ምክንያት አልቦ ለማድረግ እያደረገ ያለዉ ጥረትና በአማራዉ ልሂቅ በኩልም የትግሉን ምክንያት እስከዛሬ ሰንዶ ማቅረቡ ስላልተቻለ ለመንግስት ፍርደ-ገምድልነት በር ከፍቷል ተብሎ መታሰቡ ነዉ። በዚህ እሳቤ አነሳሽነት የተዘጋጀዉ ይህ ሰነድ የመነሻ ሃሳብ ለመስጠት ያህል የቀረበ እንጅ በራሱ ምሉዕና መዳበር የማይፈልግ የተዋጣለት አይደለም።

ከሁሉም በላይ በቂ የማጣቀሻ መጻሕፍት በማይገኝበት በእስር ቤት የተጻፈ በመሆኑ ያለቀለት ነዉ ለማለት አያስደፍርም። በመሆኑም ሌሎች ተመሳሳይ ፅሁፎች ወደ ሃሳብ ገበያዉ ቢቀርቡ የተሻለ ግንዛቤን መፍጠር ይቻላልና ተጨማሪ ጽሁፎች እንደሚከተሉ ተስፋ አደርጋለሁ፤አበረታታለሁም።

## 1.2 ሰነዱ የተተነተነበት የእሳቤ መነፅር

የማንነት ፖለቲካን ለማራመድ ዋናዉ ምዕራፍ የጠላት ምስል መፍጠር ነዉ። ይህ የጠላት ምስል በተጨባጭ በደል ያደረሰ ወይም በምናብ የተፈጠረ ጠላት (Real or Perceived Enemy) ሊሆን ይችላል። በኢትዮጵያ በብሄር(ዘዉግ) ማንነት ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ ያስጀመሩት ኦነግ/ህወሃት እና አጋሮቻቸዉ አማራ የሚባል የምናብ ጠላት (Perceived Enemy) ፈጥረዉ ስልጣን መያዝ ችለዋል። እነዚህ አማራ-ጠል የፖለቲካ ሃይሎች ስልጣናቸዉን ተጠቅመዉ አማራ ጠልነት የብሄር ፖለቲካዉ መግባቢያ ቋንቋ እንዲሆን ብዙ ሰርተዋል። በዚሁ የፖለቲካ ኮድ መሰረት በአማራ ህዝብ ላይ የሚደረግ ማንኛዉም ወንጀል( ዘር ማጥፋትን ጨምሮ) የሚያስጠይቅ ጥፋት እንዳይሆን፤ እንደዉም የብሄር ፖለቲካዉ ድል ተደርጎ የሚቆጠርና በዝምታ የሚታለፍ የፖለቲካ አዋቂነት ተደርጎ ተወስዷል። ይህ የሆነበት ዋናዉ ምክንያት አማራ ጠሉ ስርዓት የተመሰረተበት የፖለቲካ እሳቤ (Thesis) አማራዉን ከሌላዉ ህዝብ ለይቶ ማክፋፋት፣ማስጠላት፣በዝባዥ፣ጨቋኝ፣ጨፍላቂ አድርጎ የሚያቀርብ እና አማራዉን በማንኛዉም ሁኔታ መቅጣት ተገቢ እንደሆነ የሚያምን ስለሆነ ነዉ።

አማራ-ጠሉ ስርዓት ስልጣን ከያዘበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ዘመናት ፖለቲካ ማለት ብሄር ማለት እንደሆነ በይኗል። የብሄር ፖለቲካን ማስኬድ ማለት ደግሞ አማራዉን ከፖለቲካ ጨዋታ ዉጭ ማድረግ እንደሆነ የሚያስብ የፖለቲካ ዘይቤን አንብሯል። በመሆኑም በዚህ ስርዓት እሳቤ መሰረት የብሄር ፖለቲካዉ ስኬት ማለት የብሄረሰቦች ሁሉ ጨቋኝ ተደርጎ የተሳለዉን የአማራ ብሄር ከኢትዮጵያ ማህበረ-ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ሁሉ ማግለል ግፋ ሲልም ሰብአዊ መብቱን መንጠቅ እንደሆነ በግልጽም በስዉርም መግባባት የሚቻልበት ሁኔታ ላይ ተደርሷል።

ስለዚህ የስርዓቱን አማራ-ጠል ፖሊሲዎች በየአካባቢያቸዉ ለመተግበር የተሰማሩ የብሄር ፖለቲካ ልሂቃን የፖለቲካ ስራቸዉን የሚጀምሩት በአካባቢያቸዉ የሚኖሩ አማሮችን ከፖለቲካ ዉክልና ዉጭ በማድረግ፣በማፈናቀል፣በመግደል እና ንብረቱን በመቀማት የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነዉ። ይህን ማድረጉም የአማራ ጠሉ ስርዓት ዋነኛ ዓላማ ስለሆነ እንደጥፋትም እንደ ወንጀልም የሚቆጠር ሳይሆን የስርዓቱን "ጠላት" በማጥቃት መንግስታዊ መሰረቱን ማጽናት ነዉ።

በግልባጩ ስርዓቱ በአማራ ህዝብ ላይ ስለሚያደርሰዉ በደል መሞገት እና ማጋለጥ ስርዓቱ የቆመበትን የፖለቲካ እሳቤ የሚንድ ተጻራሪ እሳቤ(Anti-thesis) መፍጠር ተደርጎ ይታሰባል። ይህ ተጻራሪ እሳቤ ደግሞ የስርዓቱ ዋነኛ መቆሚያ የሆነዉን አማራ-ጠልነት የሚንድ ስለሚሆን ስርዓቱን እራሱን ድምጥማጡን የሚያጠፋ እጅግ አደገኛ እርምጃ ተደርጎ ይቆጠራል። ለዚህ ነዉ የሌላ ብሄር ፖለቲካ ልሂቃን እና እሳቤያቸዉ የብሄር ፖለቲካዉ ማገር ተደርገዉ ሲቆጠሩ የአማራ ብሄርተኛ ልሂቃን እንደ ሃገር አፍራሽ፣ ጽንፈኛ፣ ነፍጠኛ፣ አሃዳዊ፣ የድሮ ስርዓትን ሊመልሱ የሚሞክሩ ወዘተ የሚሉ ታርጋዎች ተለጥፈዉባቸዉ በየእስር ቤቱ የሚታጎሩት፤የሚገደሉት እና የሚሳደዱት። የሌላ ብሄር ልሂቃን የፖለቲካ እሳቤ እንደ ህብረ-ብሄራዊ ፖለቲካ ግብአት ተደርጎ ሲወሰድ "የአማራ ብሄርተኝነት ሃገር ያፈርሳል" ተብሎ የሚብጠለጠለዉም በዚሁ እሳቤ መሰረት ነዉ። በአምባገነን መንግስታት አስተሳሰብ የዘረጉትን ጨቋኝ ስርዓት መታገል ሃገርን የማፍረስ ወንጀል ተደርጎ ፕሮፓጋንዳ እንደሚደለቅበት የሚታወቅ ነገር ነዉ። በአማራ-ጠሉ ስርዓት ላይ የተጀመረዉ የአማራ ህዝብ ትግል በሃገር አፍራሽነት የሚከሰሰዉም በዚሁ ምክንያት ነዉ።

ጠቅለል ሲል ከ1983 ዓ.ም እስከ አሁን ድረስ ስልጣን ላይ በተሰየመዉ አማራ-ጠል ስርዓት ዉስጥ በአማራ ህዝብ ላይ ሁለንተናዊ በደል መፈጸም ስርዓቱ የተገነባበት እሳቤ(thesis) ሲሆን ስለ አማራ ህዝብ በደል ማብቃት መታገል ደግሞ ስርዓቱን የሚንድ ተጻራሪ እሳቤ(anti-thesis) ነዉ ማለት ነዉ። ስለሆነም አሁን ስልጣን ላይ ያለዉ አማራ-ጠል ስርዓት የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች ይመልሳል ማለት ራሱን ለማጥፋት በራሱ ላይ ይፈርዳል ማለት ነዉ። ጠላቱ ላለዉ የአማራ ህዝብ መፍትሄ ለማምጣት ሲል ራሱን የሚያጠፋ ፖለቲካዊ ስርዓት ይኖራል ብሎ መጠበቅ ትልቅ ስህተት ነዉ።

ለዚህ ነዉ የአማራ ህዝብ ትግል የስርዓት ለዉጥን የሚጠይቀዉ። አማራ-ጠሉ ስርዓት በበኩሉ የአማራ ህዝብ ለስርዓት ለዉጥ የሚያደርገዉን ትግል እንደ ትልቅ የፖለቲካ ሃጥያት አድርጎ ለማቅረብ ይሞክራል፣በሃገር አፍራሽነትም ይከሳል። ይህን ክሱን ተንተርሶ "ሃገርን ከአፍራሾች" በማዳን ሽፋን አማራ-ጠል ፖሊሲዉን የሚያስቀጥልበትን ስልጣኑን ለማስቀጠል የሞትሽረት ትግል እያደረገ ነዉ።

አማራ-ጠሉ ስርዓት ስልጣኑን ለማስቀጠል ከሚጥርባቸዉ ስልቶቹ ዋነኛዉ የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች በስርዓቱ ጥላ ስር ለመመለስ እንደሚችል አድርጎ የሚያቀርበዉ "ሆድ ሲያዉቅ" የሆነ አካሄድ ነዉ። ይህ አካሄድ እዉነት መስሎት የአማራ ህዝብ ጥያቄዎቹን ለስርዓቱ ሲያቀርብ ኖሯል። ሆኖም ስርዓቱ በአፉ ስለሃገራዊ አንድነት እና አብሮነት እያወራ በተግባር ግን አማራን እያሳደዱ መፍጀቱን እያባባሰ ቀጠለበት። ይህን የስርዓቱን ባህሪ ለሶስት አስርት አመታት ከተግባራዊ ተሞክሮ የተረዳዉ የአማራ ህዝብም በአሁኑ ወቅት የስርዓት ለዉጥን ብቻ መፍትሄ አድርጎ ትግሉን አፋፍሟል። አማራ-ጠሉ ስርዓትም በበኩሉ ይህን የአማራ ህዝብ ትግል "ህገ-መንግስታዊ ስርዓትን በሃይል ለመጣል የተደረገ ሙከራ ነዉ" ሲል የአዞ እንባ ያነባል። የአማራ ህዝብ በአሁኑ ሰአት እያደረገዉ ያለዉ ትግል የትጥቅ ትግልን የጨመረ መሆኑ መንግስት የሚከሰዉን መሰሪ ክስ እዉነተኛ ሊያስመስለዉ ይችላል። ሆኖም ማመዛዘኛ ህሊና ላለዉ ሰዉ ሁሉ ግልጽ የሆነዉ ሃቅ የአማራ ህዝብ ዛሬ ላይ ጠመንጃን የጨመረ ትግል ለመታገል የቆረጠዉ ለስንት አመታት ሰላማዊ ጥያቄ ሲጠይቅ ኖሮ መልስ በማጣቱ ነዉ። ሌላዉ ሃቅ የአማራን ህዝብ ህገ-መንግስታዊ ስርዓትን በሃይል ለመናድ በመሞከር የሚከሰዉ መንግስት ራሱን ህገ-መንግስታዊ ስርዓት እያለ ይጥራ እንጂ ይህን የሚያስብል ጠባይ የሌለዉ መሆኑ ነዉ።

ስርዓቱ ህገ-መንግስታዊ ለመባል በትንሹ በህገ-መንግስቱ የተጠቀሱትን የህዝብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር ይጠበቅበት ነበር። በተግባር የሚታየዉ ሃቅ ግን የመንግስት አስተዳደር ዘይቤ ከዉንብድና ጋር የሚዋሰን፣ሁሉን ነገር በአፈና ለማስፈጸም የሚሞክር፣የሃገሪቱን ትምህርት ቤቶች እና የጦር ካምፖች ሳይቀር የፖለቲካ እስረኞች ማጎሪያ ያደረገ፣በስርዓት አልበኝነቱ የሚኩራራ አይነት ነዉ።

ይህንኑ ልምዱን ወደ ዉጭ ሃገር ሰራተኞች በማስፋት የአፍሪካ ልማት ባንክ ሰራተኞችን እስከ ማፈን እና መደብደብ የደረሰ  አንገት አስደፊ አስተዳደር ነዉ፡፡ እንዲህ አይነት መንግስት “ህገ-መንግስታዊነኝና ማንም አይንካኝ” ማለቱ ራሱ የስርዓት አልበኝነቱ አካል ነዉ፡፡ በስርዓቱ ዉስጥ ከላይ እስከታች የተሰየሙ መሪዎች ከሃገር ቤት አልፎ በአህጉርና ዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ትዝብት ላይ የጣላቸዉን ፋሽስታዊ የአፈና ተግባራቸዉን ለማሻሻል አንድ ስንዝር የማይራመዱ፣ሃገርን በጣፈጠ ቋንቋ እና በአስቃቂ ጭካኔ መምራት ይቻላል ብለዉ የሚያስቡ፣ የህዝብን ጥያቄ ለማድመጥ አምባገነናዊ ተፈጥሯቸዉ የማይፈቅድላቸዉ ናቸዉ፡፡ በእነዚህ እና በሌሎች አምባገነናዊ ተፈጥሯቸዉ ምክንያት ስርዓቱ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ለመባል ዝቅተኛዉን መስፈርት እንኳን የማያሟላ ነዉ፡፡ ስለሆነም የአማራ ህዝብ በአሁን ወቅት እያደረገዉ ያለዉ ትግል ለኢ-ፍትሃዊነት እና ለአምባገነንነት የሚሰጥ ተገቢ ምላሽ እንጂ የሌለን ህገ-መንግስታዊ ስርዓት የመናድ ወንጀል አይደለም፡፡

# ክፍል ሁለት

## የአማራ ህዝብ ጥያቄዎች



## 2.1 የአማራ ህዝብ ጥያቄዎች

የአማራ ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር የሚጋራዉ የዲሞክራሲ፣የመልካም አስተዳደር እና የልማት ጥያቄዎች ያሉ ቢሆንም አማራ በመሆኑ ምክንያት ከደረሰበት ማንነት ተኮር በደሎች የተነሳ የሚያነሳቸዉ የራሱ የሆኑ ብሄር ተኮር ጥያቄዎች አሉት። እነዚህን የአማራ ህዝብ ብሄር ተኮር ጥያቄዎች በሰፊዉ በሁለት መክፈል ይቻላል። እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸዉ:-

### 2.1.1 የህልዉና ጥያቄዎች

### 2.1.2 የፍትህ ርትዕ ጥያቄዎች

እነዚህ በሰፊዉ ለሁለት የተከፈሉ ጥያቄዎች በዉስጣቸዉ በርካታ ሃሳቦች ያመቁ ናቸዉ። የአማራ ህዝብ ጥያቄዎች የሚመነጩት ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ስልጣን ላይ ከመጣዉ ስርዓት አማራ-ጠል ተፈጥሮ ነዉ። ይህ ስርዓት ለኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ችግሮች ሁሉ አማራዉን ተጠያቂ የሚያደርግ ነዉ። በዚሁ እምነቱ ምክንያት የሚያወጣቸዉ ፖሊሲዎች ሁሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አማራዉን የሚበድሉ፣የሚቀጡ እና የሚያገሉ ናቸዉ። እነዚህ ፖሊሲዎች በዉጤታቸዉ በአማራ ህዝብ ላይ ከጄኖሳይድ እስከ አፓርታይድ የሚዘረጉ ወንጀሎች እንዲፈጸሙበት አድርጓል። እነዚህን ወንጀሎች ማስተናገዱ ደግሞ የአማራ ህዝብ ፈርጀ ብዙ የህልዉና ጥያቄዎችን እንዲያነሳ አስገድደዉታል።

ሆኖም አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራ ህዝብ የሚያነሳቸዉን የህልዉና ጥያቄዎች ለመመለስ ቀርቶ ሊሰማ አይፈልግም።የመደመጥ መብቱን እንኳን መነፈጉ ደግሞ የአማራ ህዝብ የፍትህ ርትዕ ጥያቄ እንዲያነሳ አስገድዶታል። ከላይ በሰፊዉ ለሁለት የተከፈሉት የህልዉና ጥያቄ እና የፍትህ ርትዕ ጥያቄዎች በዉስጣቸዉ በርካታ እምቅ ሃሳቦችን የያዙና በዉል መተንተን ያለባቸዉ ስለሆነ ወደዛዉ ልለፍ።

## 2.1.1 የአማራ ህዝብ የህልዉና ጥያቄዎች

የአማራ ህዝብ ትግል የህልዉና ትግል እንደሆነ በአማራ ብሄርተኛ ልሂቃን ዘንድ በሰፊዉ መነገር ከጀመረ ሰንበትበት ብሏል። ልሂቃኑ የህልዉና ጥያቄ ሲሉ የፖለቲካ ቅርፀ-ሃሳብ (Political Framing) የሰጡትን የአማራ ህዝብ ጥያቄ ትርጉም አልባ ባዶ ጩኸት ነዉ የሚል ማጣጣያ ከአማራ-ጠሉ ጎራ ይሰማል። አማራ-ጠሉ ጎራ ይህንን ማጣጣያ ይዞ ሲመጣ የሚያቀርበዉ መከራከሪያ የአማራ ህዝብ ቁጥሩ ብዙ ስለሆነ ቁጥሩ አናሳ የሆነ ህዝብ የሚያነሳዉን የህልዉና ስጋት ማንሳት የለበትም የሚል ነዉ። በዚህ ክርክር ዉስጥ የህልዉና ስጋት ሊኖርበት የሚችለዉ ቁጥሩ አነስተኛ የሆነ ህዝብ ብቻ ነዉ የሚል እሳቤ አለ። ይህ ክርክር ተራ ስህተትን ያዘለ ስለሆነ የክርክሩን ቀሊልነት በሚመጥን ምሳሌ ስሁትነቱን ማጋለጥ ግድ ይላል። ይህ ክርክር አንድ ቁመቱ ዘለግ፣ ሰዉነቱ ደንደን ያለ ሰዉ ከወደ እግሩ በኩል ጥቂት ኢንች ቢቆረጥለት፤ ቁመቱ አጠር ሰዉነቱ ከሳ እንዳለ ሰዉ ችግር ደረሰብኝ ማለት የለበትም እንደማለት ነዉ። ክርክሩን የሚያመጡ ሰዎችም (በተለይ ምሁራኑ) ነገሩ ጠፍቷቸዉ አይደለም። ይህን የሚሉት ለምን እንደሆነ በሚቀጥሉት የሰነዱ ክፍሎች የሚብራራ ይሆናል። የአማራ ህዝብ የህልዉና ስጋት አለበት ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጡ በአማራ-ጠሉ ስርዓት ለሚመጣዉ ልብ አዉላቂ ክርክር ተገቢ መልስ የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን የአማራ ህዝብ ለተያያዘዉ የህልዉና ትግልም የጠራ መነሻ እና መድረሻ መንገድን የሚተልም ነዉ።

አንድ ህዝብ የህልዉና ስጋት አለበት ሲባል ህልዉ ሆኖ መኖር በሚገባዉ ፈርጀ ብዙ የህይወት ገፅታዎች ላይ ህልዉ ሆኖ እንዳይታይ(እንዳይኖር) የሚያደርግ አደጋ ተጋርጦበታል ማለት ነዉ። እነዚህ የህይወት ገጽታዎች ማህበረ-ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ግዛታዊ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ። በእነዚህ የህይወት ገጽታዎች ህልዉ ሆኖ ለመገለጥ ደግሞ የሰዉ ልጅ በህይወት መኖር አለበት።

በህይወት የመኖር መብትን የማስከበር ትግል በሌሎች የህይወት ገጽታዎች ህልዉ የመሆን መብትን የማስከበሪያዉ ዋናዉና ብቸኛዉ መንገድ ነዉ። በተመሳሳይ የህልዉና ስጋት ማለት በህይወት የመኖር መብትን መነፈግ ማለት ብቻ አይደለም።

የሰዉ ልጆች በህይወት እየኖሩም እንደ አፓርታይድ ባሉ የመንግስት ፖሊሲዎች የሚተዳደሩ ከሆን በሃገራቸዉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያ እና ማህበራዊ መስኮች ላይ ህልዉ የመሆን መብታቸዉን የማጣት አደጋ ላይ ናቸዉ ማለት ነዉ። ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ የህልዉና ስጋት ማለት በህይወት የመኖር መብትን የማጣት ስጋት ብቻ እንዳልሆነ ነዉ። በህይወት የመኖር መብትን የማጣት አደጋ የህልዉና አደጋዎች ቁንጮ ቢሆንም አንድ ህዝብ በገዛ ሃገሩ ፖለቲካ ዉስጥ እጣ ፈንታ እንዳይኖረዉ፣ "ወደ ስልጣን ድርሽ አይልም" ከተባለ፣በኢኮኖሚ ሃብት እንዳያፈራ የሚደረግ ከሆነ ወዘተ በህዝቡ ላይ የተቃጣ ፈርጀ ብዙ የህልዉና አደጋ አለ ማለት ነዉ።

የህልዉና ስጋትን የሚያመጣዉ ምን እንደሆነ መረዳቱም የአማራ ህዝብ የተጋረጠበትን የህልዉና ስጋት በተጨባጭነት ለመረዳት ይጠቅማል። አንድን ህዝብ በማንነቱ ነጥሎ ለህልዉና ስጋት የሚዳርገዉ እሳቤ የሚመነጨዉ ከበዳይ ተበዳይ ትርክት ነዉ። አንድ ተበድያለሁ ብሎ አጥብቆ የሚያምን የፖለቲካ ቡድን ይህ እምነቱ "በድሎኛል እና ጠላቴ ነዉ" ብሎ በፈረጀዉ ሌላ ማህበረሰብ(ቡድን) ላይ ለሚያደርሰዉ ማንኛዉም የጭካኔ ድርጊት የተገቢነት ማስተማመኛ ይሰጠዋል። ተበድያለሁ የሚለዉ ቡድን የፖለቲካ ስልጣን የያዘ ከሆነ ደግሞ የተበድዬ ስነ-ልቦናዉ የወለደዉን የበቀል ጥማት ህግና ፖሊሲ አድርጎ በማቅረብ የተገቢነት ገጽታ ይሰጠዋል (The Anatomy of Fascism P.219)[1] በዚህ አይነት ሁኔታ የህግና ፖሊሲ ድጋፍ ተሰጥቶት እንደትክክለኛ ድርጊት የተቆጠረ ጭካኔ እና በደል ምንም አይነት የህግም ሆነ የሞራል መርሆ ሊገታዉ አይችልም። እንዲህ ያለ በህግና በፖሊሲ የተደገፈ የጥላቻ ፍላፃ የተነጣጠረበት(የተሰነዘረበት) ህዝብ ነዉ በህልዉና አደጋ ዉስጥ ያለ ህዝብ ነዉ የሚባለዉ።

አማራ ጠላቴ ነዉ ብሎ ፈርጆ፣ ይህንኑ ጥላቻዉን በማኒፌስቶ ጀምሮ በህገ-መንግስት "የተዛባ የብሄረሰቦች ግንኙነት ነበር" የሚል ሃሳብ በማስፈር ስልጣንን የጨበጠዉ አማራ-ጠል መንግስታዊ ስርዓት በአማራ ህዝብ ላይ የህልዉና አደጋ የሚጋርጡ ሁኔታዎችን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ ፈጥሯል።

---

[1] Robert O. Paxton (2004) . The Anatomy of fascism. New York. Alfred A. Knopf Publisher

ስልጣን ላይ ባለዉ ስርዓት በበዳይነት የተፈረጀዉ የአማራ ህዝብ ግልፅ የሆነ የህልዉና ስጋት አለበት የሚለዉ የአማራ ብሄረተኛ ልሂቃን ክርክር ይህን ሃቅ መሰረት ያደረገ ነዉ። የአማራ ህዝብ የህልዉና አደጋ አለበት ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ከመረዳቱ እኩል አደጋዉ የሚገለጥባቸዉን መንገዶችም ማወቅ አስፈላጊ ስለሆነ ቀጣዩ ክፍል የአማራ ህዝብ የህልዉና አደጋ የሚገለጥባቸዉን መስኮች ያብራራል።

# 1 የህይወት ህልዉና

በህይወት የመኖር መብት የሰዉ ልጆች ሰዉ ሆነዉ በመፈጠራቸዉ ፀጋ ካገኟቸዉ መብቶቻቸዉ ዉስጥ አንዱ ሲሆን የሌሎች መብቶች ሁሉ ቁንጮ ነዉ። በህይወት የመኖር መብቱን የተነፈገ ሰዉ (ቡድን) ሌሎች መብቶች ሊኖሩት አይችሉም። በመርህ ደረጃ በህይወት የመኖር መብት (ሌሎች ሰብአዊ መብቶችም) በማንኛዉም ሁኔታ ከሰዉ ልጅ ላይ ሊነጠቁ የማይችሉ መብቶች ናቸዉ። በተግባር ሲታይ ግን (የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስለ ሰብአዊ መብቶች የማይገረሰስ ልዕልና የሚያወሱ በርካታ ህግጋትን ካወጣ በኋላ እንኳን) በአፍሪካ ብቻ የሩዋንዳዉ የዘር ፍጅት፣የሱዳኑ የዳርፉሩ እልቂት፣የናይጀሪያ የቢያፍራዉ መተላለቅ ተከስተዋል። በሃገራችንም ስለሰብአዊ መብቶች በአያሌ ገጾቹ የሚያትት ህገ-መንግስት በተጻፈ ማግስት ማንንም ያላስጠየቁ፣የማንም ጉዳይ የማይመስሉ ማንነት ተኮር እልቂቶች በአማራ ህዝብ ላይ ተፈጽመዋል። ይህ የሚያመለክተዉ የህግጋት መፃፍ ብቻዉን ለሰዉ ልጆች ሰብአዊ መብት መከበር ዋስትና እንደማይሰጥ ነዉ።

በህይወት የመኖር መብትና ሌሎችን የሰዉ ልጆች ሰብአዊ መብቶችን በማስከበሩ ረገድ ዋስትና ማግኘት የሚቻለዉ በሃገራት ፖለቲካ ዉስጥ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን ማስፈን ሲቻል ነዉ። በሰብአዊ መብቶች መከበር እና በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር መስፈን መካከል እጅግ በጣም ጥብቅ ቁርኝት አለ። ዲሞክራሲ ባልሰፈነበት ሃገር የሰብአዊ መብቶችን መከበር መሻት ሳም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነዉ። በሃገራችን ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን እዉን ማድረግ ባለመቻሉ የሰብአዊ መብቶችን ማስከበር አልተቻለም።

የሃገራችንን ሁኔታ በአፍሪካ ደረጃ ሲመዘን እንኳን ብዙ እንዲቀረዉ ያደረገዉ ዲሞክራሲን ያሰፍናል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበት የነበረዉ ህወሃት ወደ ስልጣን ሲመጣ ቀዳሚዉ የደርግ ስርዓት በነበረዉ ኢ-ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ዘይቤ ላይ ዘረኝነትን (ብሄርተኝነትን) አክሎበት ወደ ፋሺዝም የሚጠጋ አስተዳደር በማስፈኑ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ ኢ-ዲሞክራሲያዊ የመንግስት አስተዳደር በርካታ አይነት መልኮች ያሉት ነዉ፡፡ ዘረኝነትን ማጠንጠኛቸዉ ያደረጉ የኢ-ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር አይነቶች ግን እንደፋሺዝም/ናዚዝም አይነት መልክ ያላቸዉ፣በዘግናኝነታቸዉ ዓለምን ያስደነገጡ የዘር ፍጅቶችን እንደ መንግስታዊ የአስተዳደር ዘይቤ የሚጠቀሙ ናቸዉ፡፡ እንደዚህ ባሉጨካኝ መንግስታት ጠላት ተብለዉ የሚፈረጁ ህዝቦች(ቡድኖች) በዘር ማንነታቸዉ ስለሆነ "የጠላት ዘር" እስከሆኑ ድረስ በእናታቸዉ ማህጸን ያሉ ህጻናት ሳይቀሩ የፍጅቱ ዒላማ ከመሆን አያመልጡም፡፡ በአንጻሩ በኢ-ዲሞክራሲያዊ ተፈጥሮዉ ከናዚዝም እና ፋሽዝም የአስተዳደር ዘይቤ ተርታ የሚመደበዉ ኮሚኒዝም ጠላትን የሚበይነዉ ከመደብ አንጻር ስለሆነ ለአቅመ መደብ ያልደረሱ ህጻናትን የሚፈጅበት ሁኔታ አልተመዘገበም፡፡ በዚህ ረገድ ኮሚኒዝም ከፋሽዝም/ናዚዝም የተለየ ገፅታ ያለዉ ስርዓት ነዉ፡፡

በሃገራችን ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ስልጣን ላይ የመጣዉ አማራ-ጠል አስተዳደር ዋነኛ መስራች ህወሃት በታጣቂነት ዘመኑ ኮሚኒስት ነኝ ሲል የኖረ ቢሆንም ስልጣን ሲይዝ በአማራ ህዝብ ላይ ሴት ከወንድ፣ህጻን ከአዋቂ ሳይለይ ያደረሰዉ ማንነት ተኮር እልቂት ከማንም የተሰወረ አይደለምና እሱን ወደ ማዉሳት መግባቱ አስፈላጊ አይደለም፡፡ አሁን አስፈላጊ የሆነዉ ነገር በአማራ-ጠሉ ስርዓት አጋፋሪነት በአማራ ህዝብ ላይ የደረሰዉ ማንነት ተኮር ፍጅት ለአሁኑ የአማራ ህዝብ ትግል መፋፋም ያደረገዉን አስተዋጽዖ ማስቀመጡ ነዉ፡፡ አማራ ጠሉ ስርዓት የአማራን ህዝብ በህይወት የመኖር መብት ጥያቄ ሊክድ የሚሞክርባቸዉን ማምታቻዎች በማምከን የአማራ ህዝብ ትግሉን አጠናክሮ የሚቀጥልበት ሃቆችን ማስጨበጥም ሌላዉ አስፈላጊ ነገር ነዉ፡፡ ይህን ማድረግ ያስፈለገበት ዋናዉ ምክንያት ደግሞ አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራ ህዝብ አሁን የሚያደርገዉ ትግል ምክንያቱ የክልሉ ልዩ ሃይል መፍረስ ብቻ እንደሆነ አድርጎ ለማቅረብ እየተሟሟተ በመሆኑ ነዉ፡፡ ስርዓቱ ይህን የሚያደርግበት ራሱን የቻለ ምክንያት አለ፡፡

የአማራ ህዝብ ዛሬ ላይ እያደረገዉ ያለዉ ኮስተር ያለ ትግል ምክንያቱ አማራ-ጠሉ ስርዓት ስልጣን ከያዘበት ዘመን ጀምሮ ያደረሰበት ማለቂያ የለሽ የጭካኔ ግፎች እንጂ በክልሉ ልዩ ሃይል መፍረስ ብቻ አይደለም። በእርግጥ ከሌሎች የሃገራችን ክልሎች በተለየ እና በፈጠነ ሁኔታ የአማራ ልዩ ሃይልን ማፍረሱ ስርዓቱ በአማራ ህዝብ ላይ ሲያደርግ የኖረዉን ግፍ ለማስቀጠል የሚከለክለዉ ሃይል እንዳይኖር በመፈለጉ ነዉ። ስለዚህ የልዩ ሃይሉ መፍረስ የአማራን ህዝብ ለጥያቄ የማያስነሳ ነገር አይደለም። ሆኖም የልዩ ሃይሉ መፍረስ የአማራ ህዝብ አብይ(major) ጥያቄ ሳይሆን የስርዓቱ አማራ-ጠልነት ማሳያ ሌላ ምልክት ነዉ። ስርዓቱ የአማራ ልዩ ሃይልን መፍረስ ጉዳይ እንደ ብቸኛ ምክንያት የሚያስጮኸዉ የአማራ ህዝብ በአብይ(major) ጥያቄዎቹና በንዑስ(minor) ጥያቄዎቹ መካከል ተደናግሮ አበይት ጥያቄዎችን ትቶ በንዑስ ጥያቄዎች ላይ እንዲጠመድ ለማድረግ ነዉ። በንዑስ ጥያቄዎቹ ሲጠመድ ንዑስ መልሶች በመስጠት ወይም በማደናገር አብይ ጥያቄዎቹን ለማዳፈን የተደረገ የመሰሪ ተግባር ነዉ።

ከአማራ ህዝብ ዋነኛ ጥያቄዎች ቀዳሚዉ ለሰላሳ አመታት አደጋ ዉስጥ ወድቆ የቆየዉ በህይወት የመኖር መብቱን የማስከበር ጥያቄ ነዉ። የአማራን ህዝብ አንገት በማስደፋት፣በማሳደድና በመፍጀት የፖለቲካ ስኬቱን የሚለካዉ አማራ-ጠሉ ስርዓት ደግሞ በአማራ ህዝብ ላይ ለሰላሳ አመታት ሲፈጽምና ሲያስፈጽም የቆየዉን የዘር ማጥፋት መንግስታዊ ወንጀል ማመን አይፈልግም። ምክንያቱም ሁለት ነዉ። የመጀመሪያዉ ምክንያት በአማራ-ጠሉ አስተሳሰብ ጠላት ተደርጎ የተሳለዉን የአማራ ህዝብ መፍጀት የፖለቲካ ስኬት እንጅ ወንጀል ተደርጎ ስለማይቆጠር ነዉ። ሁለተኛዉ ምክንያት ስርዓቱ በአማራ ህዝብ ላይ የፈጸመዉ አሰቃቂ የዘር ማጥፋት ወንጀል በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የሚያስጠራ ትልቅ ወንጀል ስለሆነ የስልጣኑ ፀሃይ ስትጠልቅ በፍርድ አደባባይ መቆሙን ስለሚያዉቅ ከወዲሁ ወንጀሉን መካዱን እንደ ማምለጫ በመቁጠሩ ነዉ።

የአማራ-ጠሉ ስርዓት የምሁራን ክንፍ በአማራ ህዝብ ላይ ሲፈጽም የኖረዉን የዘር ማጥፋት ወንጀል በመካዱ ረገድ ከካድሬ ፖለቲከኞቹ በተሻለ ሁኔታ በአመርቂ መንገድ እየፈፀመ ኖሯል።

ምሁራኑ የስርዓታቸዉን ወንጀል ሲክዱ ደግሞ ፖለቲካዊ ፍላጎታቸዉን በምሁራዊ ዉስብስብ ጽንሰ ሃሳቦች ሸፍነዉ ለማቅረብ ስለሚሞክሩ እዉቀቱ ላይ እስከዚህም ከሆኑት ፖለቲከኛ አጋሮቻቸዉ በተሻለ ድንጋሬን ፈጥረዋል። በዚህም ምክንያት የአማራ ህዝብ መብቶቹን ለማስጠበቅ ከመነሳት ሲያመነታ ዘመናት አልፈዋል። ከማደናገሪያዎቹ አንዱ በኢትዮጵያ ዉስጥ በተለይ በኦሮሚያና በቤንሻንጉል ክልሎች የሚደረጉ(የተደረጉ) ግድያዎች ዘር ማጥፋት ለመባል አይበቁም ስለሆነም አማራዉ ስርዓቱን በዘር ማጥፋት መክሰስ አይችልም የሚል ነዉ። ይህ አባባል በዓለም አቀፍ ደረጃ ለዘር ማጥፋት ወንጀል የተሰጠዉን ብያኔ ለመሸሽ የሚደረግ ነዉ።

በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች፣ በምሁራዊ መዛግብትና በሌሎች ሁኔታዎች በተጠቀሱ ብያኔዎች ("Genocide Watch"ን በመሰሉ ተቋማት) በሰዉ ልጆች ላይ የተፈጸመ ግድያ ዘር ማጥፋት ለመባል ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ቀዳሚዉ ግድያዉ የተፈጸመበት አላማ (intention)ዘርን፣ብሄርን፣ ሃይማኖትን ወዘተ መሰረት አድርጎ ከሆነ የሚል ነዉ። ሁለተኛዉ መለያ ደግሞ ግድያዉን ለማድረግ ተጨባጭ ድርጊት (Action) ተፈጽሟል ወይ የሚለዉ ነዉ። በእነዚህ ሁለት አበይት መለያዎች መካል የሚደረጉ ወደ ሰባት የሚጠጉ አያያዥ ተግባራት አሉ። ዘር ማጥፋት የሚደረግባቸዉን ህዝቦች ከሰብአዊነት አዉርዶ ማጠልሸት (Dehumanization) የጅኖሳይድ መፈጸሚያ ስም በመስጠት መለየት (Identification)፣ ዘር ማጥፋቱን የሚፈጽሙት አካላትን ማሰልጠን፣ማስታጠቅ፣ማዳዝ፣የዘር ማጥፋቱ የሚፈጸምባቸዉ እንደ መሳሪያ ያሉ ግብዐቶችን ማዘጋጀት (Preparation) ወዘተ በሁለቱ አበይት የዘር ማጥፋት መለያዎች መሃከል የሚታዩ መሸጋገሪያ ድርጊቶች ናቸዉ። በአማራ ህዝብ ላይ የተደረጉ የዘር ማጥፋት ወንጀሎች እነዚህን ሁሉ በተገቢዉ ሁኔታ ያሟሉ ናቸዉ።

አንድ ግድያ ዘር ማጥፋት ለመባል ማንነትን በነጠለ ሁኔታ ለማጥቃት የታለመ ዓላማ ካለዉ ነዉ የሚለዉ የመጀመሪያዉን መስፈርት ብንመለከት በኦሮሚያ፣በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እናም በሌሎችም ክልሎች በአማራ ህዝብ ላይ የሚደረገዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ቦታዎቹን ከአማራ ማጽዳትን አላማ ያደረጉ ናቸዉ። ለዚህ መሰረት የሆነዉ ደግሞ ኦሮሚያን ለኦሮሞ የሚለዉ የኦሮሞ ብሄርተኝነት የፖለቲካ አስኳል መርህ ነዉ።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝም ሆነ በሌሎቹም ክልሎች ሁኔታም የየክልሎቹ ህገመንግስታት የክልሎቹ ባለቤት ያሏቸዉን ህዝቦች በይነዉ ሌሎችን እንደመጤ የሚቆጥሩ ናቸዉ። በዚህ ላይ አማሮች ደግሞ በጠላትነት፣ በጨቋኝነትና በጨፍላቂነት የሚከሰሱ ከሌላዉ ተለይተዉ ይሳደዱ ዘንድ በአማራ-ጠሉ ስርዓት የተበየነባቸዉ ናቸዉ። ከእነዚህ ፖለቲካዊና ህጋዊ ማዕቀፎች በተጨማሪ ከዘር ማጥፋቱ ያመለጡ አማሮች ገዳዮቹ አማራን ለይተዉ ሃገራችንን ልቀቁ እንደሚሉ፣ ተአስተዳዳሪዎቹ አቤት ሲባልም "ገዳዮቹ ሃገራቸዉ ነዉ፣እናንተ ሃገራችሁ ስላልሆነ እንደሚሏችሁ መሬታቸዉን ለቃችሁ ሂዱ" እንደሚሏቸዉ በተለያዩ ሚዲያዎች የሚገልጹት ነዉ። ስለዚህ የግድያዉ ዓላማ በብሄር የተለዩ አማሮችን ከየአካባቢዎች ማጽዳት ነዉ ማለት ነዉ። ዘር ማጥፋት ደግሞ ዘር የማፅዳት አንደኛዉና አሰቃቂዉ መንገድ ነዉ።ይህን አላማ ለማሳካት ተጨባጭ እርምጃ ተወስዷል ወይ ለሚለዉ መለኪያም ለሰላሳ አመታት በአማራ ህዝብ ላይ መንግስታዊ ቅንጅት/ዝምታ(በክልልና ፌደራል መንግስታት)በተጨባጭ የተደረጉ ግድያዎች ምስክር ናቸዉ።

ከአማራ-ጠሉ ጎራ/ምሁራን የሚነሳዉ ሌላ ማደናገሪያ "አማራ ብቻ አልሞተም፣ሌሎች ህዝቦችም ሞተዋል" የሚል ነዉ። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር የአማራ ህዝብ የሌሎችን ህዝቦች ሞት እንደ መፅናኛ ቆጥሮ፣እንደመልካም ነገር ተቀብሎ ትግሉን የሚያቆም አለመሆኑ ነዉ። ለአማራ ህዝብ የተደገሰዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል አልፎ አልፎ ሌሎች ህዝቦችንም ሰለባ የሚያደርግበት ሁኔታ እንዳለ የሚካድ ነገር አይደለም። በዚህም የአማራ ህዝብ የሚደሰትበት ነገር አይደለም። ይልቅስ የአማራ ህዝብ ትግል ራሱም ሌሎች ኢትዮጵያዉያን ወገኖቹም በሰላም የሚኖሩበት፣እንደፈለጉ ተዘዋዉረዉ ሰርተዉ የሚያድጉበት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለመፍጠር ያለመ ነዉ። ወደ ዋናዉ ነጥብ ስንመለስ በአማራ ህዝብ ላይ እየተፈጠረ ያለዉ የዘር ማጥፋት ሌሎችን ህዝቦችንም ተጠቂ የማድረጉ ነገር የአማራ ህዝብ በማንነቱ የተቃጣበትን በህይወት የመኖር መብት የመነጠቅ አደጋ የማጥፋፋት አቅም የለዉም። ይህን በቅጡ ማብራራት አማራ-ጠሉ ስርዓት የሚደበቅበትን አንድ ዋሻ ማፍረስ ነዉና ወደ እዛዉ እንለፍ። ይህን ለማድረግ አሁንም የዘር ማጥፋት ትርጉምን ወደ ሚበይኑ ሃቶች እንመለስ።

በሰዉ ልጆች ላይ የተፈጸመ ግድያ የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመባል ከግድያዉ ጀርባ ያለ ፍላጎት(Intention) ብሄርን፣ዘርን፣ሃይማኖትን የመሳሰሉ ማንነቶችን ለይቶ የሚያጠቃ መሆን እንዳለበት ከፍ ብሎ ተጠቅሷል፡፡ በወለጋ፣ቤንሻንጉል ጉሙዝ እና ሌሎች ክልሎች በአማራ ህዝብ ላይ የተደረጉ ማንነት ተኮር ግድያዎች ደግሞ አማራ /ነፍጠኛ/ በሚል እና የነፍጠኛ ሃይማኖት ተከታይ በሚልም ሃይማኖትንም መሰረት ያደረገ የዘር ማጥፋት ኮድ ተሰጥቶት የተፈጸመ እንደሆነ የመንግስት አካል የሆነዉ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንም ሪፖርት ያደረገዉ ነገር ነዉ፡፡ ስለዚህ ዘር ማጥፋቱ ሲፈጸም ኢላማ/Target/ አድርጎ የተነሳዉ አማራነትን ነዉ ማለት ነዉ፡፡ አማራዉን ከየአካባቢዉ ለማጽዳት ኢላማ/Target/ አድርጎ የተነሳዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ወደ ተግባር በገባበት ሂደት አማራ ያልሆኑ ወገኖችንም በተለያዩ ምክንያቶች ሰለባ/Victim/ አድርጓል:: እነዚህ አማራ ያልሆኑ ወገኖች ሰለባ/Victim/ የሆኑበት ምክንያት ዒላማ ከሆነዉ ከአማራ ህዝብ ጋር በአንድም በሌላ የተገናኘ ነዉ፡፡ አማራ ያልሆኑ ወገኖች የሚገደሉበት ምክንያት ለምሳሌ ሰብአዊነት ተሰምቷቸዉ በአማራዉ ላይ በሚደረገዉ ግድያ ላይ ተቃዉሞ አሰምተዉ፣የሚገደሉ አማሮችን ደብቀዉ፣ለመግደል አብረዉ አልሰለፍ ብለዉ ሊሆን ይችላል፡፡ "የአማራ" የተባለን ሃይማኖት መከተላቸዉም ለግድያዉ ምክንያት ሊሆን የቻለ ነገር ነዉ፡፡

በአለም ላይ በተከሰቱ የዘር ማጥፋት እርምጃዎች ላይ ኢላማ/Target/ እና ሰለባ/Victim/ ህዝቦች መኖራቸዉ የተለመደ ነገር ነዉ፡፡ መረሳት የሌለበት ነገር ግን ሰለባ ህዝቦች መኖራቸዉ የግድያዉን ዘር ማጥፋትነት ተፈጥሮ የሚቀይር እንዳልሆነ እና የዘር ማጥፋት ወንጀል የተፈጸመባቸዉ ህዝቦች በህይወት ለመኖር መብታቸዉ የሚያደርጉትን ትግል ለማስቀረት አቅም የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ የነገሩን ደርዝ ላለመሳት የሚጠቅመዉ ነገር ዘር ማጥፋቱን ያመጣዉን ግዙፍ ፖለቲካዊ አላማ(Grand Political Objective) ምንነት መመርመር ነዉ፡፡ በኦሮሚያ(በተለይ ወለጋ) እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ አማሮች በማንነታቸዉ ተለይተዉ ዘር ማጥፋት እንዲፈጸምባቸዉ ያደረገዉ ትልቁ የፖለቲካ አላማ (አማራን ጠላት ማድረግ) በሂደቱ ሰለባ ከሚሆኑ ሺናሻዎች ወይም ኦሮሞዎች ጋር የሚያገናኘዉ ነገር የለም፡፡ በሌላ አነጋገር የኦነግ ታጣቂ አማራን ጠላቴ ስለሆነ ከአካባቢዬ መጥፋት አለበት ብሎ፣የፖለቲካ አላማ ቀርጾ አማሮችን በየቤታቸዉ እየዞረ ሲገድል ባለዉ ሂደት(ምናልባትም ከአማራዉ ጋር ባላቸዉ ቁርኝት) የሌሎች ብሄር ተወላጆችን መግደሉ ኦነግ የተፈጠረዉ አማራ ጠላቴ ነዉ ከሚለዉ የፖለቲካ እሳቤ መሆኑን አይቀይረዉም፡፡

የኦነግ ታጣቂ ወይም የኦሮሞ ብልጽግና ልዩ ሃይል አማራን የዘር ማጥፋቱ ኢላማ/Target/ ሲያደርግ ከጀርባዉ ያዘለዉ አማራን ጠላት ብሎ የመፈረጅ እሳቤ ሽናሻዉን ወይም ኦሮሞዉን ሲገድልም የሚያስበዉ እሳቤ አይደለም። ለዘር ማጥፋት ወንጀል መከሰት ዋነኛ ምክንያት የሆነዉ የጠላት ምስል ፈጠራ ዉስጥ የሌሉ የሽናሻ፣ የኦሮሞ ወይም ሌላ ብሄረሰብ ተወላጆች ለዘር ማጥፋት ወንጀል የሚያጋልጣቸዉ ምንም ነገር የለም። ወይም በአማራዉ ላይ የተቃጣዉን የዘር ማጥፋት ወንጀል ተራ ግድያ ሊያደርገዉ አይችልም። ስለዚህ ለአማራ ጠሉ ስርዓት መመስረት፣መታጠቅ፣የዘር ማጥፋት መፈጸም ምክንያት በሆነዉ አማራ-ጠል የፖለቲካ እምነት ሳቢያ የዘር ማጥፋት ኢላማ/Target/ የሆነዉ የአማራ ህዝብ ሲሆን በዘር ማጥፋቱ ሂደት አልፎ አልፎ ህይወታቸዉን የሚያጡ የሌላ ብሄረሰብ ተወላጆች ደግሞ(victim) ናቸዉ፤ እንጂ የፖለቲካ ዓላማ ተይዞባቸዉ ለዓላማዉ መሳካት ደግሞ የዘር ማጥፋት ወንጀል እንደ ስልት(Strategy) የተያዘባቸዉ ህዝቦች አይደሉም። እዚህ ላይ መረሳት የሌለበት ቁም ነገር ዒላማ የተደረጉ አማሮችም ሆኑ ሰለባ የሚሆኑ ሌሎች ማህበረሰቦች ላይ የሚደርሰዉ በደል ዉጤት ደረጃ የሁለቱንም ብሄር ተወላጆች በህይወት የመኖር መብት የሚነጥቅ መሆኑ አይካድም። ሆኖም በሁለቱም ወገኖች ላይ የሚደርሰዉ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዲቆም የሚፈልግ አካል ደግሞ የሁለቱን ሁኔታ ለይቶ ነዉ ለመፍትሄዉ መሄድ ያለበት። አሁን መንግስት የያዘዉ በደፈናዉ "አማራ ብቻ አይደለም የሞተዉ ሌላዉም ሞቷል" የሚለዉ አካሄድ ዘር ማጥፋቱን ለማስቀጠል የሚደረግ ማምታቻ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም።

ነገሩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ከሃገራችን ወጣ ብለን ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን እንመልከት። በሩዋንዳ የተፈጸመዉ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ሲታቀድ ኢላማ(Target) ያደረገዉ ቱትሲዎችን ነበረ። ይህ ማለት ግን ከሁቱዎች ምንም የሞተ ሰዉ የለም ማለት አይደለም፤የሁቱዎች መሞትም በሩዋንዳ የተከናወነዉ የዘር ማጥፋት ቱትሲዎችን ኢላማ አድርጎ የተነሳ የመሆኑን ሃቅ አይቀይረዉም። በሩዋንዳ በተደረገዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ቱትሲዎች ኢላማ (Target) ሲሆኑ ለዘብተኛ ሁቱዎች ደግሞ (Victim) ነበሩ። እዚህ ላይ ልብ መባል ያለበት የዘር ማጥፋቱን እቅድ ያወጡት ሁቱዎች አምሳያ ብሄር (Co-ethnic) የሆኑት ሁቱዎች ይገደሉ የነበረዉ ከቱትሲዎች ጋር በነበራቸዉ በጎ መስተጋብር ምክንያት ነበር።

እነዚህ ሁቱዎች ከቱትሲዎች ጋር የነበራቸዉን ግንኙነት ወደ አሉታዊ መልክ ቀይረዉ በዘር ማጥፋቱ ቢተባበሩ ኖሮ በህይወት የመኖር ተስፋቸዉ መቶ ፐርሰንት ነበር፡፡ዘር ማጥፋቱ ኢላማ ያደረጋቸዉ ቱትሲዎች ግን እጣፋንታቸዉ አሰቃቂ ሞት ብቻ ነበር፡፡ ኢላማ መሆን እና ሰለባ መሆን ትልቁ ልዩነቱ ይህ ነዉ፡፡

ሌላ ተጨማሪ ዓለም አቀፍ ጉዳይ ለማንሳት ያህል ዓለማችንን እያመሰ ያለዉ ሃይማኖት ቀመስ ሽብርተኝነት በዋነኝነት ዒላማ ያደረገዉ እስራኤል እና አሜሪካን ሲሆን ምዕራባዉያን የሚባሉ ሃገራትን በአጠቃላይ ነዉ፡፡ የጸረ-ምዕራባዊነትን ግዙፍ አላማ(Grand Objective) ይዞ ሲንቀሳቀስ ኬንያና ኡጋንዳ እንደ ድርጊቱ ማስፈጸሚያ መቼት የተጠቀመበት ወቅት ተከስቷል፡፡ በዚህ ሁኔታ በጣት የሚቆጠሩ እስራኤላዉያንን ወይም አሜሪካዉያንን ለመግደል ሲል በርካታ ኬንያዉያን/ኡጋንዳዉያን የሚሰበሰቡባቸዉን የእግር ኳስ መመልከቻ ቤቶች፣ሞሎች፣መዝናኛዎች ላይ ቦምብ ተጥለዉ በርካታ የሃገሬዉ ሰዎች ሲያልቁ ኢላማ/Target/ የተደረጉት ምዕራባዉን ቁጥር ከአንድ እጅ ጣት አይበልጡም፡፡ በዚህ ሁኔታ በተለይ ኬንያ ሰለባ የምትሆነዉ ከቀዝቃዛዉ ጦርነት ጀምሮ ለምዕራባዉያን እና ለእስራኤል (የኢንቴቤዉን ኦፕሬሽን ተባብራለች) ካላት ወዳጃዊ ትስስር የተነሳ ነዉ እንጂ በራሷ ጠላት ተደርጋ ስለተቀመጠች አይደለም፡፡

የሆነዉ ሆኖ በኬንያ/ኡጋንዳ ፍንዳታ ከምዕራባዊዉም ከአገሬዉም ወገን የሞቱት ሰዎች ሰዉ በመሆናቸዉ ሃዘኑ ለሁሉም እኩል መሆን አለበት፡፡ ሆኖም ችግሩን ለመፍታት የተነሳ አካል ግን የሁለቱን ወገኖች አሟሟት ሁኔታ፣መንስኤ፣ትልቅ ምስል ለያይቶ መመልከት ግድ ይለዋል፡፡ ነገር ግን "ሁለቱም ሰዉ ናቸዉ፣ሁለቱም ሞተዋል፣የተለየ ነገር መታየት የለበትም " የሚል ማደናቆሪያ ማምጣት ከመፍትሄ ተፋትቶ ከችግር ጋር ለመኖር መማል ነዉ፡፡ በተመሳሳይ ከተወሰነ ዓመታት በፊት ሶማልያ ሪፐብሊክ ዉስጥ በሽግግር መንግስት ቁጥጥር ስር ባለ ዩኒቨርሲቲ ተምረዉ በህክምና ዶክትሬት ሊመረቁ ከቤተሰቦቻቸዉ ጋር አዳራሽ ዉስጥ በከተሙ ተመራቂዎች/ቤተሰቦቻቸዉ ላይ የአጥፍቶ ጠፊ ቦምብ ፈንድቶ 22 የሚሆኑ ተመራቂዎች አልቀዋል ፡፡ ይህን ያደረገዉ አሸባሪ ጠቡ ከምዕራባዉያን እና የፖለቲካ ዘይቤያቸዉ እንጂ ከእነዚህ ተመራቂዎች አልነበረም፡፡

በመሃል ቤት ሰለባ የሆኑ ተመራቂዎች ጉዳት በሽግግር መንግስቱ በኩል አልፎ አሜሪካን ለማስደንገጥ/ለማስበርገግ ነበር። በወቅቱ አሜሪካ በሶማሊያ የሽግግር መንግስት አቋቁማ አልሸባብን ዋሻ ለማሳጣት እየደከመች ነበረና በንጹሃን ተማሪዎች ደም አልሸባብ ማስተላለፍ የፈለገዉ የሽግግር መንግስቱን ደካማ ነዉ የሚል መልዕክት ነበር። ከላይ የተጠቀሱ ዓለም አቀፍ ምሳሌዎችን ማንሳት ያስፈለገዉ በሃገራችን የአማራ ህዝብን ሞት ለማቃለል "አማራ ብቻ አልሞተም" የሚለዉን ባዶ ማደናቆሪያ ጩኸት ከንቱነት በተሻለ መንገድ ለማስረዳት ያህል ነዉ።

በአማራ ህዝብ ላይ የተደለቀዉ የእልቂት ነጋሪት እንዲህ ባሉ ጥቃቅን ማደናቆሪያዎች የሚጥፋፉ አይደለም።የሚያዋጣዉ እዉነታን ተቀብሎ የመፍትሄዉን መንገድ መሻት ነዉ። ካልሆነ እንደተራራ ገዝፎ የሚታየዉን ሃቅ በእራፊ የሃሰት ጨርቅ ለመጋረድ መሞከር የአማራ ህዝብ ይበልጥ ተስፋ እንዲቆርጥ ከማድረግ ዉጭ የሚፈይደዉ ነገር የለም። የአማራ ህዝብ በህይወት የመኖር መብቱን ለማስከበር ከብዙ ትዕግስት በኋላ እያደረገ ያለዉን ፍትሃዊ ትግል ህገ-መንግሰታዊ ስርዓትን ለማፍረስ የታለመ የጦረኝነት አባዜ አድረጎ ማቅረብም ከችግር ጋር ተጋብቶ ለመኖር መወሰን ነዉ። በህገ-መንግስቱ የሰፈሩ ሰብአዊ መብቶች ቁንጮ የሆነዉ በህይወት የመኖር መብት አክብሮ ማስከበር ያልቻለ/ያልፈለገ/ መንግስት ስለ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት የሚያወራበት አፍ የለዉም።ህገ-መንግሰት የሚከበርዉ በህዝብ ብቻ ሳይሆን በመንግሰትም ጭምር ነዉ።ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ለመባል መንግስትን ራሱን የመሰረተዉን ህገ-መንግስት ማክበር ያስፈልጋል።ህገ-መንግስቱን አክብሮ፣በየቀኑ በማንነቱ ሲያልቅ የኖረን ህዝብ ማዳን ያልቻለ/ያልፈለገ/ መንግሰት ህገ-መንግስታዊ ነኝ ቢል የቁራ ጩኸት ነዉ የሚሆነዉ። ከእልቂት ያላዳኑትን ህዝብ "ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ስለሆንኩ ተገዛልኝ" ማለት ኢ-ሰብአዊ ሆኜ ስገድል እና ሳስገድልህ ህገ-መንግስታዊ ሆነህ በዝምታ ሙትልኝ ማለት ነዉ:: እንዲህ ባለ ዉል ተስማምቶ የሚገዛ ህዝብ ደግሞ አይኖርም።

## 2 የኢኮኖሚ ህልዉና አደጋ

በህይወት የመኖር መብቱን በአማራ-ጠሉ ስርዓት የተነጠቀዉ የአማራ ህዝብ ተዘዋዉሮ ሰርቶ፣ንብረት የማፍራት ሰብዓዊ/ህገመንግሰታዊ መብቱንም አጥቷል።

ተዘዋዉሮ ሰርቶ ንብረት የማፍራት መብቱን የመነጠቁ ነገር በአመዛኙ በህይወት የመኖር መብቱን ከመነጠቁ ጋር የሚመጋገብ ነዉ። ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በሃገሩ የትም ቦታ ተዘዋዉሮ የመስራትና ንብረት የማፍራት መብት እንዳለዉ በስራ ላይ ያለዉ ህገመንግስት ይደነግጋል። በተግባር የሚታየዉ ግን ተቃራኒ ነዉ። በተለይ የአማራ ህዝብ ተዘዋዉሮ መስራቱም፣ሰርቶ ባገኘዉ ንብረት ተጠቃሚ የመሆን መብቱም አደጋ ዉስጥ የወደቀ ህዝብ ነዉ። ይህን በማድረጉ ረገድ የአማራ-ጠሉ መንግስት ሚና በቀጥታ ከመሳተፍ የአማራዉን ንብረት ለሚያወድሙ የብሄር ፖለቲካዉ ወንበዴዎች ተገን እስከመስጠት የሚደርስ ነዉ። በዚህ መንግስታዊ ድጋፍ ባለዉ የዉንብድና ተግባር ሳቢያ ከአማራ ክልል ዉጭ የሚኖሩ አማሮች በሚያፈሩት ንብረት የመጠቀም መብት የላቸዉም። በቡድን የሚንቀሳቀሱ የብሄር ፖለቲካዉ ነፍሰ ገዳይ ደጋፊዎች በአማራዉ ህዝብ ላይ የሚፈፅሙት የግፍ ዉድመት መነሻዉ ሊተነበይ የማይችል፣የድንገቴ እና ብዙ ቁጥር ባላቸዉ የታጠቁና ያልታጠቁ ቡድኖች የሚፈጽም መሆኑ፣የመንግስት ግልጽ እና ስዉር ድጋፍ ያለዉ መሆኑ ሲታከልበት ችግሩን እጅግ ከባድ ያደርገዋል።

አማራ-ጠሉ ስርዓት የሚፈጽመዉ አማራዉ በሃገሩ ኢኮኖሚ ላይ ህልዉናዉ እንዲቀንስ/እንዲጠፋ የማድረጉ እርምጃ በአማራ አርሶ-አደር፣የመንግስት ቢሮ ስራ ዉስጥ ተቀጥሮ በሚሰራዉ፣በነጋዴዉ፣በስራ ፈጣሪዉ፣በስራ ፈላጊዉ ላይ ሁሉ የሚፈፅም ነዉ። ከአማራዉ አርሶ አደር ብንጀምር ከአማራ ክልል ዉጭ የሚኖረዉ አርሶ አደር ህይወቱንም ንብረቱንም ተነጥቆ ነፍጠኛ፣ወራሪ፣ጨቋኝ፣ሰፋሪ የሚሉ የዘር ማጥፋት ታርጋዎች (Genocidal Code) ተለጥፈዉበት ማንነቱን ኢላማ ያደረገ ግድያ እና መፈናቀል ይደርስበታል። ይህ ሲሆን ደግሞ የሞተዉም የተፈናቀለዉም አማራ ጥሮ ግሮ ያፈራዉ ሃብቱ ይወድማል፣ቤቱ ይቃጠላል፣ለዘር ያስቀመጠዉ እህል ሳይቀር ይዘረፋል/ይቃጠላል። ይህ ሁሉ የሚሆነዉ የተፈናቀለዉ አማራ ቤት ንብረት አለኝ ብሎ ወደ አካባቢዉ ለመመለስ ተስፋ እንዳያደርግ ነዉ። መንግስት ለዜጎቹ እንዲህ ካለ አስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት ከለላ መስጠት ሲገባዉ ራሱ በታችኛዉ መዋቅር የሚሳተፍበት ግልጽ የሰብኣዊ መብት ጥሰት ሲፈፀም ኖሯል። ጠያቂም ተጠያቂም ሳይኖር ዘመናት አልፈዋል። ይህ ሁሉ ግፍ የተፈጸመበት የአማራ ህዝብ ከዘር መጥፋቱ አደጋ የመትረፍ እድል ካገኘ ማንም ዞሮ ወደማያየዉ የስደተኛ ጣቢያ ገብቶ ከልመና የማይሻል ኑሮ ይኖራል።

እንደ አርሶ አደሩ ሁሉ ነጋዴዉ አማራም በሚኖርበት አካባቢ በሚነሱ ድንገተኛ ሁከቶች( ለምሳሌ የሃጫሉ ሁንዴሳ ሞት፣ የአቶ ጃዋር ተከበብኩ ጥሪ ወዘተ) ንብረቱ ተለይቶ ዒላማ መደረጉና መወደሙ የቅርብ ጊዜ እዉነት ነዉ። የአማራዉን ንብረት ማዉደም እና ማቃጠል እንደ ታጋይነት ይቆጠራል እንጂ እንደ ወንጀል አስጠይቆ አያዉቅም። ከአማራ ክልል ዉጭ በሚኖረዉ የአማራ ህዝብ ላይ የሚደረገዉ ንብረት የማፍራት መብቱን በማንኛዉም ሰዓት የመግፈፍ ወንጀል በአማራ-ጠሉ መንግስት መዋቅር ታስቦበት በግልፅ የሚደረግ ነዉ። ለዚህም የቅርብ ጊዜ ማሳያ የሚሆነዉ ክስተት የሸገር ከተማን መፍጠር በሚለዉ የኦሮሚያ ክልል መንግስት ዘረኛ ፕሮጀክት ሰዎች በማንነታቸዉ ተለይተዉ በማታ ጨቅላ ልጆቻቸዉን ይዘዉ በተኙበት ሁኔታ ሳይቀር ቤት ንብረታቸዉ በዶዘር እንዲፈርስ መደረጉ ነዉ። ይህን ያደረጉ የኦሮሚያ ክልል ባለስልጣናት በመገናኛ ብዙሃን ቀርበዉ ስለ ጉዳዩ ሲጠየቁ ስለድርጊታቸዉ "ተገቢነት" ያስረዱ ነበር። በዚህ የፋሽስታዊ የዘረኝነት ተግባር ኦሮሞ ያልሆኑ ኢትዮጵያዉያን ተለይተዉ በግልጽ መንግስታዊ የሰብአዊ መብት ጥሰት ቤት ንብረታቸዉን ያጡ መሆኑ አይካድም። ይህን መንግስታዊ ወንጀል ስርዓቱ የአማራን ህዝብ ከሃገሪቱ ዋና ከተማና አካባቢዉ የኢኮኖሚ ህልዉና ለመንቀል ከሚያደርገዉ በአጠቃላይ ሴራ የሚመነጭ እርምጃ ነዉ።

በአዲስ አበባ ከተማ በባጃጅ ትራንስፖርት ስራ ላይ የተሰማሩ የአማራ ተወላጆችን ከጨዋታ ዉጭ ለማድረግ በተደጋጋሚ የሚደረገዉ የመንግስት እርምጃ አማራን ከዋና ከተሞች የኢኮኖሚ ህልዉና የማስወገድ ዘረኛ ፖሊሲ አካል ነዉ። ከጎንደር-ባህርዳር-ደጀን-አ.አ- በሚወስደዉ መንገድ ከባድ መኪና የሚያሽከረክሩ የአማራ ተወላጅ ሹፌሮች ኦሮሚያ ክልል ሲገቡ በጥይት ተደብድበዉ ተገድለዉ መኪናቸዉ እንዲቃጠል ሲደረግ አራት አመታት አስቆጥሯል። ለዚህ ከባድ ወንጀል የኦሮሞ ብልፅግና ፓርቲ መኳንንት የሚሰጡት መልስ ክህደት አልያም መሳለቅ ነበር። የግብርና ዉጤቶች ከአማራ ክልል ወደ አዲስ አበባ እንዳይገቡ ስዉርና ግልጽ የማገድ እርምጃዎች ያለ ሃፍረት በመንግስት ይደረጋሉ። ይህ የሚሆነዉ የአማራ አርሶ አደር በተሻለ ዋጋ ምርቱን የሚሸጥበትን እድል በማሳጣት ኢኮኖሚያዊ አቅሙን ለማድቀቅ ነዉ። በተመሳሳይ በአዲስ አበባ የሚገኙ የግል ትምህርት ቤቶች ከ70% በላይ በአማራ ባለሃብቶች የተቋቋሙ መሆናቸዉን ዘረኛዉ የኦሮሞ ብልፅግና መንግስት አስጠንቼ ደርሼበታለሁ በማለት እነዚህን ባለሃብቶች የእኔ በሚለዉ ብሄር ባለሃብቶች ለመተካት እየተራወጠ እንደሚገኝ የማያጠራጥር መረጃ ደርሶኛል። ይህ ሁሉ የአማራዉን የኢኮኖሚ ህልዉና ለማጥፋት የሚደረግ አሳፋሪ ዘረኝነት ነዉ።

አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራውን ኢኮኖሚያዊ ህልዉና አዳክሞ ሊያጠፋበት የሚሰራበት ሌላዉ መንገድ በመንግስት ቢሮክራሲ ዉስጥ ያሉ የአማራ ተወላጆችን በሰበብ አስባቡ ማስወገድ ነዉ። አማራ-ጠሉ ስርዓት ስልጣን እንደያዘ የአማራ ብሄር ተወላጅ የሆኑ ከአርባ በላይ የሚሆኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምርጥ ምሁራን ከስራ አባሯል። ይህ የሆነዉ አማራ-ጠሉን ስርዓት ህወሃት በሚመራበት ወቅት ነበር። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በህወሃት ትዕዛዝ የተባረሩት ምሁራን የመባረራቸዉ ምክንያት በህወሃት ማኒፌስቶ ጠላት ተብሎ በተፈረጀዉ የአማራ ብሄር መወለዳቸዉ ነበር። ለዚህ ማረጋገጫዉ አቶ መለስ ዜናዊ በ1994 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ማህበረሰብ ጋር ባደረጉት ዉይይት የተናገሯቸዉ ንግግሮች ናቸዉ። አቶ መለስ በዚህ ንግግራቸዉ ፓርቲያቸዉ በዩኒቨርሲቲዉ ላይ የወሰዳቸዉ እርምጃዎች ያነጣጠሩት በዩኒቨርሲቲዉ የበላይነት ይዞ በተቀመጠዉ "የትምክህተኞች መዋቅር" ላይ እንደሆነ፣ይህ መዋቅር ደግሞ ሁል ጊዜ በሃገሪቱ ዉስጥ የሚካሄደዉን የዲሞክራሲ ሂደት እየተቃወመ የሚኖር መሆኑን ገልጸዋል። ሰዉየዉ አክለዉም ፓርቲያቸዉ የወሰደዉ እርምጃ ዩኒቨርሲቲዉን በመአህድ ከመዋጥ የታደገ እንደሆነ በተለመደዉ አሽሙራቸዉ ተናግረዋል። (ብርሃኑ ደቦጭ፣ ገጽ 38)[2]

በዚሁ ስብሰባ በዩኒቨርሲቲዉ ዉስጥ የአማራ የበላይነት እንዳለ በዶ/ር ገመቹ መገርሳ በኩል በግልጽ ተነግሮ ነበር። ዶ/ር አማረ አስገዶም የተባሉ አፍቃሬ ህወሀት የዩኒቨርሲቲዉ መምህር ደግሞ የአቶ መለስን አማራ-ጠል አቋም በሚያጠናክር መንገድ በዩኒቨርሲቲ ዉስጥ የጨቋኝ ተጨቋኝ ግንኙነት ስር ሰዶ እንደኖረ የሚያትት የመመረቂያ ጽሁፍ ጽፈዋል።(ብርሃኑ ደቦጭ፣ ገጽ 68-72)[3] በዩኒቨርስቲ ዉስጥ አለ ያሉት የጨቋኝ ተጨቋኝ ግንኙነት በብሄር ላይ የተመሰረተ ነዉ ባይ ናቸዉ አማረ አስገዶም። በብሄር ላይ የተመሰረተ የጨቋኝ ተጨቋኝ ግንኙነት አለ ሲባል ደግሞ የጨቋኝነቱ መርገም የሚወረወረዉ በመከረኛዉ የአማራ ብሄር ላይ እንደሆነ የህወሃት ማኒፌስቶ በግልጽ፣ የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ደግሞ በስዉር ያስቀመጡት ማንንም የማያደናግር ግልጽ ነገር ነዉ።

[2] ብርሀኑ ደቦጭ፣ የድንቁርና ጌቶች፣ ሞገሱን የገፈፉት ዩኒቨርሲቲ (ከ1983 — 2012 ዓ.ም) አዲስ አበባ፣ 2012 ዓ.ም

[3] ብርሀኑ ደቦጭ፣ የድንቁርና ጌቶች፣ ሞገሱን የገፈፉት ዩኒቨርሲቲ (ከ1983 — 2012 ዓ.ም) አዲስ አበባ፣ 2012 ዓ.ም

የተባረሩት ከተባረሩ በኋላ የቀሩት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አማራ ምሁራን ደግሞ በዩኒቨርሲቲዉ አንገታቸዉን ደፍተዉ ከማስተማር በቀር ወደ ዩኒቨርሲቲዉ የመሪነት ወንበር ዝር እንዳይሉ አማራነታቸዉ በቂ ወንጀል ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡ በ1993ዓ.ም በተደረገዉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ምርጫ በዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብ በተደረገ ምርጫ ከአምስት የመጨረሻ ተወዳዳሪዎች በሁለተኝነት ተመርጠዉ የነበሩት ፕ/ሮ ደምሴ ሃብቴ ለትምህርት ሚኒስቴር ከሚላኩት ሶስት ተወዳዳሪዎች ዉስጥ እንዳይገቡ የዩኒቨርሲቲዉ ቦርድ ቀንሷቸዉ ነበር፡፡ የተቀነሱበት ምክንያት "አማራ ከበቂ በላይ መርቷል " በሚል ምክንያት ነበር፡፡ በዚህ ምርጫ በስተመጨረሻዉ በትምህርት ሚኒስቴር የተመረጡት ፕ/ር እሸቱ ወንጨቆ በዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብ የተሰጣቸዉ ድምጽ በአምስተኝነት ደረጃ ያስቀመጣቸዉ ነበሩ፡፡ በአንደኛነት ተመርጠዉ የነበሩት እዉቁ የታሪክ ምሁር ፕ/ር ባህሩ ዘዉዴ ቢሆኑም የትምህርት ሚኒስትሯ ወ/ሮ ገነት ዘዉዴ ቀልብ ስላልወደዳቸዉ የዩኒቨርሲቲዉ ፕሬዝዳንት ሳይሆኑ ቀርተዋል(የድንቁርና ጌቶች፣ብርሃኑ ደቦጭ ገጽ 58-59)[4]

በእነዚህ ምርጥ ምሁራን የተጀመረዉ የአማራ ተወላጆችን ከሲቪል ቢሮክራሲዉ የመንቀል ፋሽስታዊ ወንጀል በሌሎች የሲቪል እና ወታደራዊ መስሪያ ቤቶች ተቀጥረዉ በሚሰሩ የአማራ ብሄር ተወላጆች ላይም በማንአለብኝነት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ በሲቪል እና ወታደራዊ ተቋማት የሚሰሩ አማሮችን ጠራርጎ የማስወገዱ የዘረኝነት ወንጀል ምክንያቱ የብቃት ማነስ ነዉ፡፡ ከብቃት ማነሰ በተጨማሪ የአማራ ተወላጆችን ማስወገጃዉ መንገድ እድሜአቸዉ ሳይደርስ በጡረታ የማግለል እብሪት ነክ አርምጃ ነዉ፡፡ ይሄኛዉ ዘዴ በተለይ የአማራ የጦር መኮንኖችን ከስራ አፈናቅሎ ጦሩን ሃገሩን በሚገዙ መሪዎች ብሄር ተወላጆች ለመሙላት ሲሆን እግረ መንገዱንም የአማራ የጦር መኳንንትን ከስራ አባሮ በኢኮኖሚ ጉስቁልና ዉስጥ የመክተት ሌላ ግብ ያለዉ ነዉ፡፡

አማራዉን ከሲቪል እና ወታደራዊ የስራ መደቦች የመጥረጉ እርምጃ ኢትዮጵያ በአማራ ምስል ተሰርታለችና አማራ በኢትዮጵያ ሁለንተና ዉስጥ ጉልህ ህልዉና አለዉ፤ይህም መሆን የሌለበት ነገር ነዉ ከሚለዉ የአማራ-ጠሉ የፖለቲካ ጎራ መሰረታዊ የፖለቲካ እምነት የመነጨ ነዉ፡፡

---

[4] ብርሀኑ ደቦጭ፣ የድንቁርና ጌቶች፣ ሞገሱን የገፈፉት ዩኒቨርሲቲ (ከ1983 — 2012 ዓ.ም) አዲስ አበባ፣ 2012 ዓ.ም

የአማራ-ጠሉ ስርዓት የምሁራን ክንፍ ይህን ሃሳብ በግልጽ በተለያዩ በሚዲያዎች የሚናገሩት ነዉ። “ኢትዮጵያ አማራን እንዳትመስል ማድረግ አለብኝ” ብሎ የሚያስበዉ አማራ-ጠሉ ስርዓት ይህን ለማድረግ ይረዱኛል ብሎ ከሚያስባቸዉ ስልቶች አንደኛዉ አማራዉን ከሲቪል ብሮክራሲዉ ጠራርጎ ህልዉናዉን ማዳከምና ማጥፋት ነዉ። ይህን አካሄድ ለመንግስታቸዉ በግልጽ ሲመክሩ የኖሩት የአማራ-ጠሉ መንግስት ደጋፊ የብሄር ፖለቲካ አፍቃሪ ምሁራን ናቸዉ። በዚህ አንጻር የኦሮሞ ምሁራን የመጀመሪያዉን ድርሻ ይወስዳሉ። መንግስታቸዉም ይህን ተቀብሎ ከህወሃት መሪነት ጀምሮ እስከ ኦነጋዊዉ የብልጽግና መንግሰት ድረስ እየተገበረዉ ይገኛል፡፡ በቅርቡ ጠ/ሚሩ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ዉስጥ የአማራ ተወላጅ የሆኑ ሰራተኞች ከ ግማሽ በላይ የሚሆነዉን ፐርሰንት እንደሚይዙ መናገራቸዉ አማራ-ጠሉ ስርዓት ከህወሃት ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን አማራዉን ከኢኮኖሚያዊ ህልዉናዉ ለመንቀል ያለዉን የማይናወጥ አቋም የሚያመለክት ነዉ።

የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የአማራ ባለሀብቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅም የማዳከሙ ተግባር በአማራ-ጠሉ ስርዓት በጥብቅ የሚሰራበት እርምጃ ነዉ። በተለይ ከአማራ ክልል ዉጭ ኢንቨስት የሚያደርጉ የአማራ ባለሃብቶች በርካታ ተግዳሮቶች እንዳሉባቸዉ ይታወቃል፡፡ የአማራ ባለሃብቶችን ከሚገጥማቸዉ ተግዳሮቶች መካከል የብድር አገልግሎት መነፈግ፣ለልማት በሚል ሰበብ የተጋነነ መጠን ያለዉ መዋጮ እንዲያዋጡ ማስገደድ፣ሰበብ ፈልጎ እስር ቤት ማስገባት ወዘተ ሲሆኑ በጥቃቅን የንግድ ስራዎች ላይ የተሰማሩ ታዳጊ የአማራ ነጋዴዎችን ደግሞ የንግድ ፈቃድ ባለማደስ፣መታወቂያ በመከልከል የእድገት ጉዞአቸዉ በመንግስታዊ የዘረኝነት ወንጀል እንደሚገታ የአደባባይ ሃቅ ነዉ። ይህ አማራዉን ከኢኮኖሚ ህልዉና የማስወገዱ መንግስታዊ እርምጃ በዚህ ብቻ የሚየበቃ ስላለሆነ ሰፋ ያለ ጥናት ሊደረግበት የሚገባ መስክ ነዉ።

በሃገራችን ብሄር ተኮር ባንኮችን ማቋቋም ችግር የሌለበት ነገር ሆኖ በሃገራችን ሲሰራበት የኖረ ፈለግ ነዉ። ይህ እየታወቀ በቅርቡ የአማራ ባንክ ሲቋቋም በአማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራ ጋሻ አጃግሬዎች አንደበት ሲወገዝ ተሰምቷል፡፡ ይህን ዉግዘት በአደባባይ የተናገሩት በወቅቱ የብሄራዊ ባንክ ገዥ የነበሩት በዉልደት አማራ የሆኑት ዶ/ር ይናገር ደሴ ናቸዉ።

ሰዉየዉ የአማራ ባንክን መከፈት አስመልክቶ ንግግር እንዲያደርጉ ሲጋበዙ በብሄር ባንክ ማቋቋም ጥሩ እንዳልሆነ ሊያስረዱ ሞክረዉ ራሳቸዉን ትዝብት ዉስጥ ጥለዋል። ከዶ/ር ይናገር ንግግር መረዳት የሚቻለዉ አማራዉ በኢኮኖሚ እንዳይደራጅ በአማራ-ጠሉ ስርዓት ዘንድ ሃፍረት የለሽ ጠንካራ አቋም መኖሩን ነዉ። የዚህ ሁሉ እርምጃ የመጨረሻ ግብ አማራዉ በኢኮኖሚ በማድቀቅ በሃገሩ ላይ ጉልህ ኢኮኖሚያዊ ህልዉና እንዳይኖረዉ ማድረግ ነዉ።

## 3-የባህል ህልዉና

ባህል የሚለዉ ፅንሰ ሃሳብ በአካዳሚዉ ዓለም በርካታ ትርጓሜዎች የሚሰጡት ቢሆንም ባህል ማለት የሰዉ ልጅ ከተወለደ በኋላ የሚማራቸዉን ልምዶች ሁሉ የሚያጠቃልል ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ ነዉ የሚለዉ ትርጉም በዚህ ሰነድ ሁኔታ የተሻለ ትርጉም ሆኖ ተወስዷል። የሰዉ ልጅ ባህልን ከተማረ በኋላ ለሌሎች ማህበረሰቦች የሚያጋራዉ፣ የሚያሳድገዉ፣ አንዳንዴም የሚተወዉ/የሚለዉጠዉ እንደሆነ መዛግብት ያስረዳሉ። በዚህ ብያኔ መሰረት ባህል በመጀመሪያ በየትኛዉ ማህበረሰብ እንደተፈጠረ ለማወቅ አዳጋች ነዉ ማለት ነዉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች የአንድ ማህበረሰብ ነዉ ተብሎ የተበየነ ባህል በታሪክ መዛግብት ወደ ኋላ ተሂዶ ሲጣራ ባለቤት ከተባለዉ ህዝብ በፊት በሌላ ማህበረሰብ ዘንድ የተዘወተረ ሊሆን ይችላል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነዉ በአሁኑ ወቅት የምዕራባዉያን ባህል ተደርገዉ የሚቆጠሩት የሳይንስ፣ የሒሳብ፣ የአስትሮኖሚ ትምህርቶች ከምዕራቡ ዓለም ቀደም ብለዉ በዓረቡ አለም ተዘዉትረዉ ወደ ምዕራቡ አለም ከጊዜ በኋላ የተሻገሩ እንደሆኑ ማስረጃ አለዉ። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት እነዚህ ትምህርቶች የምዕራባዉያን ተብለዉ፣እነርሱን መማር ሃራም(የተከለከለ) ነዉ የሚል እሳቤ ከራሱ ከአረቡ አለም ተነስቶ፣እሳቤዉ አድጎ ዓለምን ያሳሰበዉን ሃይማኖት ቀመስ አሸባሪነት ወልዷል።

ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ አንድ ባህልን ማን እንደጀመረዉ ለማወቅ ቢያስቸግርም ባህሉ በሰፊዉ ህዝብ ህይወት ዉስጥ የገዘፈ፣ የተዘወተረና፣ ስር የሰደደ ከሆነ የዚያ ህዝብ ባህል ተደርጎ እንደሚወሰድ ነዉ። የአማራ ህዝብም እንደማንኛዉም የሰዉ ልጅ ባህልን የሚማር፣ የሚጋራ/የሚያጋራ፣ የሚያሳድግ፣ የሚለዉጥና የሚተዉ ቢሆንም በማህበረሰቡ ህይወት ዉስጥ የገዘፈ ቦታ ያላቸዉ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ባህሎች አሉት።

እነዚህ ባህሎች ባህልን መጋራት በሚለዉ መርህ መሰረት ሌሎች የኢትዮጵያ ብሄሮችም የሚጋሯቸዉ ቢሆኑም በርካታ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ የሃገራችን ቅርሶች በአማራ-ጠሉ አገዛዝ የአማራ ተብለዉ ተፈርጀዉ ለውድመት ተዳርገዋል፡፡ በእዚህ እሳቤ ሳቢያ በአዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ የሚገኙ በርካታ የሚዳሰሱ ቅርሶች ህዝብ እያዬ ፈርሰዋል፡፡ ቅርሶቹ በብሄራዊ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን የተመዘገቡ ቢሆኑም ከዉድመት ሊተርፉ አልቻሉም፡፡

የኦሮሞ ብልጽግና መራሹ መንግስት አዲስ አበባ የሚገኙ ጥንታዊ ቅርሶችን በፍጥነት እያወደመ የሚገኘዉ ትልቅ የፖለቲካ ምክንያት ስላለዉ ነዉ፡፡ ይኸዉም እነዚህ ቅርሶች "አዲስ አበባ የኦሮሞ ነች" የሚለዉን የኦሮሞ ፖለቲከኞች ከሃቅ የተጣላ ክርክር በእጅጉ የሚያፈርሱ ታሪካዊ ማስረጃዎችን ስለያዙ ነዉ፡፡  ቅርሶቹ በዉስጣቸዉ የያዟቸዉ ተጨባጭ ታሪካዊ ማስረጃዎች አማራ-ጠሉ ስርዓት "የአማራ ናቸዉ" ሲል የፈረጃቸዉን ባህላዊ ሃቆችን ነዉ፡፡ በመሆኑም አዲስ አበባ የአንድ ብሄር ትሁን ከተባለ የኦሮሞ ከመሆን ይልቅ የአማራ መሆኗን ቅርሶቹ ሊመሰክሩ ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ በኦሮሞ ብልጽግና ዘንድ በእጅጉ የማይፈለግ ነገር ነዉ፡፡ ስለዚህ ለምስክርነት የቆሙ ቅርሶችን ማዉደሙ ስልጣን የሰጣቸዉ ቀላል አማራጭ ነዉ፡፡

ከአዲስ አበባ ወጣ ስንል በሃረር ከተማ ለዘመናት ቆሞ የኖረዉ የራስ መኮንን ሃዉልት እንደዋዛ ፈርሶ ቀርቷል፡፡ ራስ መኮንን በአድዋ ጦርነት የሚያኮራ ጀብዱ ያስመዘገቡ ጀግና አርበኛ ነበሩ፡፡ ሆኖም በአማራ-ጠሉ ስርዓት እይታ ራስ መኮንን አማራ በመሆናቸዉ የኦሮሞ/የአደሬ ከተማ ተደርጋ የተበየነችዉ ሃረር ከተማ መሃል ሃዉልታቸዉ መቆሙ ትልቅ ችግር ነዉ፡፡ ሃዉልቱን መንግስት አላፈረሰዉም የሚል የየዋህ መሳይ ክርክር የሚነሳ ከሆነ መንግስት ባለበት ከተማ የሃገር ባለዉለታ ጀግና ሃዉልትን ገንድሶ መጣል የተቻለዉ በመንግስት ዝምታ ዉስጥ የሚገለጽ መስማማት ስላለ ነዉ፡፡ በተጨማሪም መንግስት የሃወልቱን መፍረስ ባይደግፍ ኖሮ ድርጊቱን አዉግዞ ሃወልቱን መልሶ ሲያቆም መታየት ነበረበት፡፡

አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራ ያለዉን አሻራ ለማደብዘዝ/ለማጥፋት የሚወስደዉ እርምጃ ቅርሶችን ማፍረስ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቅስ ጉልህ ስራ የሰሩ ሰዎች አማራ እስከሆኑ ድርስ መታሰቢያ እንዳይቆምላቸዉ መከልከልም ጭምር ነዉ፡፡ በአፍሪካ ህብረት ግቢ ዉስጥ የክዋሚ ኒክሩማ ሃዉልት እንዲቆም የተደረገበት የአማራ-ጠሉ አገዛዝ ርብርቦሽ ለዚህ አይነተኛ ምልክት ነዉ፡፡

የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን ከጽንሰት ጀምሮ እስከዉልደት በከፍተኛ ትግል እዉን ያደረጉት አፄ ሃይለስላሴ ናቸዉ፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሰረት ምክንያት የሆነዉ ነገር ራሱ ሃወልቱ ለማን መቆም እንዳለበት አመላካች ነዉ፡፡ ድርጅቱ እንዲቋቋም የተፈለገበት ምክንያት የአፍሪካ ሃገሮች ድምጽ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዉስጥ እንዲሰማ እና ነጻ ያልወጡ የአፍሪካ ሃገራት ነጻ እንዲወጡ ለማስቻል ነበር፡፡ ይህን ለማሰብ ደግሞ የተባበሩት መንግስታትን ከመስራችነት ጀምራ ከአፍሪካ በብቸኝነት ወንበር የነበራት ሃገር ኢትዮጵያ ነች፡፡ አፍሪካዉያን ባለመኖራቸዉ የጎደለዉን ነገር ለመረዳትም ከኢትዮጵያ የሚቀድም የለም፡፡ አጼ ሃይለስላሴ ከታዋቂዉ ዲፕሎማት አቶ ከተማ ይፍሩ ምክር በመቀበል የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲቋቋም ሌት ተቀን የለፉ ናቸዉ፡፡ በዚሁ ምክንያት በአፍሪካዉያን በራሳቸዉ "የአፍሪካ አባት" የሚል ስም የተሰጣቸዉ ነበሩ፡፡

ኒክሩማ በአንጻሩ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን እዉን መሆን አደጋ ላይ ጥለዉ ከነበሩት ሁለቱ ቡድኖች የካዛ ብላንካዉ ቡድን ቀንደኛ ዘዋሪ ነበሩ፡፡ አጼ ሃይለስላሴ ግን የሁለቱ ቡድኖች መፈጠር ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት እዉን መሆን ደንቃራ እንደሆነ በአቶ ከተማ በኩል ተረድተዉ ከነበሩበት የሞኖሮቪያ ቡድን ወጥተዉ ገለልተኛ በመሆን ሁለቱን ቡድኖች አይሆኑ ሆነዉ አስታርቀዉ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን እዉን ያደረጉ መሪ ናቸዉ፡፡ ይህ ሁሉ ሃቅ እያለ የአማራ-ጠሉ ስርዓት የወቅቱ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ በአፍሪካ ህብረት ግቢ ዉስጥ መቆም ያለበት የክዋሚ ኒክሩማ ሃዉልት እንደሆነ ተከራክረዉ የፈለጉትን አደረጉ፡፡ የአቶ መለስ ጥብቅ ክርክር ኒክሩማን ከመዉደድ ይልቅ አማራ የተባሉትን ንጉስ አሻራ ለማየት ከመጥላት የመጣ እንደሆነ ታሪካዊ ሃቆች ምስክር ናቸዉ፡፡

የአጼ ምኒሊክን ሃዉልት ማፍረስም አማራ-ጠሉ ስርዓት ጮክ ብሎ የማይናገረዉ የዘወትር ምኞቱ ነዉ፡፡ ሃዉልታቸዉን ማፍረሱ እንዲህ በቀላሉ የማይሆን ስለሆነ የምኒሊክን ቤተ-መንግሰት ወደ አንድነት ፓርክ የመቀየሩ የረቀቀ አካሄድ ተመራጭ ሆኖ ተተግብሯል፡፡ ይህ ቤተ-መንግስት የአጼ ምኒሊክን ስም አስወግዶ አንድነት ፓርክ ሲባል ትልቅ ታሪካዊ አሻራ እየጠፋ ነዉ፡፡

የቤተ-መንግስቱ ወደ ፓርክነት መቀየር ደግሞ እስከዚህም የማንንም ቀልብ የሳበ ነገር ሊሆን አልቻለም። ይህ የኦሮሞ ብልጽግና እያደናገሩ ማሳሳት የፖለቲካ ስልት ቀመር ነዉ። ይህን ቅርስ የማጥፋት የአላዋቂ ጉዞ የታሪክ ምሁራን ጭምር የተሳተፉበት መሆኑ ነገሩን የበለጠ አሳዛኝ ያደርገዋል።

ከሚዳሰሱ ቅርሶች በተጨማሪ የአማራ ናቸዉ ተብለዉ የተፈረጁ የማይዳሰሱ ባህላዊ መገለጫዎችም የአማራ-ጠሉ ስርዓት የጥቃት ኢላማዎች ናቸዉ። ስርዓቱ የአማራ ናቸዉ ብሎ ከሚፈርጃቸዉ የማይዳሰሱ ቅርሶች የአማርኛ ቋንቋ፣የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት፣የሃገረ መንግስትን ቀጣይነት የመሻት ፖለቲካዊ ስነልቦና ዋነኞቹ ናቸዉ። አማርኛ ቋንቋ ሀገርን ከማስተሳሰር አንጻር በታሪክ የነበረዉን አቅሙን እንዲያጣ አማራ-ጠሉ ስርዓት በርካታ ስልቶችን ተጠቅሟል። ከአማራ ክልል ዉጭ ባሉት የሃገሪቱ ክልሎች አማርኛ ቋንቋን እንደ አንድ የትምህርት አይነት እንደሚሰጥ በፖሊሲ የተቀመጠ ቢሆንም በተለይ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርቱ በተገቢዉ መንገድ እንዳይሰጥ ይፋ ያልሆነ መግባባት ላይ የተደረሰ በሚመስል ሁኔታ ተማሪዎቹ አማርኛ ቋንቋን መናገርም መጻፍም የማይችሉ ሆነዉ ይገኛሉ። ለዉጥ የተባለዉ ነገር በመጣ ሰሞን ታዋቂዉ የኦሮሞ ፖለቲከኛ ጃዋር መሃመድ "በኦሮሚያ ክልል አማርኛ የሚያስተምሩ የግል ትምህርት ቤቶቹን ዝርዝር አሳዉቁኝ እና እርምጃ ይወሰድባቸዋል" የሚል መልዕክት በማህበራዊ ድህረ-ገጹ እስከማስተረላለፍ ደርሶ ነበር።

በሃገራችን ዩኒቨርሲቲዎች ዉስጥ የአማርኛ ቋንቋ በንዑስ የጥናት መስክ (minor) የሚሰጥበት ሁኔታ በጣም ቀንሷል። በአብይ ትምህርት (major) ቢሆንም የአማርኛ ቋንቋን የመስጠቱ ነገር ከጊዜ ወደ ጊዜ እተመናመነ ሄዷል። የአማርኛ ቋንቋ የሚጻፍባቸዉን ፊደላት ለሌሎች ብሄሮች ቋንቋ መጻፊያነት (ተገቢዉን ማስተካከያ ተደርጎ) ለማዋል ይቻል አይቻል በገለልተኛ ምሁራን ሳረጋገጥ በላቲን ፊደላት ለመጠቀም የተቸኮለዉ ችኮላ ስርዓቱ አማርኛ ቋንቋን ከሚያዳክምበት ስልቱ አንዱ ነዉ። አማርኛ ቋንቋን መናገር እየቻሉ አልችልም ማለት ለአማራ-ጠሉ ስርዓት እድምተኞች እንደምጡቅ ታጋይነት የሚወሰድ ነገር ነዉ። የዚህ ሁሉ ድምር ዉጤት አማርኛ ቋንቋን በእጅጉ እንዳዳከመዉ የማይካድ ሃቅ ነዉ። አቶ ሽመለስ አብዲሳ በአንድ ወቅት ሾልኮ በወጣዉ ንግግራቸዉ ኦሮምኛ ቋንቋን ከማሳደጉ ጎን ለጎን አማርኛ ቋንቋን የመግደል "ጀብዱ" እየሰሩ እንደሆነ ሲገልጹ በአድማጮቻቸዉ የሞቀ ጭብጨባ ታግዘዉ ነበር።

እንደ አማርኛ ቋንቋ ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስተያንም የአማራ-ጠሉ ስርዓት ኢላማ ነች፡፡ ቤተ-ክርስቲያኗ ከአማራዉ ባላነሰ በትግሬዉ ብሄር ዘንድ ስር የሰደደ ህልዉና ያላት ቢሆንም የአማራ ሃይማኖት ነች ተብላ የተፈረጀችዉ ከትግራይ በወጡ የህወሃት መሪዎች ነበር፡፡ የአማራ በመባሏ ሳቢያም ቤተ-መቅደሶቿ ተቃጥለዉ ካህናቶቿ/ምዕመኗ እየተገሉ እየተሳደዱ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ቤተ-ክርስትያኗ ለአማራ ህዝብ የመጣዉን የጥላቻ ጦስ ሁሉ አስተናግዳለች፡፡ የቤተ-ክርስቲያኗን በብሄር ፖለቲካ የሚመራዉ አማራ-ጠል ስርዓት ተሳቢ ለማድረግ በእጅጉ ሞክሯል፡፡

በአማራ-ጠሉ ፖለቲካ ብያኔ የሃገርን ህልዉና ጠብቆ የማቆየቱ ፖለቲካዊ ስነ-ልቦና አማራዉ በኢትዮጵያ ስም ፍላጎቱን በሌሎች ብሄሮች ላይ የሚጭንበት መንገድ ነዉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ እሳቤ ምክንያት አማራ-ጠሉ ስርዓት በርካታ ስህተቶችን ሲሰራ ኖሯል፡፡ ከእነዚህ ስህተቶች አንዱ ሃገሪቱን ወደብ አልባ ያደረገዉ እጅግ አደገኛ ዉሳኔ ነዉ፡፡ በአማራ-ጠሉ ስርዓት እሳቤ ኢትዮጵያ ወደቧን እንዳትነጠቅ የሚከፈለዉን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል መሞከር ተስፋፊነት ነዉ፤ ተስፋፊነት ደግሞ የአማራ ፖለቲካዊ ስነ-ልቦና ነዉ፡፡ ይህን እሳቤ ተከትለን ስንሄድ ለአማራ-ጠሉ የፖለቲካ እሳቤ ኢትዮጵያ እራሷ የተሰራችዉ በአማራ የተስፋፊነት ስነ-ልቦና ሳቢያ ነዉ፡፡ ይህ እሳቤ ደግሞ "በአማራ የተስፋፊነት ልማድ" ወደ ኢትዮጵያ ሃገረ መንግስት የገቡ ብሄሮች ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከኢትዮጵያ የመገንጠል መብት እንዳላቸዉ የሚደነግገዉን ህገ-መንግስታዊ አንቀጽ ወለደ፡፡ በአጠቃላይ በዚህ አዉዳሚ እሳቤ መሰረት ለኢትዮጵያ ሃገረ መንግስት ግዛታዊ አንድነት መከበር ዘብ መቆም የአማራ ስነልቦና ነዉ፡፡ የአማራ ስነ-ልቦናን ማመናመን እና ማጥፋት ደግሞ የአማራ ጠሉ ስርዓት ዋነኛ ግብ ነዉ፡፡ ስለሆነም አማራ-ጠሉ ስርዓት ወደ ስልጣን ከመጣበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ስለ ኢትዮጵያ ሃገረ መንግስት ግዛታዊ አንድነት መከበር መንግስት ሊኖረዉ የሚገባዉ ሃላፊነትና ሚና በእጅጉ ተቀይሯል፡፡ ይኸዉም ለኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት አለመጨነቅ፣ወደቧን ጨምሮ የተለያዩ ግዛቶቿን ለዉጭ ሃይል ሳይቀር አሳልፎ መስጠት እንደጥፋት ሳይሆን እንደበሳል መሪነት ይታይ ጀመር፡፡

የአማራ ጠሉ ስርዓት ፊተኛ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ አሰብን (ፈረንጆች እንኳን ለሃገራቸዉ እንዲያስቀሩ እየወተወቷቸዉ) ያለምንም ማመንታት ለኤርትራ መስጠታቸዉን ከአማራ ተስፋፊነት ርቆ የተቀመጠ ዲሞክራት መሪነታቸዉ ማመሳከሪያ አድርገዉ ያዩት እንደነበር ተመዝግበዉ የተቀመጡ ንግግሮቻቸዉ ምስክር ናቸዉ። ከንግግሮቻቸዉ አንዱን ለመጥቀስ ያህል በ1994 ዓ.ም በወጣዉ ዜጋ መጽሄት ላይ ንግግራቸዉ እንዲህ ሰፍሮ ነበር

> *የአሰብን ጥያቄ ማንሳት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ኤርትራ የምትባል ነጻ ሃገር የለችም ማለት ነዉ። ወደዚህ አይነት ጨዋታ የምንመለስበት ምክንያት የለም።የኛ አላማ ልማት ነዉ፣ዲሞክራሲ ነዉ፣ሰላም ነዉ። ልማት፣ሰላም፣ዲሞክራሲና ግዛት አብረዉ አይሄዱም። አንድን ህዝብ ያለፍላጎቱ ማስተደደር አብረዉ አይሄዱም አይቻልም አይገባምም። (ጌታቸዉ ረዳ፣ዜጋ መጽሄት "ሰላዩ ስዕላይ ባራኪ! እነሆ ጉያችን ዉስጥ በ1994 (እንዳለ ጌታ ከበደ በበዓሉ ግርማ ህይወቱና ስራዎቹ ከሚለዉ መጽሃፍ ገጽ 307 የተገኙ።)[5]*

አማራ-ጠሉን ስርዓት ከአቶ መለስ ፓርቲ ከህወሃት ተቀብሎ እየመራ ያለዉ ኦነግ ቀመሱ የብልፅግና አስተዳደርም  ከአቶ መለስ የተለየ እሳቤ የለዉም። ከአመታት በፊት የሱዳን ጦር የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ጥሶ ገብቶ የጎንደርን ግዛቶች በርካታ ቦታዎች በተቆጣጠረበት ጊዜ የሃገር ዳር ድንበርን ለማስጠበቅ የተቋቋመዉን የሃገር መከላከያን ይመሩ የነበሩት ጄኔራል ባጫ ደበሌ ለመሬት እና ግዛት ብለዉ ከማንም ጋር ግጭት ዉስጥ እንደማይገቡ ያለምንም ሃፍረት ይናገሩ ነበር። በአጠቃላይ አማራ-ጠሉ ስርዓት አንድ ሃገረ መንግስትን ለማስቀጠል፣ሃገርን ለማሳደግ የሚያስችሉ ላቅ ያሉ የፖለቲካ ስነልቦናዎችን ሁሉ የአማራ ፖለቲካዊ ስነልቦና ናቸዉ በሚል ሲዘምትባቸዉ በመኖሩ ኢትዮጵያ ዛሬ ያለችበት ደረጃ ላይ ደርሳለች። ስርዓቱ ይህንን ስህተቱን የተረዳዉ ዛሬ ላይ ለወደብ የሚከፍለዉ ገንዘብ ከእጁ ላይ ሲያጣ ነዉ። ይህን ችግር ለመፍታት መፍትሄ ብሎ የሚሄድበት መንገድ ደግሞ ከችግሩ የማይሻል ነዉ።

---

[5] እንዳለጌታ ከበደ፣ በአሉ ግረማ፡ ህይወቱ እና ስራዎቹ፣ 2009 ዓ.ም

ጠቅለል ሲደረግ አማራ-ጠሉ ስርዓት ኢትዮጵያ አማራን ትመስልበታለች ብሎ የፈረጀዉን ባህላዊ ገጽታ ሁሉ እያሳደደ ማዉድም ከዋነኛ የፖለቲካ ግቦቹ ቀዳሚዉ ነዉ፡፡ የአንድን ህዝብ መገለጫ ባህሉን በመንግስታዊ እቅድ የማጥፋት እርምጃም ሆነ እሳቤ ህዝቡ በሃገሩ ላይ ህልዉ ሆኖ የሚገለጽበት ምልክቶቹን የማጥፋት አደገኛ ምልክት ብቻ ሳይሆን የዘር ማጥፋት ወንጀል አንዱ ዘርፍ ነዉ፡፡ የአንድን ማህበረሰብ ባህል በማዉደም የሚገለጸዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል አይነት በአማርኛዉ አቻ ቃል ባላገኘለትም በ እንግሊዝኛዉ "Ethinocide" በመባል የሚታውቅ ወንጀል ነዉ፡፡ ይህ ወንጀል በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ድንጋጌ የተደነገጉትን ማንኛዉም ህዝብ ባህሉን የመጠበቅ፣የማሳደግና ወደ ትዉልድ የማስተላለፍ መብት የሚጣረስ ነዉ፡፡ ሆኖም በሃገራችን አማራ-ጠል ልሂቃን ዘንድ ይህን ወንጀል በአማራዉ ላይ መፈጸም እንደ ጀብዱ የሚወራ ብቻ ሳይሆን የሌሎችን ብሄሮች መብት እንደማስከበር ሆኖም ይቆጠራል፡፡

በአማራ ህዝብ ባህሎች ላይ የሚፈጸመዉ የ"ethinocide" ወንጀል ቀጣይነት እንዲኖረዉ ያደረገዉ የአማራ ልሂቅ የባህሎቹ መመናመን እና መዉደም የሚያመጣዉን አደጋ በዉል ሊረዳ ባለመቻሉ ነዉ፡፡ የአንድ ህዝብ ባህላዊ ህልዉነት መመናመን እና መጥፋት ማለት ህዝቡ በሃገሩ ሁለንተናዊ ጉዳይ ላይ ያለዉን ድርሻ ማዉደም፣ ለወደፊት የሚኖረዉን ሚናም ማጥፋት ማለት ነዉ፡፡ የዚህ አካሄድ መጨረሻ ግብም አንድ ህዝብ ህልዉናዉን ጠብቆ በራሱ ቀለም ከመኖር ወደ አለመኖር መቀየር ማለት ነዉ፡፡ የአማራን ህዝብ ባህላዊ ህልዉና ከማጣጣል እስከ ማዉደም የሚደርሰዉ አማራ-ጠሉ ዘይቤ የመጨረሻ ግብም የአማራ ህዝብ ባህላዊ ግዝፈቱ ጎልቶ እንዳይታይ ማድረግ ነዉ፡፡ ባህል ደግሞ የአንድ ህዝብ ክብርና ኩራቱ ምንጭ የእድገቱ ዋስትና ስለሆነ ባህሉን ማጣጣል ማመናመን እና ማክሰም ማለት ስነልቦናዉን መስለብ፣ የእድገት ግስጋሴዉን መግታት እና በራስ መተማመኑን ማጥፋት ማለት ነዉ፡፡

## 4-የታሪክ ህልዉና (የትርክት ቅልበሳ)

ሃገራችን ኢትዮጵያ ለረዥም አመታት በሃገረ መንግስትነት እንድትቀጥል ያስቻሉ በርካታ የታሪክ አሻራዎች ቢኖሯትም ዘመን ሲለወጥ አብረዉ መለወጥ፣ መስተካከል እና መሻሻል ያለባቸዉ የታሪክ ዱካዎችንም የያዘች ሃገር ነች፡፡

የአማራ ህዝብም በሁለቱም የታሪክ አሻራዎች የበኩሉን ያዋጣ፣ለወደፊቱ የሃገራችን ጉዞም ጉልህ ተሳትፎ ሊኖረዉ የሚገባ ሰፊ ህዝብ ነዉ። ሆኖም አማራ-ጠሉ የፖለቲካ ጎራ የአማራ ህዝብ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ዉስጥ ያዋጣዉን መዋጮ ሁሉ በክፉ የመተርጎም ስልትን የሙጥኝ ብሎ ስልጣን ላይ የተሰየመ ቡድን ነዉ። በዚህ ጎራ ፖለቲካዊ እሳቤ መሰረት የአማራ ህዝብ በታሪክ ዉስጥ ያበረከታቸዉ መዋጮዎች በሙሉ ሌሎችን የሃገሪቱን ብሄሮች ለመጉዳት፣ ለመጨፍለቅ፣ ለመበዝበዝ፣ ለመጨቆን ተደርገዉ ይቀርባሉ። በመሆኑም የአማራ ህዝብን በኢትዮጵያ የሚገኙ ሌሎች ብሄረሰቦች ብሄራዊ ጠላት አድርጎ የመዉሰዱ ነገር በአማራ-ጠሉ ፖለቲካ ቀማሪዎች፣ አራማጆች፣ አቀንቃኞች እና ደጋፊዎች ዘንድ መግባባት የተያዘበት ግንዛቤ ከመሆን አልፎ የሃገራችን የብሄር ፖለቲካዉ መግባቢያ ቋንቋ የሆነዉን አማራ-ጠል ትርክት አዋልዷል።

ትርክቱ የአማራ ህዝብ ከኢትዮጵያ ሃገረ መንግስት ጋር ያለዉ እዉነተኛ የታሪክ መስተጋብር አማራ-ጠሉ ጎራ በፈበረከዉ እዉነት ዉሸቱን በአካዳሚዉ ዓለም በማይመሳከር ምናብ እንዲተካ አድረጓል። በሌላ አባባል አማራ-ጠሉ ስርዓት በትጋት በሰራዉ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ሳቢያ የአማራ ህዝብ በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ያስመዘገበዉ አስተዋጽኦ በእኩይነቱ ብቻ እንዲታወቅ ሆኗል። ይህ የአማራ-ጠሉ ጎራ የፖለቲካ "እዉቀት" መጀመሪያ ነዉ። በዚህ ጎራ ህግ የፖለቲካ ጥበብ መጀመሪያ አማራን መጥላት ነዉ። በዚህ ትርክት አቀንቃኞች እሳቤ የአማራ ህዝብ ለሃገረ መንግስት መሰራት እና መቀጠል ያበረከተዉ ህይወትን ጭምር የተከፈለበት ዉድ አበርክቶ እንደመርገም ጨርቅ የሚቆጠር ነዉ። "ሃገር ከእግዚአብሄር በተሰጠ ጥበብ ብቻ ይመራል" የሚል ጥብቅ እምነት የነበራቸዉ ነገስታት "በአማራ ትምክህት" ሃገር የሚመሩ ዘረኞች ተደርገዉ ተብጠልጥለዋል። ነገር ግን ነገስታቱ በትዉልድ አማራ ሊሆኑ ይችላሉ እንጅ የብሄር ማንነታቸዉን የስልጣን መያዣና ከአማራ በቀር ሌላዉን ብሄር መጉጃ አድርገዉ የሚያስቡበት የፖለቲካ ስነ-ልቦና አልነበራቸዉም። ይልቅስ ስልጣን መያዛቸዉንም ሆነ ስልጣን ማጣታቸዉን ከፈጣሪ ፈቃድ የሚያገናኙ ነበሩ። ስለሆነም በስልጣን ዘመናቸዉ ስለሚሰሩት ጥፋት ተጠያቂነታቸዉን የሚያስተሳስሩት ከፈጣሪ ጋር ነበር።

አማራ-ጠሉ ጎራ በትግል መባቻ ሁሉንም የአማራ ህዝብ ጨቋኝ በማለት ፈርጆ የተነሳ ነበረ። አንድን ህዝብ በጅምላ ጠላት አድርጎ መነሳት ስህተት መሆኑን ዉሎ አድሮ ሲገነዘብ ደግሞ ጠቡ ከአማራ ገዥ መደብ ጋር እንደሆነ መወትወት ጀመረ። የትርክቱንም ጭብጥ አልቦነት ማሳያዉ ይህ አባባል ነዉ። አማራ-ጠሉ ስርዓት ጠቡ ከአማራ ገዥ መደብ ጋር እንደሆነ በሚያዉጀበት ወቅት ብሄሩን ሰረገላ አድርጎ ስልጣን ላይ ተፈናጦ ሃገር ሲዘርፍ የነበረዉ የትግሬ ገዥ መደብ እንጂ የአማራ ገዝ መደብ የሚባል ነገር በመንበረ ስልጣን ላይ አልነበረም። ስለዚህ የአማራ-ጠሉ ስርዓት ትግል በፖለቲካዉ ህልዉ ሆኖ ስልጣን የያዘ አካል ጋር ሳይሆን ልክ የመሰላቸዉን ሰርተዉ ወደ ማይመቀረዉ ከሄዱት ከአማራ ነገስታት ጋር ነበር። ሆኖም በተጨባጭ ሲታይ የአማራ-ጠሉ ስርዓት ትግልም ሆነ ጠብ የአማራ ገዥ መደብ ከሚለዉ ህልዉ ያልሆነ አካል ጋር ሳይሆን አማራ ከተባለዉ ህዝብ ጋር እንደሆነ በሃገሪቱ ዳርቻ በአሰቃቂ ሁኔታ ተፈጅቶ በዉርደት እንደቆሻሻ ተጠቅልሎ በጅምላ የሚቀበረዉ የድሃዉ አማራ ደም ምስክር ነዉ።

አማራ-ጠሉ ጎራ በጥላቻ ደመነፍስ ተነስቶ የፈጠረዉ ትርክት በእጅጉ የጎዳዉ የአማራ ህዝብ ታዲያ ሞት ያሳወጀበት ትርክት እንዲሰበርለት በእጅጉ ለምኖ ነበር። የጨዋ ልመናዉ ሰሚ ያላገኘዉ የአማራ ህዝብ ታዲያ ዋስትናዉ ትግሉ ብቻ እንደሆነ ከነባራዊ ኑሮዉ ተረድቶ አልሰማም ያሉትን በተራዉ አልሰማም ብሏል። አማራ-ጠሉ ስርዓት አማራዉ ሲያቀርብ የነበረዉን የትርክት ቅልበሳ ልመና ጆሮ ዳባ ልበስ ያለበት ምክንያት ስርዓቱ የሚፈልገዉና የአማራ ህዝብ የሚጠይቀዉ ሆድና ጀርባ ስለሆነበት ነዉ። አማራ-ጠሉ ስርዓት የሚፈልገዉ አማራዉ በትርክት የተደፈደፈበትን የወንጀለኛነት ክስ ተቀብሎ፣ሁሌ በይቅርታ መንፈስ ሆኖ፣ የሚወርድበትን መአቱን ሁሉ አጎንብሶ እንዲቀበል ነዉ። በዚህ ምክንያት ነዉ ስርዓቱ የአማራ ህዝብ የተሰነዘረበትን ትርክት ወለድ ፍላጻ ለማስቀረትም ሆነ ሌሎች ጥቄዎቹን ለማስመለስ የሚያደርገዉን ትግል ምክንያት አልቦ የጦረኝነት አባዜ አድርጎ ሲያጣጥል የሚሞክረዉ። ስልጣን ላይ ያለዉ አማራ-ጠል ስርዓት እያሳየ ያለዉ የአማራ ህዝብን ጥያቄዎች የማጣጣል፣የማናናቅና የማዳፈን ሙከራ አማራዉ ጥያቄዎቹን ማስመለስ የሚችለዉ ስልጣን ሲይዝ ብቻ እንደሆነ እንዲገነዘብ አድርጓል።

## 5-ማህበራዊ ህልዉና

ሃገራችን ባነበረችዉ የብሄር ፖለቲካ ዘይቤ የብሄር ቁጥር ስልጣን ለመያዣ ብቸኛዉ ተፈላጊ ነገር ነዉ። በቁጥር ብዙ የሆነዉ ብሄር ስርወ-መንግስት መሳይ ነገር መስርቶ ስልጣን ላይ ለመወዘት ከልካይ የሌለዉ ነዉ። በአንጻሩ በቁጥር ጥቂት የሆኑ ብሄሮች ደግሞ በሃገራችን ዋነኛ የስልጣን ኮረቻ ላይ ለመዉጣት ያላቸዉ እድል ግመል በመርፌ ቀዳዳ አይነት ነገር ነዉ። ከዚህ አንጻር ህወሃቶች በጥቂት ቁጥር ብሄር ሃገራችንን ለሩብ ምዕተ አመት መግዛት መቻሉ የተለየ ነገር ሊመስል ይችላል። ሆኖም ህወሃት ስልጣን የያዘዉ በትጥቅ ትግል እንጂ በብሄር ፖለቲካዉ የጨዋታ ህግ ተጫዉቶ አልነበረም። በትጥቅ ትግል ወደ ስልጣን መጥቶ ያዋለደዉ የብሄር ፖለቲካ የኊላኊላ እራሱ አዋላጁን ከወንበር ላይ የተገፈተረዉ በብሄር ቁጥር የትየለሌ የሚበልጠዉ ኦህዴድ የጨዋታ ህጉን ስለሚያሟላ ነዉ። ለህወሃት ከስልጣን መገፍተር ምክንያቱ በግፈኛ አስተዳደር ዘይቤዉ ላይ ንዑስ ቁጥርነቱ ተደራርቦ ነዉ። በህወሃት እና እህት ድርጅቱ ኦህዴድ የስልጣን ቅብብል መሃከል ብቅ ብለዉ የነበሩት አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ የብሄር መሰረታቸዉ በቁጥር ጥቂት ከሆነዉ የወላይታ ብሄር መሆኑ የብሄር ፖለቲካዉን እንደ ልባቸዉ እንዳይዘዉሩ ደንቃራ ነበር። ስለሆነም ኦህዴድ/ኦሮሞ ብልጽግና "ብትነኩኝ በሺዎች የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ ይተላለቃል" የሚልለትን ወንበር አቶ ሃይለማርያም "የዉሰዱልኝ" ማመልከቻ አስገብተዉ ከወንበር ፍች አደረጉ።

መሰረታዊ የፖለቲካ ቀለሙን አማራን በመጥላትና በማሳደድ ያደረገዉ የሃገራችን የብሄር ፖለቲካ ጠላት አድርጎ የሳለዉ የአማራ ብሄር በብሄር የቁጥር ብልጫዉ (Demographic Advantage) ስልጣን ላይ የመዉጣት ሰፊ እድል እንዳለዉ ስለሚያዉቅ የአማራን ህዝብ ቁጥር ሲከረክም ኖሯል። ክርከማዉን ለማካሄድ ብዙ መንገዶችን ይጠቀማል በመጀመሪያዉ ዘዴ በሃገሪቱ ህዝብ ቆጠራ ሲደረግ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማሮች የገቡበት ጠፉ የሚል ሰሚን ሁሉ የሚያስደንቅ ግልጽ ክህደት መካድ ነዉ። ሁለተኛዉ መንገድ ከ90% በላይ የሚሆነዉ ነዋሪ ህዝብ የአማራ ተወላጅ የሆኑበትን ግዛቶች ወደ አማራ ክልል በማካለል ፋንታ በግድ ወደ ሌሎች ክልሎች እንዲካለሉ ማድረግ ነዉ። በእነዚህ ክልሎች የተከለሉ የአማራ ተወላጆች በግድ በተከለሉባቸዉ ክልሎች ዉስጥ ሆነዉ "አማራ ነኝ" ማለት ለህይወታቸዉም ለንብረታቸዉም አደገኛ ነገር እንደሆነ ከህይወት ልምዳቸዉ ይገነዘባሉ።

ስለዚህ በህዝብ ቆጠራ ስዓት የሚኖሩበትን ክልል ማንነት ማንነታቸዉ አድርጎ በማስመዝገብ ህይወት እና ንብረታቸዉን ለማትረፍ የሚሞክሩ የአማራ ተወላጆች አሉ። ይህን አካሄድ ልክ ባልሆነ መንገድ የአማራዉን ቁጥር የሚቀንስ እና የሌላዉን ብሄር ቁጥር የሚጨምር አሳሳች የህዝብ ቆጠራ ምዝገባን የሚፈጥር ነዉ። አማራ ጠሉ ስርዓት የሚፈልገዉም ይሄን ነዉ።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ አሁን ስልጣን ላይ ያሉት ጠ/ሚኒስቴር ኦሮሚያ ክልል ዉስጥ ያሉ አማሮች እንደ አማራ ሳይሆን እንደ ኦሮሞ መቆጠር እንዳለባቸዉ፣የአማራ ህዝብ መብት ተሟጋቾችም ስለ እነዚህ ሰዎች መናገር እንደሌለባቸዉ በፓርቲያቸዉ ስብሰባ ላይ ለአማራ ብልጽግና መኳንንት ሊገልጹ እንደሞከሩ በቦታዉ የነበረ ሰዉ አጫዉቶኛል። ጠ/ሚኒስቴሩ ይህን የሚሉት በኦሮሚያ ክልል በተለይ በወለጋ፣በአርሲ ወዘተ እልቂት የታወጀባቸዉን አማሮች ጉዳይ ማንም እንዳያነሳ በር መዝጋታቸዉ እንጂ ለሌላ እንዳልሆነ ግልጽ ነዉ። የሆነዉ ሆኖ ጠ/ሩ የሚሉትን ብንቀበል በአማራ ክልል የሚኖሩ የከሚሴ ኦሮሞዎችም እንደ አማራ መቆጠር ነበረባቸዉ ማለት ነዉ። ሃቁ ግን ሌላ ነዉ። በአማራ ክልል የሚኖሩ ኦሮሞም ሆኑ የሌላ ብሄር ህዝቦች ቁጥራቸዉ ተከርክሞ ማንነታቸዉ ወደ አማራነት ሊቀየር ቀርቶ ራሳቸዉን የሚያስተዳድሩበት ልዩ የብሄረሰብ አስተዳደር እንዲኖራቸዉ ተደርጎ፣ለሰዉ ልጅ በሚገባ ክብር እንደሚኖሩ የሚታወቅ ነዉ።

-

የአማራን ህዝብ ቁጥር መከርከም ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት የአማራ-ጠሉ የብሄር ፖለቲካ ስርዓት አማራዉ ወደ ስልጣን ዝር እንዳይል አጥብቆ ስለሚሻዉ። አማራዉ የብሄር ፖለቲካ የሚጠይቀዉን የብሄር ቁጥር ግዝፈት ጠቅሶ የስልጣን ኮርቻን የማማተር እድል እንዳለዉ ደግሞ የማይካድ ሃቅ ነዉ። ይህ የአማራዉ የብሄር ቁጥር ግዝፈት አማራ-ጠሉ ስርዓት አስቀድሞ በአማራዉ ላይ የወሰነዉን ወደ ስልጣን እንዳይመጣ የማገድ ዉሳኔ ጥያቄ ዉስጥ እንደሚጥል ይታወቃል። ስለዚህ አማራዉ በቁጥር ቅሸባ ቁጥሩ እንዲያሽቆለቁልና አንድ ብሄር(ኦሮሞ) በሩቅ እርቀት በቁጥር እንደሚበልጠዉ አድርጎ ማቅረቡ አማራዉን ከስልጣን አግልሎ ለማስቀረት ሁነኛ መንገድ ነዉ። ከስልጣን ከማግለል ቀጥሎ የአማራን ህዝብ ቁጥር መቀናነስ ያስፈለገበት ምክንያት በጀት ነዉ። በብሄር ፖለቲካዉ እንደስልጣን ሁሉ በጀት የሚመደበዉ በብሄር የተካለሉ ክልሎችን ከሚያቀርቡት የብሄር ቁጥር አኳያ ነዉ።

ስለሆነም የአማራዉን ቁጥር በትክክል ማስቀመጥ ማለት የአማራ ህዝብ የሚገባዉን በጀት ሊበጀትለት ግድ ይሆናል። በስርዓቱ በጠላትነት የተፈረጀዉ የአማራ ህዝብ ደግሞ የሚገባዉን ስልጣን እንደተከለከለ ሁሉ የሚገባዉን በጀትም ተከልክሎ በድህነት መቀጣት አለበት።

የአማራ ክልል የድህነቱ ምጣኔ ሃገሪቱ በአጠቃላይ ካላት የድህነት ምጣኔ በሁለት/ሶስት ፐርሰንት እንደሚበልጥ የዓለም ባንክ በአንድ ወቅት ያስጠናዉ ጥናት ላይ እንዳነበብኩ አስታዉሳለሁ። ጥናቱ አክሎም አማራ ክልል በሃገሪቱ ካሉ ክልሎች ሁሉ በመሰረተ ልማት ኋላ ቀሩ እንደሆነና ክልሉ እርስ በእርሱ በመንገድ ያልተያያዘ እንደሆነ ይገልጻል። በሃገራችን በከፋ ረሃብና የህጻናት መቀንጨር የሚታወቀዉ ቦታ በአማራ ክልል የሚገኘዉ ሰቆጣ የሚባለዉ አካባቢ መሆኑ ነዉ። የሰቆጣ ዲክላሬሽን የተባለዉን ስምምነት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ሃገራችን እንድትፈራረም መንስኤ የሆነዉ ሃገራችን ዉስጥ እጅግ አስከፊ የሆነ የህጻናት በቂ እና ተመጣጣኝ ምግብ ያለማግኘት፣መቀንጨር እና የእድገት ዉስንነት መሆኑ በመረጋገጡ ነዉ። ይሄ ሁሉ የድህነት ማጥ የመጣዉ የአማራ ህዝብ ከድህነት መዉጫዉ የታታሪነት ማህበረሰባዊ እሴት አንሶት ሳይሆን አማራ-ጠሉ ስርዓት በረቀቀ ሁኔታ የሚጭንበት ቀንበር ቀና እንዳል ስላላስቻለዉ ነዉ።

የአማራን ህዝብ ቁጥር በመቀሸብ ተገቢዉን የፌደራል መንግስት በጀት እንዳያገኝ የሚያደርገዉ አማራ-ጠሉ ስርዓት ለክልሎች እድገት አይነተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የዉጭ ሃገር መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወደ አማራ ክልል ሄደዉ እንዳይሰሩ በስዉር እና ግልጽ ሁኔታ ይሰራል። የአማራ ክልልን የሚመሩ ፖለቲካ በዞረበት ያልዞሩ የብአዴን አመራሮችም እነዚህን ድርጅቶችን ለመሳብ የሚያስችል እዉቀቱም ፍላጎቱም የላቸዉም። ይህ ሁሉ ሆኖ የአማራ ክልል ህዝብ ከመንግስት ያጣዉ የልማት ጭላንጭል መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችም እንዳያገኝ አድርጎታል። በአንጻሩ የህወሃት መኳንንት የፌደራል ስልጣኑን ተቆጣጥረዉ በነበረ ጊዜ ከዉጭ ድርጅትም አማርጠዉ በሌሎች ክልሎች የተሻለ የማልማት አፈጻጸም ያሳዩት ወደ ትግራይ ክልል እንዲሄዱ ያደርጉ እንደነበር፣ለዚህም በሲዳማ ዞን ጥሩ የልማት እንቅስቃሴ ያሳየዉ "Irish Aid" በምሳሌነት በመጥቀስ አብረዋቸዉ ሲሰሩ የነበሩ ጓዶቻቸዉ ይመሰክራሉ።

አማራ-ጠሉን ስርዓት ለመምራት ተራዉን ከህወሃት የወሰደዉ የኦሮሞ ብልጽግና ስልጣን ላይ በወጣ ማግስት ከሌላ ክልል በተለየ እና እጅግ አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ የአማራ ክልል ተማሪዎች የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ዉጤታቸዉን ባዶ እንዲሆን ያደረገበት መንገድ ስርዓቱ የአማራ ህዝብን የሚጠላበትና ለመጉዳት የሚሄድበት መንገድ በመሪዎች መቀያየር የሚብስ እንጂ የሚሻል ነገር እንደሌለዉ የሚያስረግጥ ነዉ፡፡ ለወትሮዉ የአማራ ክልል ተማሪዎች ለእንደዚህ አይነት ብሄራዊ ፈተናዎች የሚያስመዘግቡት ላቅ ያለ ዉጤት ነዉ፡፡ የአማራ ህዝብ/ልሂቅ በማንነቱ ላይ የሚቃጡበትን ግልጽ እና ስዉር ጥቃቶችን በቶሎ ተረድቶ እንደ አመጣጣቸዉ፣አደገኝነታቸዉን በሚመጥን መንገድ መልስ ያለመስጠት የቆየ ልምድ ስለነበረዉ ይህ በተማሪዎች ህይወት ላይ ለመቀለድ የተሞከረዉ ሙከራም ህዝቡ ካልነቃ በየዓመቱ ለማስቀጠል የታለመ እንደሚሆን ከስርዓቱ ባህሪ መረዳት ይቻላል፡፡ በወለጋ፣በቤንሻንጉል በተደረጉት አሰቃቂ የዘር ፍጅቶች አማራዉም ተባብሮ መቃወም ስላልቻለ ለአመታት እንደቀጠሉ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎች ዉጤት ጉዳይም ከዚህ የተለየ አይሆንም ነበር፡፡ በአማራ ተማሪዎች ላይ የተሞከረዉ አስተዛዛቢ ሙከራ አማራዉ ከማህበራዊ ጉዳዮች አንዱ በሆነዉ የትምህርት መስክ ጨብጦት የኖረዉን በቂ ምሁራንን የማፍራት መዋጮ ለማቀጨጭ እና የማህበራዊ ፍትህን ለማዛባት የተደረገ አደገኛ ሙከራ ነበር፡፡ በአጠቃላይ አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራዉን ማህበራዊ ህልዉና ለማሳሳት የሚያደርገዉ ጥረት ዲሞግራፊያዊ ቁጥሩን ከርክሞ በድህነት ከማማቀቅ እስከ በታዳጊ ተማሪዎች የወደፊት ህይወት ላይ መፍረድ የደረሰ አደገኛና ጨካኝ እንደሆነ መገንዘብ የትግል ወገብን ጠበቅ አድርጎ መብትን ለማስከበር ይበጃል፡፡

## 6- የግዛት ህልዉና

አማራ-ጠሉ የብሄር ፖለቲካ በአማራዉም ግዛታዊ ህልዉና ላይ የሚደቅነዉ አደጋ ሶስት ዋና ዋና ስልቶችን በመከተል ነዉ፡፡ የመጀመሪያዉ ስልት በ1980ዎቹ በተደረገዉ የኢትጵያን ሃገረ መንግስት በብሄር ክልሎች የማደራጀት ፖሊሲዉ የአማራ ክልል ግዛቶችን ወደ አጎራባች ሃገሮች በማካለል የአማራ ክልልን ግዛታዊ ግዝፈት ማኮሰስ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ስልት በአማራ ክልል የህዝቦችን የብሄር/ቋንቋ ብዝሃነትን ለማክበር ሲባል የተፈጠሩ ልዩ የብሄረሰብ ዞን አስተዳደሮችን የአማራ-ጠሉ ፖለቲካ አማራን ማጥቂያ ሴራ መጠንሰሻና ማስፈጸሚያ ሜዳዎች እንዲሆኑ ማመቻቸት ነዉ፡፡

ሶስተኛዉ ስልት የአማራ ክልልን በአዉራጃዊ ስሜት በመከፋፈል የአማራ ማንነት ስሜት በአዉራጃዊ ስሜት እንዲዋጥ ማድረግ ነዉ፡፡ እነዚህን ሶስት ዋነኛ ስልቶችን በመጠቀም አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራ ክልልን ግዛታዊ ህልዉና አደጋ ላይ የሚጥልባቸዉን አካሄዶች ጠለቅ ብሎ መመርመር አስፈላጊ ስለሆነ ከመጀመሪያዉ ጀምረን ወደ ማየቱ እንለፍ፡፡

ከ1983 ዓ.ም ወዲህ በተዘረጋዉ የብሄር ፖለቲካ አሰራር ሃገራችን በብሄር ላይ ወደ ተከፋፈሉ ክልሎች ተሸንሽናለች፡፡ አማራ-ጠሉ የብሄር ፖለቲካ ስርዓት ይህን በማድረጉ የብሄረሰቦችን መብት እያስጠበቀ እንደሆነ በማዉሳት የሚኩራራበት ስራዉ ነዉ፡፡ ሆኖም ወደ አማራ ክልል ሁኔታ ሲመጣ የብሄር ፖለቲካዉ ከራሱ መሰረታዊ መርሆዎች በመዉጣት የብሄረሰቦችን መብት በማክበሩ የሚኩራራበትን አሰራር የሚጋጭ ተግባር ፈጽሟል፡፡ በብሄር ማንነታቸዉ የተካለሉ ክልሎችን የፈጠረዉ ስርዓቱ ክልሎቹን የፈጠረዉ አንድ አይነት ቋንቋ የሚናገሩ እና ተመሳሳይ ስነልቦና ያላቸዉን ህዝቦች ወደ አንድ ክልል በማካለል መርህ እንደሆነ ሳያሰልስ የሚገልጸዉ ነገር ነዉ፡፡ ከዚህ መርህ በሚጋጭ ሁኔታ ግን ከ90% በላይ የሚሆነዉ ነዋሪያቸዉ የአማርኛ ቋንቋ የሚናገሩ እና ከአማራ ክልል ጋር ስነልቦናዊ ትስስር ያለዉ እንደ ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ሁመራ፣ ራያ መተከል በኒላም ደራ ያሉ ቦታዎች ወደ አማራ ክልል ማካለሉን ትቶ ወደ ትግራይ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እና ኦሮሚያ ክልሎች እንዲካለሉ ተደረገ፡፡

ይህ መደረጉ በአማራ ህዝብ ላይ ሁለት አበይት ጉዳቶችን አምጥቷል፡፡ የመጀመሪያዉ እነዚህ ግዛቶች በግፍ ወደ ሌላ አጎራባች ክልሎች መካለላቸዉ የአማራ ክልል ህዝብ ቁጥር በእጅጉ እንዲቀንስና የክልሉ ግዛታዊ ህልዉና ትርጉም ባለዉ መጠን እንዲሚሸሸ አድርጓል፡፡ ቀደም ባለዉ ንዑስ ርእስ እንደተገለጸዉ በብሄር ፖለቲካ ቀመር የግዛት ግዝፈትና የህዝብ ቁጥር ለስልጣን ወሳኝ ግብዓቶች ናቸዉ ፡፡ የአማራ ክልል ግዛቶች ወደ አጎራባች ክልሎች በቅርጫነት መታደል የአማራ ህዝብ ላይ የሚያመጣዉ ሁለተኛዉ ጉዳት ከእናት ግዛታቸዉ ተነጥለዉ ለሌላ ክልሎች የተሰጡት መሬቶች ላይ የሚኖሩ ህዝቦች በግድ ወደ ተከለሉበት ክልሎች ሲሄዱ እንደ መጤ፣ሰፋሪ፣ጨቋኝ አማራ የሚል የዘር ማጥፋት ወንጀል ኮዶች ተለጥፈዉባቸዉ ከአሰቃቂ ማንነት ተኮር የዘር ማጥፋት ግድያ ይዳረጋሉ፡፡

በመተከል፣ በወልቃይት ጠገዴ የሚኖሩ አማሮች ያሳለፏቸዉ የእልቂት አመታት ማንም ሊሸፋፍነዉ የማይችለዉ የስርዓቱ መንግስታዊ ዘር ማጥፋት ወንጀል ማህተሞች ናቸዉ። እነዚህ ግዛቶች በጣም ለም እና በስፋትም ግዙፍ መሆናቸዉ የአማራ ክልልን በእጅጉ የሚጎዳ ጉድለት የሚያመጡ ናቸዉ።

በወልቃይት ጠገዴ የሚመረተዉ የሰሊጥ እና የእንስሳት ምርት ግዛቱን ነጥቀዉ የወሰዱ የትግራይ ልሂቃንን ወደ ባለጸግነት ማማ ያስወነጨፉ ናቸዉ። ለቤንሻንጉል ጉሙዝ የተሸለመዉ መተከል የጎጃም ክፍለ ሃገር በስፋት ቀዳሚዉ አዉራጃ ነበር። ለምነቱም ቢሆን እንደ አብዛኛዉ የጎጃም መሬት ብዙ ምርት የሚያሳፍስ ነዉ። የአማራ ክልል  እነዚህን ክልሎች በማጣቱ በኢኮኖሚዉ ረገድ ብዙ የተጎዳ ቢሆንም የሚብሰዉ ጉዳት ግን በነዚህ ግዛቶች ላይ አማራ መሆን አደገኛ ወንጀል ሆኖ ተቆጥሮ የአማራ ህዝብ በህይወቱ የከፈለዉ ከባድ ዋጋ ነዉ። የአማራ ህዝብ እነዚህ ግዛቶቹ እንዲመለሱለት ሲጠይቅም አማራ-ጠሉ ስርዓት እንደሚለዉ የግዛት አምላኪነት አባዜ ተጠናዉቶት አይደለም። ዋናዉ ነገር የሰዉ ልጅ ህይወት ነዉና የአማራ ህዝብ ለትግል ያስነሳዉ ትልቁ ጉዳይ እነዚህን ግዛቶች በግፍ መነጠቁ ሳያንስ የሚፈጸምበት የዘር ማጥፋት ወንጀል ዝም ብሎ የሚያስቀምጥ ተራ ነገር ስላልሆነ ነዉ። በአጠቃላይ የአማራ ህዝብ ስለተወሰዱበት ግዛቶቹ መመለስ ሲጠይቅ እየጠየቀ ያለዉ ከመሬቶቹ ጋር ስለተነጠቀዉ በህይቀት የመኖር መብቱ፣ስለዲሞግራፊያዊ ግዝፈቱ፣ስለኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቱ ስለ ፖለቲካዊ ዉክልናዉ ሁሉ ነዉ።

የአማራ ክልሎችን ለአጎራባች ክልሎች ከማቃረጡ በመቀጠል አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራ ክልልን ግዛታዊ ህልዉና የሚያዉክበት ሌላዉ መንገድ የአማራ ክልል ሲል በሰየመዉ ክልል አዉራጃዊነትን ስፖንሰር በማድረግ ህዝቡ በአማራ ማንነቱ ተሰባስቦ በአማራነቱ የተቃጣበትን ጥቃት እንዳይመክት ማድረግ ነዉ። ስርዓቱ አማራ የተባለን ሁሉ ከየትም ይምጣ ከየት እያሳደደ ሁለንተናዊ በደል የሚያደርስ ሆኖ ሳለ የአማራ ህዝብ ግን አማራነት እንዳይሰማዉ ይልቅስ በአዉራጃዊነቱ ላይ እንዲበረታ ግልጽም ስዉርም እርምጃ ይወስዳል።

ከእነዚህ እርምጃዎች አንዱ የአማራ ብልጽግናን የሚመሩ ፖለቲካ በዞረበት ያልዞሩ ሰዎችን በአዉራጃዊነት ማጥ ዉስጥ እንዲገቡ በማድረግ፣ይህንኑ ተከትለዉ የሚያራግቡ የመንደር አክቲቪስቶችን በመግዛት በየማህበራዊ ድረገጹ በማሰማራት፣የጥፋት ሰነዶችን በመጻፍ የሚተመን ተልዕኮ በመስጠት የአማራ ማንነት ስነልቦናን በመንደርተኝነት ለመተካት በእጅጉ ተግቶ እየሰራ ይገኛል፡፡

አማራ-ጠሉ ስርዓት በአማራ ብልጽግና ዉስጥ መንደርተኝነትን ከሚዘራባቸዉ መንገዶች አንዱ የአንዱን አካባቢ ልሂቅ በማቅረብ፣በመሾምና የአካባቢዉን ባለሃብቶች ያለአግባብ ሃብት እንዲያፈሩ እንዲያደርግ በመተዉ የመንደርተኝነቱን ጥቅም ተኮር ተከታይ ሰልፍ ማርዘም ነዉ፡፡ በዚህ ላይ የአማራ ብልጽግና/የቀድሞዉ ብአዴን/ ወለድ ባለሃብቶች ደግሞ በበኩላቸዉ የአማራ አክቲቪስት ተብየዎችን በመቅጠር መንደርተኝነቱን ያለሃፍረት እንዲያራግቡ ያደርጋል፡፡ በዚህ ሳቢያ የአማራ ተወላጅ ልሂቃን ዋናዉን ባለጋራቸዉን ወዳጅ አድርገዉ በገዛ ወንድሞቻቸዉ ላይ ሰይፋቸዉን ይመዛሉ፡፡ በዚህ የመንደርተኝነት ሰይፍ ህይወት ሳይቀር መቅጠፍ አልበቃ ብሎ በብአዴን ቤት የተጠነሰሰዉ መርዛማ ጥንስስ ወደ አብን ቤትም ተዛምቶ ፓርቲዉን አሽመድምዷል፣የአማራን ህዝብንም ያለጠበቃ አስቀርቷል፡፡ ይህ ችግር አሁንም በጥንቃቄ ካልተያዘ የሚያመጣዉ መዘዝ ከባድ ነዉ፡፡

የአማራ ብሄርተኝነት ገዝፎ ከወጣ አማራ-ጠሉ ስርዓት መኖር እንደማይችል ጠንቅቆ ስለሚያዉቅ ነዉ የመንደርተኛነቱን ሾተላይ በአማራ ብሄርተኝነት ጎን ላይ መሰካት እንደ መፍትሄ ወስዶ ጠንክሮ የሚሰራበት፡፡ ስርዓቱ መንደርተኝነትን በብአዴን በኩል ስፖንሰር በማድረግ የበላተኛ ደጋፊ ቁጥሩን ከማብዛቱ በተጨማሪ የአማራ ብሄርተኝነትን እንደ ማሳፈሪያ መንገድ በመጠቀም አማራዉ አማራ ነኝ በማለቱ እንዲያፍር የማድረግ ሙከራም በተለያዩ መንገድ ይሞክራል፡፡ ጠ/ሚ አቢይ አህመድ ወደ ስልጣን እንደመጡ  ከአማራ ክልል ወጣቶች ጋር በባህርዳር ከተማ በነበራቸዉ አንድ መድረክ "አማራ ብሄርተኝነት አያምርበትም" በማለት በግልጽ የአማራ ብሄርተኝነትን አጣጥለዋል፡፡ ብሄርተኝነት በሃገሪቱ ህገመንግስት የሃገሪቱ ፖለቲካ መዘዉር በሆነበት ሁኔታ "አማራ ብሄርተኝነት አያምርበትም" ማለት አማራ ኢ-ህገ-መንግስታዊ መሆን አለበት ብሎ እንደ መምከር ነዉ፡፡ ሰዉየዉ በተለያዩ አጋጣሚ አማራ ከማለት ይልቅ የበጌምድር ሰዉ፣የወሎ ሰዉ፣የጎጃም ሰዉ እያሉ መናገር ያበዛሉ፡፡

ይህ የሚያሳየዉ በሃገሪቱ ሌላዉ ክልል በብሄር ፖለቲካ ቀመር እየተመራ የአማራ ክልል ለብቻዉ በሲቪክ ፖለቲካ እንዲመራ የመፈለግ የአማራ-ጠሉ ጎራ ደመ-ነፍሳዊ መሻት ነዉ። የአማራን ብሄርተኝነትን አጥብቆ የመፍራቱ የአማራ ጠሉ ስርዓት አዝማሚያ ድምር ዉጤት አማራዉ በሲቪክ ፖለቲካ የሚገኘዉን የሃገር ባለቤትነት በብሄር ፖለቲካዉ ከተነጠቀ በኋላ የብሄር ፖለቲካ ቀመር የሚገኘዉን የክልል ባለቤትነትም የሚያሳጣ አደገኛ ነገር ነዉ።

የአማራ ክልልን ግዛቶች ለአጎራባች ክልሎች አከፋፍሎ ከጨረሰ በኋላ ክልሉን በመንደርተኝነት አረንቋ ዉስጥ ዘፍቆ የእርስ በእርስ እርግጫን በማፋፋም የአማራ ብሄርተኝነትን ለማክሰም ከመጣሩ በተጨማሪም አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራ ክልልን ግዛታዊ ህልዉና አደጋ ላይ ለመጣል ተጨማሪ ሶስተኛ ስልት ይጠቀማል። ይህ ሶስተኛ ስልት የአማራ ክልል የህዝቦችን ብዝሀነት በተገቢዉ መንገድ ለማክበር ሲባል የተመሰረቱ የብሄረሰብ አስተዳደር አካባቢዎችን የአማራን ህዝብ ለማጥቃት የሚጠነስሰዉ ሴራ ማስፈጸሚያ አድርጎ መጠቀምን ነዉ። በአማራ ክልል የተመሰረቱ የብሄረሰብ ዞኖች የሰዉ ልጆች ሰብአዊ መብት የሆነዉን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ለማክበር የተቋቋሙ በመሆናቸዉ በአስተዳደሮቹ መመስረት ላይ ማንም ተቃዉሞ የለዉም። እንደዉም የአማራ ህዝብ የሚጠይቀዉ እነዚህ ብሄረሰቦች በአማራ ክልል የተከበረላቸዉ የፖለቲካ ዉክልና መብት በሌላ ክልል ለሚኖሩ የአማራ ተወላጆችም ተፈጻሚ ይሁን የሚል ነዉ። ነገር ግን በአማራ ክልል ያሉ የብሄረሰብ አስተዳደሮች መብት የአማራ ህዝብን መብት እስከመጣስ የዘለቀ ጤናማ ያልሆነ እንዲሆን አማራ-ጠሉ ስርዓት የሚያደርገዉ አካሄድ ተቀባይነት ሊኖረዉ አይችልም።

በአማራ ክልል የኦሮሞ ልዩ ዞንን እንደ መጠጊያ በመጠቀም የአማራ ክልልን የማጥቃቱ የአማራ-ጠሉ እኩይ ዓላማ በአጣዬ ዘጠኝ ጊዜ መቃጠልና የመንግስት ዝምታ ተጋልጧል። በተመሳሳይ በአማራ ክልል የሚገኘዉን የአገዉ ህዝቦች አስተዳደር በመጠቀም የአማራ ክልልን አንድነት ለመሸርሸር የተሞከረዉ ሙከራ በሁለቱ ህዝቦች ንቃት ፍሬ ያላፈራ ቢሆንም የብልጽግናዉ መንግስት ከአገዉ ህዝብ የወጡ ካድሬዎችን በማሰማራት የክልሉን ፖለቲካ ለማወክ እና በሁለቱ ህዝቦች መሃል ንፋስ ለማስገባት ከንቱ ድካም መድከሙን አላቆመም።

## 7. የፖለቲካ ህልዉና

ስልጣን ላይ ያለዉ አማራ-ጠል የብሄር ፖለቲካ ስልጣን ላይ ለመሰንበት ከሚጠቀምባቸዉ መንገዶች አንዱ "የነፍጠኛዉ ስርዓት ተመልሶ እንዳይመጣ አደርጋለሁ" የሚል ማስፈራሪያ ነዉ። ይህ ዘይቤ አንድን ብሄር ጠላት አድርገዉ ስልጣን በመያዝ መንግስታዊ የዘር ማጥፋት ወንጀልን የፖለቲካ ዘይቤ ያደረጉ መንግስታት የተለመደ ባህሪ ነዉ። ዓለምን ያስደነገጠ መንግስታዊ ዘር ማጥፋትን በሩዋንዳ ያካሄደዉ ወንጀለኛ የመንግስት አስተዳደር በወቅቱ ይደጋግመዉ የነበረዉ ፕሮፖጋንዳ "የድሮዉ የቱትሲዎች መንግስት ተመልሶ እንዳይመጣ የምከለክልላችሁ እኔ ነኝ፣እኔ ከተነሳሁ የቱትሲዎች ስርዓት ይመለሳል" የሚል ማስፈራሪያ ነበር። በተመሳሳይ የአማራ ማንነትን የጥቃት ኢላማዉ ያደረገዉ የእኛ ሃገር የብሄር ፖለቲካ ስርዓት አራማጆችም የአማራ የሆነዉ የነፍጠኛዉ ስርዓት ተመልሶ እንዳይመጣ እኔ በስልጣኔ ላይ መኖር አለብኝ የሚል ፕሮፖጋንዳዉን እንደ እድሜ ማስነበቻ ይጠቀምበታል።

የነፍጠኛዉ ስርዓት ተመልሶ እንዳይመጣ የሚለዉ አባባል ጥቅል ትርጉሙ አማራዉ በሃገሩ ፖለቲካ ላይ ህልዉ ሆኖ እንዳይታይ የሚከለክል፣ስዉር እና ግልጽ ማገጃዎችን የሚዘረጋ የፖለቲካ ስርዓት በኢትዮጵያ ማንበር ማለት ነዉ። ይህ ማለት ደግሞ በአጭር አገላለጽ በኢትዮጵያ ዉስጥ አማራዉን የሚያገል የአፓርታይድ የፖለቲካ ዘይቤ ያለዉ ስርዓት መገንባት ማለት ነዉ። አማራ-ጠሉ ስርዓት ይህን አፓርታይዳዊ አስተዳደሩን በአማራ ህዝብ ላይ የሚጭንበት ሶስት መንገዶች አሉት፡-

1.አማራዉን በፌደራል ደረጃ ጠንካራ ስልጣን (Hard Power) ያስጨብጣሉ ከሚባሉ የስልጣን ቦታዎች ማግለል ነዉ።

2.አማራ በሚባለዉ ክልል የአማራ ህዝብን እዉነተኛ ፍላጎት የሚወክሉ ፖለቲከኞች ወደ ስልጣን እንዳይመጡ በማድረግ የአማራ-ጠሉ ስርዓት አስፈጻሚ ቅጥረኞችን ብቻ መሾም ነዉ።

3.የአማራ ክልል ከሚባለዉ ግዛት ዉጭም ባሉ አካባቢዎች የሚኖረዉ በርካታ ቁጥር ያለዉ የአማራ ተወላጅ በሚኖርባቸዉ አካባቢዎች የፖለቲካ ዉክልና እንዳይኖረዉ ማድረግ ነዉ።

እነዚህን ሶስት መንገዶች ዘርዘር አድርጎ ማየቱ ጠቃሚ ስለሆነ ከመጀመሪያዉ እንጀምር፡፡ አማራዉ በፌደራል ስልጣን ላይ ትርጉም ያለዉ ተጽዕኖ መፍጠር በሚችልበት ጠንካራ የመንግስት ስልጣን (Hard Power) እንዳይኖር በማድረግ ግን ደግሞ በፌደራል የስልጣን ቦታዎች ላይ አልተወከለም እንዳይባል በሃገሪቱ ፖለቲካ ላይ እምብዛም ተጽዕኖ ማምጣት የማያስችል ስስ የመንግስት ስልጣን ( Soft Power ) እንዲይዝ ማድረግ ነዉ፡፡ የጠቅላይ ሚንስትርነት የስልጣን ቦታ፣የሃገር መከላከያ እና ደህንነት መስሪያ ቤቶችን ትርጉም ባለዉ መንገድ መምራት የሚያስችል ስልጣን የጨበጠ አካል ጠንካራ የመንግስት ስልጣንን ጨብጧል ማለት ይቻላል፡፡ በኢትዮጵያ የብሄር ፖለቲካ ዘይቤ ግን ከዚህም በጠበበ ሁኔታ የጠቅላይ ሚኒስቴርነቱን ስልጣን የተቆጣጠረ ሰዉ ህግ አዉጭዉንም ተርጓሚዉንም አስፈጻሚዉንም በመሃል እጅ አስገብቶ እንደፈለገ የማሾር ግለሰባዊ ጠንካራ ጡንቻ ይኖረዋል፡፡ በሌላ አባባል ሃገር ተጠቅልላ በግለሰብ መዳፍ ዉስጥ ትገባለች ማለት ነዉ፡፡ ስለዚህ የጠቅላይ ሚኒሰቴርነቱን ስልጣን እጅ ዉስጥ ያላስገባ አካል ትርጉም ያለዉ የፖለቲካ ህልዉና አለኝ ማለት አይችልም ማለት ነዉ፡፡ በሃገሪቱ ህገመንግስት በሶስቱ የመንግስት ክንፎች መሃከል የስልጣን ልይይት (Separation of Power) አለ ቢባልም በተግባር ግን ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን የያዘዉ ሰዉ ብቻ ሳይሆን ግለሰቡ የወጣበት ብሄር ልሂቃን ሳይቀሩ በሃገሪቱ ፖለቲካ ላይ የሚታይ የበላይነት እንደሚኖራቸዉ ብርሃነ ጽጋብ የተባለ የህወሃት የፖሊት ቢሮ አባል የነበረ ጸሃፊ "የኢህአዴግ የቁልቁለት ጉዞ" በሚል ርዕስ በጻፈዉ መጽሃፍ ተገልጿል:: በብርሃነ ገለጻ በህወሀት መራሹ ኢህአዴግ የቤታቤት ህግ የግንባሩ አባል ደርጅቶች ጠቅላይ ሚኒስትሩ የወጣበትን ፓርቲ ልሂቃን አቤት ወዴት ብለዉ ማገልገል እንዳለባቸዉ ሳይነገራቸዉ ያዉቃሉ፡፡ የኢህአዴግን ስህተቶች ሁሉ በአስከፊ መንገድ እየደገመ ያለዉ የብልጽግና ፓርቲም ከኢህአዴግ የተለየ የፖለቲካ ባህልም የፖለቲካ ማንነትም ያለዉ ፓርቲ አይደለም፡፡ ሁለቱም በስም የተለያዩ በመንፈስ አንድ የሆኑ የአማራ-ጠሉ ስርዓት መሪ ድርጅቶች(ህወሃትና ኦሮሞ ብልጽግና) አካሄድ መረዳት የሚቻልዉ የጠቅላይ ሚኒስተርነቱን ስፍራ ያልያዘ ሰዉም ሆነ ብሄር ትርጉም ያለዉ ስልጣን አለን ለማለት እንደማይችል ነዉ፡፡ ይህን ስለተረዱ ነበር የኦህዴድ መኳንንት እዉነተኛዉን የጠቅላይ ሚኒስተርነት ስልጣን ለመያዝ የተሟሟቱት፡፡

ኦህዴድ በለዉጥ አመራር ስም የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ ለመያዝ በሚቃትትበት ጊዜ ለዚህ ወሳኝ ወንበር በቅርብ ርቀት የነበሩት የአማራ ብሄር መኳንንት ወንበሩን ለመመኘት እንኳን ሳይሞክሩ ለኦህዴድ እያዘጋጁት ነበር፡፡

ይህ የሆነበት ዋነኛ ምክንያት የአማራ ወደ ስልጣን መምጣት "የነፍጠኛው ስርዓት ተመለሰ" የሚለዉን የዛገ ፕሮፓጋንዳ አምጥቶ ሃገርም ወንበርም የሚረጋጋበት ሁኔታ ስለማይኖር ወንበሩን አሳልፎ መስጠቱ አማራጭ የሌለዉ ነገር ነበር። ይህ በመደረጉ የአማራ ህዝብ ከሌላዉ ህዝብ የበለጠ ድጋፍን አሳየ እንጂ ምንም ቅሬታ አላሰማም። በአማራ ህዝብ በኩል የአቋም ለዉጥ የመጣዉ ኦሆዴድ መራሹ መንግስት ስልጣን በያዘ ማግስት የአማራን ህዝብ ሁለንተናዊ ህልዉና አደጋ ዉስጥ የሚጥሉ እጅግ አሳሳቢ እርምጃዎችን መወሰድ ሲጀምር ነዉ። እነዚህ እርምጃዎች የአማራን ህዝብ በብሄር ማንነቱ ነጥሎ በተለይ በኦሮሚያ ክልል ጭፍጨፋ ተገቢ ተግባር እስኪመስል ድረስ መንግስት በዝምታ የሚደግፈዉ መሆኑ ነዉ። በሌላኛዉ ጫፍ በኩል ደግሞ አማራ ወደ አዲስ አበባ እንዳይገባ የሚያደርገዉ ትእዛዝ በመንግስት ባለስልጣናት ኮራ ተብሎ የሚነገር ትእዛዝ እስከመሆን ደረሰ። እነዚህ ሁለት ሁነቶች የአማራ ህዝብ በኦሆዴድ/ኦሮሞ ብልጽግና የስልጣን ዘመን የደረሰበትን ከጄኖሳይድ እስከ አፓርታይድ የሚዘረጉ ማንነት ተኮር በደሎችን ያመቁ ክስተቶች ናቸዉ።

እነዚህን በደሎች በጣም በአጭር ጊዜ ዉስጥ በአሰቃቂ ሁኔታ ያስተናገደዉ የአማራ ህዝብ የተቃጣበትን ማንነት ተኮር ጥቃት ለመቀልበስ አማራጭ የሌለዉ ነገር ዋነኛ የስልጣን ቦታዎች ላይ እዉነተኛ ወኪሎችን ማስቀመጥ እንደሆነ ተገንዝቧል። የአማራ ህዝብ ትርጉም ያለዉ የፌደራል ስልጣንን ያለመ ትግል የማድረግ አቋም ላይ እንዲደርስ ያደረገዉ አማራ-ጠሉ ስርዓት ከትላንት እስከ ዛሬ እየመሩት ያሉ/የነበሩት ህወሃት/ኦነግ ብልጽግና የአማራ ህዝብ ጥቄዎችን ለመመለስ ቀርቶ ለማዳመጥ የማይፈልጉ፣የህዝብን ጥያቄ ህዝብ ከሚጠይቀዉ መንፈስ እጅግ በራቀ መንገድ አጣመዉ የሚተረጉሙ እና ከመንግስት በማይጠበቅ የወረደ መንገድ የአማራ ህዝብ ጥያቄዎችን የሚያጣጥሉ፣የአማራ ህዝብ መንግስት ናቸዉ ብሎ ጥያቄ ሲያቀርብላቸዉ "አልቅሱ ሶፍት እናቀርባለን" አይነት አሳፋሪ መልስ የሚሰጡ በመሆናቸዉ ነዉ። አማራ-ጠሉ ስርዓት(ህወሃት፣ኦሮሞ ብልጽግና) የአማራ ህዝብ ጥያቄዎችን የሚተረጉምበት ቀና ያልሆነ አተረጓጎም እንዴት ያለ እንደሆነ በሚቀጥለዉ ንዑስ ርዕስ የምናየዉ ይሆናል።

መሰረታዊ የህልዉና ጥያቄዎችን ለማስመለስ የአማራ ህዝብ ትርጉም ያለዉ የፌደራል ስልጣን ሊይዝ ይገባል ሲባል አሁንም አማራ በፌደራል ስልጣን ላይ በሙሉ ዉክልና ላይ ይገኛል ሲሉ እነ አቶ ተመስገን ጥሩነህ፣ አቶ ብናልፍ አንዱአለምን፣ አቶ መላኩ አለበልን ወዘተ በመጥቀስ ከእነዚህ ሰዎች የበለጠ አማራ ከየት ይመጣል? የሚል የአዉቆ አበድ ጥያቄ የሚጠየቅበት ጊዜ ብዙ ነዉ። ለዚህ ጥያቄ መልሱ የሚከተለዉ ነዉ። በአሁኑ ሰአት የአማራ ህዝብ ትግል ወሳኝ ምእራፍ ላይ ደርሷል። ይህ የትግል ምእራፍ የሚመራበት ወሳኝ መርህ ደግሞ "አማራ ነኝ የሚል ሁሉ ስልጣን ላይ ያለዉን አማራ ጠል ስርዓት መታገል እንጂ መቀላቀል የለበትም" የሚል ነዉ።ከላይ ስማቸዉ የተጠቀሱ ሰዎች እና መሰሎቻቸዉ ደግሞ ከጋሜ እስከ ሽበት አማራ-ጠሉን ስርዓት እያደገደጉ ሲያገለግሉ የኖሩ በመሆናቸዉ ( በዉልደት አማራ መሆናቸዉን ማንም ባይክድም) ከላይ በተጠቀሰዉ ጥብቅ መርህ እየተመራ ያለዉን ፋኖነት የሆነዉን የወቅቱን የአማራ ማንነት መወከል ግን አይችሉም።

ከፌደራሉ ስልጣን በመቀጠል አማራዉ የፖለቲካ ህልዉና ያጣዉ የራሱን ክልል አማራ ክልልን በማስተዳደሩ ረገድ ጭምር ነዉ። የአማራ ክልል በአማራ-ጠሉ ስርዓት አማራ ምስለኔዎች የሚተዳደርበት መንገድ ምን ያህል አስከፊ፣አሳዛኝና አሳፋሪ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለምና ወደ ዝርዝሩ መግባት አስፈላጊ አይደለም። ነገር ግን ክልሉ በአማራ አስተዳዳሪዎች የሚተዳደር እንደሆነ ጠቅሶ እንዴት አማራዉ ክልሉን ለማስተዳደር እንኳን የፖለቲካ ህልዉና የለዉም ይባላል የሚል የአዉቆ አበድ ጥያቄ እዚህም ላይ መነሳቱ ስለማይቀር ከላይ ለፌደራሉ የአማራ ባለስልጣናት የተሰጠዉ ምላሽ እዚህም ላይ የሚሰራ መሆኑን መጥቀስ ያስፈልጋል። የሚገርመዉ ነገር አዲስ አበባ ላይ ሆኖ አማራ ክልልን የሚያስተዳድሩ ምስለኔዎች ቀጥሮ የሚያሰራቸዉ የኦሮሞ ብልጽግና በነዚሁ ወኪሎቹ ላይ የሚያደርሰዉ ግራ መጋባት ሰዎቹ ለመታዘዝ ባቀዱት ልክ እንኳን እንዲታዘዙ የማያስችል ነዉ።

የአማራ ምስለኔዎችን በባህርዳር የሰየመዉ የኦሮሞ ብልጽግና እርሱ በሚያስተዳድረዉ በኦሮሚያ ክልል በተለይ በወለጋ ፈረንጆች እንኳን "አማሮች እንደ ዶሮ ታረዱ" ብለዉ እስኪጽፉ ድረስ ዓለምን ያስገረመዉ የዘር ፍጅት ያካሂዳል፣ ሲካሄድ መስማማቱን በዝምታ ይገልጻል።

በዚህ ሰአት የአማራ ህዝብ ለምን ወገኖቻችን በእናንተዉ ባልደረቦች ማድረግ ወይ አለማድረግ ያልቻሉ? ይህን ማስቆም ሳትችሉ እንዴት የአማራ መንግስት ነን ትላላችሁ? የሚል ምሬት ያሰማል፡፡ የኦሮሞ ብልጽግና አሰሪያቸዉ እንጂ ባልደረባቸዉ እንዳልሆነ የሚያዉቁት እነዚህ የአማራ አስተዳዳሪ ነን ባዮች አሳዳሪ ጌቶቻቸዉን አሻቅበዉ መናገር ስለማይችሉ ህዝቡን ያስቆጣዉን ዘር ማጥፋት ጋብ እንዲያደርጉላቸዉ ካባ በማልበስ ልምምጥ ያደርጋሉ፡፡ የኦሮሞ ብልጽግና ግን እንኳን ካባ ሰባት አክሊል ከሰማይ ቢወርድለት እንኳን ዋና የፖለቲካ ግቡ የሆነዉን አማራዉን እያሳደዱ መፍጀት/ማስፈጀት የሚያቆምበት የፖለቲካ ተፈጥሮ የለዉም፡፡ ስለዚህም ከካባ  ተገናፅፎም፣ከፎቶዉም በኋላም ሳይዉል ሳያድር የባሰዉን ያመጣዋል-አማራ የተባለ ወደ አዲስ አበባ ከተማ እንዳይገባ ብሎ በግልጽ አዉጆ መንገደኞችን ወደመጡበት ያስመልሳል፡፡ በዚህ ጊዜ የአማራ ብልጽግና መኳንንት መንግስት ነኝ ማለት ቀርቶ ሰዉ ነኝ ማለት ሳይከብዳቸዉ አልቀረም፡፡ እናም በተለይ የታችኛዉ አመራር የህዝብን ብሶት አንግቦ ከኦሮሞ ብልጽግና መኳንንት ጋር ፊት ለፊት መግጠም ጀመረ፡፡ ይሄኔ ካባ መልበስ የለመደዉ የኦሮሞ ብልጽግና መደናገጥ ጀመረዉ፡፡

ተደናግጦም ካባ በመሸለም ፋንታ የህዝቡን ጥያቄ አንስተዉ በእጅጉ የሞገቱ የአማራ መኳንንትን ከወንበራቸዉ ማንሳትና በከሃዲነት፣በአመጽ አጋጋይነት መክሰስ ጀመረ፡፡ እነዚህ የአማራ ብልጽግና ሰዎች የስልጣን ቆይታ እዚህ ጋር ያከትም ዘንድ ተፈጥሮአዊ ግዴታ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ለአማራ ህዝብ እየተከራከሩም በአማራ-ጠሉ ስርዓት ተሹሞ ወንበር ላይ መቀመጥም አይቻልም፡፡ አንዱን መምረጥ ግድ ነዉ! ወንበሩ ይቅርብኝ ያሉ የአማራ ብልጽግና መኳንንት መልካም እድልን መርጠዋል ሊደሰቱ ይገባል፤የአማራ ህዝብም ለትግሉ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ሊረሳዉ አይችልም፡፡ ሆኖም አብዛሃኞቹ ሲሄዱ የሚተኩ የአማራ መኳንንት አልታጡም፡፡ እነዚህ ታሪክ ይቅር የማይለዉ ስህተት ብቻ ሳይሆን ወንጀልም የሰሩ ናቸዉና በታሪክ መዝገብ በዚሁ ወንጀላቸዉ ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡

ከላይ በተዳሰሱት አማራዉ የፌደራል እና የራሱን ክልል ትርጉም ያለዉ ስልጣን ካጣባቸወዉ ሃቆች በተጨማሪ የፖለቲካ ህልዉና ጥያቄ የሚያነሳበት ሶስተኛዉ ነጥብ የአማራ ክልል ከሚባለዉ ግዛት ዉጭ የሚኖሩ አማሮች በሚኖሩበት አካባቢ ፖለቲካ ላይ ህልዉ ሆነዉ መብታቸዉን የሚያስከብሩበት ህልዉና የማግኘት መብት ነዉ፡፡

ከአማራ ክልል ዉጭ የሚኖሩ የአማራ ተወላጆች በሚኖሩበት አካባቢ የፖለቲካ ዉክልና የማግኘት መብት ጉዳይ በህይወት ከመኖር መብታቸዉ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ፣እጅግ አንገብጋቢ፣ለነገ የማይባል ጥያቄ ነዉ። እንደሚታወቀዉ ከአማራ ክልል ዉጭ የሚኖሩ የአማራ ብሄር ተወላጆች ሰባት ጉልበታቸዉ እየተቆጠረ በማንነታቸዉ ጭፍጨፋ ሲካሄድባቸዉ ሩብ ምዕተ-አመት አልፏል። በዚህ ረዥም ዘመን በአማራ ህዝብ ላይ ሲደርስ ለኖረዉ/አሁንም እየደረሰ ላለዉ የዘር ማጥፋት፣መፈናቀል፣መሳደድ ወንጀል በማንም ላይ ተጠያቂነት ሲቀርብ አልታየም። በእርግጥ አማራን መግደል ማፈናቀል በዚህ ስርዓት ዉስጥ ተጠያቂነትን እንዲያመጣ መጠበቅ ሞኝነት ነዉ። ስለዚህ ከአማራ ክልል ዉጭ በሚኖሩ አማሮች ላይ እየደረሰ ያለዉ ዘር ማጥፋትን የጨመረ ወንጀልን ለማስቆም አማራዉ ግብር በሚከፍልበት፣ለአካባቢዉ ልማት የበኩሉን ለሚያበረክትባት አካባቢ የፖለቲካ ዉክልና የሚያገኝበትን መንገድ የሚከፍት መንግስት ወደ ሃገሪቱ መንበረ ስልጣን መምጣት አለበት። እሳካሁን በታየዉ ተሞክሮ ደግሞ አማራዉ ራሱ ስልጣን ላይ ካልወጣ በስተቀር ችግሩን ሰምቶ የሚመልስለት ሌላ አካል እንደሌለ ተረጋግጧል።

አማራ ከሚባለዉ ክልል ዉጭ የሚኖሩ የአማራ ተወላጆች በሚኖሩበት አካባቢ የፖለቲካ ህልዉና ካገኙ በመንግስት የተለያዩ ክንፎች ማለትም ህግ-አዉጭ፣ አስፈጻሚዉ፣ ተርጓሚዉ የመንግስት አካል ዉስጥ ድምጻቸዉን የሚሰማ የሚያስተጋባና ለጥቅማቸዉ የሚቆም ወኪል ይኖራቸዋልና መብቶቻቸዉን አስከብረዉ ለሰዉ ልጅ ሁሉ በሚገባዉ ሰብአዊ ክብር ይኖራሉ ማለት ነዉ። አሁን ስልጣን ላይ ያለዉ አማራጠል የኦሮሞ ብልጽግና መራሽ መንግስት ግን ይህን አይፈልግም። አማራዉ በኦሮሚያ ክልል ፖለቲካ ዉስጥ ህልዉ እንዳይሆን፣ከክልል እስከ ወረዳ በተለያዩ ደረጃዎች ባሉ ምክር ቤቶች አማራዉ ወንበር እንዳያገኝ ለክልሎቹ ተወላጆች ተደራራቢ የኮታ ህግ እያወጣ በምክር ቤቶች የአማራ ዉክልና እንዳይኖር ወገቡን አጥብቆ ይሰራል። ኦሮሚያ ክልል የጀመረዉን ሌሎችን(በተለይ አማራን) የማግለል የአፓርታይድ ዘይቤ የቀድሞዉ የደቡብ ክልልም ይሰራበት ጀምሮ ነበር።በአጠቃላይ የአማራ ህዝብ እየታገለለት ያለዉ የፖለቲካ ህልዉና ጥያቄ በሃገሪቱ የፌደራል፣የአማራ ክልልና በሌሎች የሃገሪቱ ክልሎች ተገቢዉን የስልጣን ድርሻ አግኝቶ መብቱን ለማስከበር ነዉ።

## 8. ህገ-መንግስታዊ ህልዉና

የአንድ ሃገር ህዝብ ከሚያስተዳድረዉ መንግስት ጋር የሚኖረዉ መስተጋብር የሚቃኘዉ በህገ-መንግስት ነዉ። ህገ-መንግስት በህዝብና በመንግስት መካከል ያለዉን መስተጋብር መሃለኛ ሆኖ ሚዛን የሚያስጠብቅ የመግባቢያ ሰነድ ነዉ። ህገ-መንግስት ይህን ሚናዉን እንዲወጣ ህዝብም መንግስትም የመግባቢያ ሰነዳቸዉ ሆኖ ይተዳደሩበት ዘንድ ይሁንታቸዉን መስጠት አለባቸዉ።

ህዝብና መንግስት እኩል የተስማሙበት ህገ-መንግስት በአንድ ሃገር ዉስጥ እንዲኖር ዲሞክራሲያዊ ዘይቤ በሃገሪቱ ይሰፍን ዘንድ ግድ ነዉ። በሃገራችን ዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ የማስፈኑን ነገር ገና ዉሃም ያልሞቀ ነገር ስለሆነ በዲሞክራሲያዊ መንገድ፣በተገቢዉ የህዝብ ተሳትፎ የተጻፈ ህገ-መንግስት ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም። ሃገራችን እስካሁን በተራመደችበት የታሪክ ጉዞ ህገ-መንግስት የሚጻፈዉ በቀለም ሳይሆን በጠመንጃ ነዉ። ህገ-መንግስቱን ለማስጠበቅም ጠመንጃ ይመዘዛል እንጂ ህዝብና መንግስት ህገ-መንግስቱን እኩል የሚያስከብሩበት ሰዉኛ እድገት ገና አልመጣም። በመሆኑም አሁን ስራ ላይ ያለዉ ህገ-መንግስት ህዝቡ ሁሉ የተስማማበት እና የሚጠብቀዉ ሳይሆን መንግስት በጠመንጃ ፅፎት በዓፈበት ጠመንጃ የሚያስከብረዉ የሁከት ዶሴ እንጂ የመግባቢያ ሰነድ አይደለም።

በዚህ መንገድ የተፃፈ ህገ-መንግስት የመንግስትን እንጂ የህዝብን ፍላጎት አያንጸባርቅም። በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝብ በህገ-መንግስቱ ላይ የሚያነሳቸዉ በርካታ ጥያቄዎች አሉ። ሆኖም የአማራ ህዝብ ከመላዉ ኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ከሚያነሳዉ ጥያቄ በተጨማሪ እንደ ብሄር የሚያነሳቸዉ የእራሱ ጥያቄዎች አሉት። ስለ ህገ-መንግስት ጉዳይ ሲነሳ የአማራ ህዝብ ያለዉ ጥያቄ ከሌሎች ህዝቦች ጥያቄዎች ያልተለየ አድርጎ ለማቅረብ የሚደረገዉ የመንግስት የተለመደ ሸረኛ አካሄድ ወደ መፍትሄ የሚወስድ አይደለም።

የአማራ ህዝብ በማንነቱ ተለይቶ ህገ-መንግስቱን በማርቀቅ ሂደት ላይ ምንም አይነት ዉክልና እንዳይኖረዉ ሆን ተብሎ በተያዘ መንግስታዊ እቅድ መገለል ደርሶበታል።

አማራውን ለማግለል የታቀደዉ መንግስታዊ እቅድ የሚጀምረዉ በሽግግሩ ወቅት ከተደረጉ ወሳኝ ሃገራዊ መድረኮች በማግለል ነዉ። እነዚህ መድረኮች ሌሎች ኢትዮጵያዉያን ብሄሮች ልሂቃኖቻቸዉ በባትሪ እየተፈለጉ በተወከሉባቸዉ እንደ ሰላም ኮንፈረንስ፣የሽግግር ምክር ቤት፣የህገ-መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ምስረታ ያሉ መድረኮች ናቸዉ። በእነዚህ መድረኮች የተወሰኑ ዉሳኔዎች እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ በኢትዮጵያ የሚካሄደዉን ፖለቲካዊ ጉዳዮች የሚበይኑ ታላቅ ዉሳኔዎች ናቸዉ። አማራዉ ሆን ተብሎ በእነዚህ መድረኮች እንዳይሳተፍ በመደረጉ በሃገሩ ፖለቲካ ላይ መጻተኛ ሆኖ እየኖረ ነዉ። የሽግግሩን ዘመን ይዘዉሩ የነበሩ ባለጠመንጃ ፖለቲከኞች አማራዉን ከሽግግር ዘመኑ የፖለቲካ ትእይንት ሁሉ እንዲገለል ያደረጉት ወደፊት ሊገነቧት ያሰቧት ኢትዮጵያ አማራዉን ለመቅጣት የተመቸች እንድትሆን አርቀዉ ስላሰቡ ነበር። በዚህ እቅድ መሰረት ነዉ ህገ-መንግስቱ የተጻፈዉ።

ህገ-መንግስቱ በአንቀፅ ደረጃ ስለ አማራ ህዝብ በግልጽ ያሰፈረዉ ነገር ባይኖርም የተጻፈበት መንፈስ አማራዉን ያገለለ ብቻ ሳይሆን በሃገሪቱ አማራ የሚባል ብሄር እንዳለ እንኳን አዉቆ የረሳ ነዉ። የህገ-መንግስቱ መንፈስ የአማራን ህዝብ ያስታወሰዉ የሃገሪቱን ብሄረሰቦች ታሪካዊ ግንኙነት "በማዛባት" አሉታዊ መንፈስ ነዉ። ህገ-መንግስቱ ያዘላቸዉ ቀጣይ አንቀፆች በአብዛኛዉ የተፃፉት ይህን "የተዛባ" የተባለ ግንኙነት "ለማስተካከል" ነዉ። የማስተካከሉ ሙከራ ደግሞ ግንኙነቱን "ሲያዛባ" ኖሯል ተብሎ በሌለበት ወንጀለኛ የተደረገዉን የአማራ ብሄር በመቅጣት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ የአማራ ህዝብ ያሳለፋቸዉ የመከራ አመታት ምስክር ናቸዉ።

በአጠቃላይ አሁን ሃገሪቱ እየተመራችበት ያለዉ ህገ-መንግስት የአማራ ህዝብ ችግሮች ሁሉ ምንጭ የሆነ፣ራሳቸዉን የአማራ ጠላት ባደረጉ የፖለቲካ ልሂቃን ጉባኤ የተፃፈ የበቀል ደብዳቤ ነዉ። በመሆኑም አማራዉ በዚህ ሰነድ እንዲገዛ የሚገደድበት የህግም፣የሞራልም፣የፖለቲካም ምክንያት የለም። የአማራ ህዝብ ትግል አንዱ አጀንዳ ህገ-መንግስታዊ ዉክልናን እዉን የማድረግ የሆነዉም ለዚህ ነዉ።

## 2.1.2 የአማራ ህዝብ የፍትህ ርትዕ ጥያቄዎች

ፍትህ ርትዕ የሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ በህግና በሌሎች የማህበራዊ ዘርፍ ጥናቶች የሚሰጠዉ ሙያዊ ትርጉም እንዳለ የሚታወቅ ነዉ፡፡ በዚህ ሰነድ ሁኔታ ግን የፍትህ ርትዕ ጥያቄ የሚለዉ ሃሳብ የተሰጠዉ ትርጓሜ የአማራ ህዝብ በብሄር ማንነቱ ተለይቶ በሚሰነዘርበት ሁለንተናዊ በደል እና ጥቃት ሳቢያ የደረሰበትን ሁለንተናዊ ጉዳት የመናገር፣የመደመጥ እና መፍትሄ የማግኘት መብቱን በአማራ-ጠሉ ስርዓት መነጠቁን ለመግለጽ ነዉ፡፡ የአማራ ህዝብ በዚህ ሰነድ ቀደም ብለዉ የተጠቀሱ እጅግ አሳሳቢ የህልዉና አደጋዎችን እያስተናገደ ያለ ህዝብ ነዉ፡፡ ዘር ማጥፋትን የጨመሩ እነዚህ የህልዉና አደጋዎች የአማራ ብሄርተኝነት አንግቧቸዉ የተነሱትን ጥያቄዎች ፈጥረዋል፡፡ የአማራ ህዝብ ከህልዉና አደጋዎቹ የሚመነጩ ብሄር ተኮር ጥያቄዎች እንዳሉት ቀድመዉ ተረድተዉ፣እነዚህን ጥያቄዎች ያስተጋቡ እንደ ፕ/ር አስራት ወልደየስ ያሉ የአማራ ህዝብ ጠበቆች ካጋጠሟቸዉ ተግዳሮቶች ዋነኛዉ በአማራ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለዉን አሰቃቂ በደል የማስረዳት እና የመደመጥ መብታቸዉን መነፈግ ነዉ፡፡

አማራ-ጠሉ ስርዓት አማራዉ እየደረሰበት ያለዉን አሰቃቂ በደል እንዳይናገር እና እንዳይደመጥ የሚያደርግበት ስልቱ አማራዉ እንደተበደለ እንኳን ሳይታወቅለት በሽፍን እንዲያልቅ አድርጓል፡፡ በመሆኑም ስርዓቱ በጥላቻዉ መጠን የአማራን ህዝብ ለመቅጣት በሚያስችል የበደል እና የእልቂት አዙሪት ዉስጥ ለሰላሳ አመታት ለማቆየት አስችሎታል፡፡ ይህ ስልት ለአማራ-ጠሉ ስርዓት እንደ ፖለቲካ ድል የሚቆጠር ሲሆን ለአማራ ህዝብ ደግሞ የአንገት መድፋቱ ማስረጃ ነዉ፡፡ አማራ-ጠሉ ስርዓት አማራዉ የሚደርስበትን በደል እንዳይናገር እና እንዳይደመጥ አድርጎ የሚፈጅበት፣የሚያሳድድበት እና የሚገድልበት ስልት አንድን ህዝብ ጠላቴ ብለዉ ፈርጀዉ መንግስታዊ የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚፈፅሙ መንግስታት ሁሉ የጋራ ስልት ባህሪ ነዉ፡፡

አንድን ህዝብ በማንነቱ ነጥሎ ዘር ማጥፋት፣ማፈናቀል እና ማሳደድ በዓለም ላይ እጅግ የተወገዘ እና ከባድ ቅጣት ሊያመጣ የሚችል ወንጀል ነዉ፡፡ በዲፕሎማሲዉ ረገድም ቢሆን የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚሰሩ መንግስታት ለወዳጅነት የማይፈለጉ ናቸዉ፡፡

ስለዚህ የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚሰሩ መንግስታት በሃገራቸዉ የሚሰሩት ወንጀል በልኩ እንዲገለፅ አይፈልጉም። ወንጀሉን የሚያጋልጡ ፖለቲከኞች፣የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች እና ጋዜጠኞችን ያሳድዳሉ፣ያስራሉ፣ያስገድላሉ። አሰቃቂ የሰብአዊ መብት ጥሰት ቀድመዉ ያጋለጡት ፕ/ር አስራት ወልደየስ እስራቱንም፣መሳደዱን ሞቱንም ያስተናገዱት ለዚሁ ነዉ። ይህ ልማድ የዘር ማጥፋትን እንደ ፖለቲካ ዘይቤ የሚጠቀሙ መንግስታት ሁሉ ባህሪ ነዉ። ሆኖም በመረጃ ዘመን መንግስታዊ የዘር ማጥፋቱን ለማስቀጠል ሌላ ዘዴ ያመጣሉ። ይኸዉም በሃገራቸዉ እየተደረገ ያለዉ የዘር ማጥፋት አይደለም ሲሉ ይክዱና ለወንጀላቸዉ ሌላ ስም ያወጡለታል።

በአረመኔነቱ ዓለምን ሁሉ ያስደነገጠዉን የሩዋንዳ ዘር ማጥፋት የመራዉ መንግስት በወቅቱ በሃገሪቱ የነበረዉ የእርስ በእርስ ጦርነት እንጂ የዘር ማጥፋት እንዳልሆነ አይኑን በጨዉ አጥቦ ይከራከር ነበር። እዉነታዉ ግን ሌላ ነበር። በእርግጥ በወቅቱ በሩዋንዳ የእርስ በእርስ ጦርነት ነበር። ጦርነቱ ይካሄድ የነበረዉ ፓልካጋሜ በሚመሩት " Rwanda Patriot Front (RPF)" እና በወቅቱ ሩዋንዳን በሚመራዉ የዘር ማጥፋት መንግስት መካከል በቡሩንዲ ጠረፍ አካባቢ ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከጦርነቱ ጎን ለጎን በሩዋንዳ ዋና ከተማ ኪጋሊ ሳይቀር በመላዉ ሩዋንዳ ያልታጠቁ ሰላማዊ ቱትሲዎችን በቆንጨራ የመፍጀት አረመኔያዊ የዘር ማጥፋት ወንጀልም በመንግስት መሪነት ይካሄድ ነበር። በዚህ የጭካኔ ትእይንት ህጻናት፣ሴቶች፣አረጋዉያን ሁሉ ቱትሲ ሆነዉ እስከተገኙ ድረስ እንደ ቲማቲም በቆንጨራ ይቀጠቀጡ ነበር። ይህን አርመኔያዊ ወንጀል እየመራ የነበረዉ መንግስት ታዲያ ይህን ስራዉን ከእርስ በእርስ ጦርነት ጋር አዳብሎ በመጥራት ያደናቁር ነበር።

በተመሳሳይ ከጀርመን አልፎ በመላዉ አዉሮፓና እስያ የሚኖሩ አይሁዶችን እያደነ ሲፈጅ የነበረዉ የጀርመኑ የዘር ማጥፋት (የናዚ) መንግስት የፈጸመዉ ወንጀል የጀርመን ብሄርተኝነትን ማስጠበቅ እንጂ የዘር ማጥፋት እንዳልነበር አይኑን በጨዉ አጥቦ ይከራከር ነበር። አሁን ባለንበት ዘመን በሩሄንጂያ ሙስሊሞች ላይ ዘር ማጥፋት፣ ማፍናቀል፣ ማሳደዱን እያኸጎደጎደ የሚገኘዉ የቀድሞዋ በርማ መንግስት እየፈጸመ ያለዉ የዘር ማጥፋት እንደሆነ አምኖ አያወቅም።

በሃገራችን በአማራ ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለዉ የዘር ማጥፋት መንግስታዊ ወንጀል ከላይ ለምሳሌ ከቀረቡት ሶስት ሃገራት ተሞክሮዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ፣የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጻሚ መንግስታት ባህሪ ነዉ። ሆኖም የእኛን ሁኔታ ለየት የሚያደርገዉ ዘር ማጥፋትን የጨመረዉን መንግስታዊ ወንጀል ለመካድ፣ለመሸፋፈን የአማራዉ ልሂቅም ከፍተኛ ሚና ሲጫወት የኖረ መሆኑ ነዉ።

የአማራ ህዝብ በአማራ-ጠሉ ስርዓት የሚደርስበት በደል በየጊዜዉ እየጨመረ፣ በየዓይነቱ እየከፋ የሚሄድ ሆኖ ሳለ ይህንኑ በደል በአደባባይ የመናገርና የመደመጥ መብቱን የተነፈገበት ስልት የአማራ ህዝብን ፍትህ ርትዕ እንዳያገኝ፣ በበደል አዙሪት፣ በጥቃት ሰንሰለት ዉስጥ እንዲኖር አስገድዶታል። በዚህ ሰነድ የአማራ ህዝብ ፍትህ ርትዕ አጥቷል ሲባል የአማራ ህዝብ ለሶስት አስርት አመታት በአስከፊ ብሄር ተኮር በደል ዉስጥ ማለፉ ሳያንስ በደሉን የሚያስቆምለት ቀርቶ በደሉን የሚያዳምጠዉ ጆሮ ማጣቱን ለማመልከት ነዉ። ፍትህ ለማግኘት መደመጥ ቀዳሚዉ ነገር ነዉ። ማንኛዉም ተበደልኩ የሚል አካል ፍትህ ፍለጋ ወደ ፍርድ ቤት ሲሄድ ፍትህ ሊሰጡ ከተቀመጡ ዳኞች ሊያገኘዉ የሚገባዉ ቀዳሚዉ ነገር መደመጥ ነዉ። ይህን ወደ አማራ ህዝብ ስናመጣዉ ህዝቡ ከሰላሳ አመታት በላይ በበደል አዙሪት ዉስጥ እየተንከራተተ መድረሻ ማጣቱ ጉልህ ሃቅ ሆኖ ሳለ ይህን በደሉን የሚናገርበት መድረክም፣አድማጭ ጆሮም የተነፈገ ህዝብ ነዉ። በገዛ ሃገሩ በደሉን መናገርና መደመጥ የተነፈገ ህዝብ ያለዉ ብቸኛ አማራጭ ፍትህ የነፈገዉን ስርዓት መታገል ነዉ። የአማራ ህዝብ አሁን እያደረገ ያለዉ ይህንኑ ነዉ።

ለዘመናት ስርዓቱ የሚያደርስበትን ሞት፣መሰደድ፣መፈናቀል፣መገለል ሁሉ ለኢትዮጵያ ሲል ታግሶ የኖረዉ የአማራ ህዝብ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ እንዲደርስ ያደረገዉ መበደሉ ብቻ ሳይሆን በደሉን ለመናገር እና ለመደመጥ እንኳን አለመቻሉ ነዉ። የአማራ ህዝብ በደል የወለዳቸዉን ጥያቄዎቹን በሰላማዊ መንገድ ሲያቀርብ ከማድመጥ ይልቅ ሲሳለቅ የነበረዉ ብዙ ነዉ። በተለይ አማራ-ጠሉ ስርዓት በአማራ ህዝብ ላይ የሚፈጽመዉን ጭካኔ የሚነዳዉ በደል ከህገ-ግስታዊነትና ህዝባዊ መንግስትነት ይቆጥረዋል።

ስለሆነም የአማራ ህዝብ እየተጎነጨዉ ያለዉን መራራ የበደል ጽዋ ለማስወገድ የሚያደርገዉን ፍትሃዊ ህዝባዊ ትግል ህግ-መንግስታዊ ስርዓትን በሃይል ለመናድ የሚደረግ ተራ ዉንብድና አድርጎ ለማቅረብ ሲቪል እና መለዮ ለባሽ ካድሬዎቹን አሰማርቶ የአማራን ህዝብ የሚዘልፍ ፕሮፓጋንዳ እንዲደለቁ ያደርጋል፡፡

አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራ ህዝብ ጥያቄዎችን ላለማድመጥ ከሚከተላቸዉ ስልቶች መካከል የሚከተሉት ዋነኞቹ ናቸዉ፡፡

## 1.በዝምታ ማለፍ

አማራ-ጠሉ ስርዓት በአማራ ህዝብ ላይ የሚያደርሰዉን በደል አስመልክቶ የሚቀርብለትን የፍትህ ርትዕ ጥያቄ በዝምታ የሚያልፈዉ የስርዓቱ ቀዳሚ የፖለቲካ አላማ አማራዉን መቅጣት ስለሆነ ነዉ፡፡ ስርዓቱ ጥፋተኛ ጠላት አድርጎ በፈረጀዉ የአማራ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለዉን ወንጀል ራሱ ስርዓቱ ዳኛ ሆኖ በተቀመጠበት ሁኔታ አማራን የሚታደግ ስራ ሊሰራ አይችልም፡፡ ስለዚህ በአማራ-ጠሉ ስርዓት ዉስጥ የአማራዉ መቀጣት በዝምታ የሚታለፍ ብቻ ሳይሆን እንደ ፖለቲካ ስኬት የሚቆጠር ነዉ፡፡ የአማራ ብሄርተኝነት አድጎ አማራዉን የመታደግ ጥንካሬ ላይ ሳይደርስ ዘመናት መንጎዳቸዉ ስርዓቱ በአማራ ህዝብ ላይ የሚያደርሰዉን በደል በአመርቂ ሁኔታ እንዲፈጽም ረድቶታል፡፡

አማራ-ጠሉ ስርዓት በከፍተኛ ንቃት የአማራን ብሄርተኝነትን የማሳደዱን እርምጃ ለዘመናት ማካሄዱ እና በአማራዉ ልሂቅ በኩልም የአማራ ህዝብ ጥያቄዎችን ነቅሶ በማዉጣት ረገድ ዉስንነት መኖሩ ተደማምሮ የአማራ ብሄርተኝነት በሚፈለገዉ ደረጃ/ፍጥነት/ እንዳያድግ ምክንያት ሆነዋል፡፡ በመሆኑም የአማራ ህዝብ ሞት፣እንግልት የማንንም ጆሮ ሳይስብ፣የማንንም ልብ ሳያስደነግጥ እንደተገቢ ነገር ተቆጥሮ በዝምታና በሽፍን ለዘመናት ያለማቋረጥ ተካሂዷል፡፡

## 2. መካድ

የአማራ ብሄርተኝነት ላለፉት አምስት አመታት ያስመዘገበዉን ፈጣን እድገት/ስኬት/ተከትሎ የአማራዉን በደል በዝምታ የማሳለጡ የስርዓቱ ዘይቤ እንደወትሮዉ ቀላል ሊሆንለት አይችልም፡፡ የአማራ ብሄርተኝነት ማደግ በርካታ የአማራ የሲቪክ ማህበራት በመፈጠራቸዉ፣ስለአማራዉ በደል በትኩረት የሚዘግቡ ሚዲያዎች በመቋቋማቸዉ፣ ስለአማራዉ መብት የሚሞግቱ ግለሰቦች ብቅ ብቅ በማለታቸዉ ሁሉ ይገልጻል፡፡ የላይኛዉ አመራር የፈጠረዉ ችግር እያደገ ባለዉ የአማራ ብሄርተኝነት ላይ መጥፎ ጥላ ማጥላቱ ባይካድም የአብን መፈጠርም ለአማራ ብሄርተኝነት ማደግ የማይናቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ የፓርቲዉ ሰፊዉ አባል እና የታችኛዉ መዋቅር የአማራ ብሄርተኝነት ካምፕ ጉልህነት እንዲኖረዉ የራሱ የሆነ ሚና ነበረዉ፡፡የእነዚህ አዳዲስ ክስተቶች ድምር ዉጤት የአማራን ህዝብ በደል በዝምታ የማለፉን የፀረ-አማራዉን ስርዓት የምቾት ዞን ነቅንቆታል፡፡

ስለሆነም ስርዓቱ በዝምታዉ ፋንታ ክህደት ጀመረ፡፡ የስርዓቱ ክህደት የአማራ ህዝብ ከሌላዉ የሃገሪቱ ህዝቦች የተለየ የደረሰበት በደል የለም፣ የተዘረጋዉ ስርዓት አማራዉንም የሃገር ባለቤት ያደረገ ነዉ የሚል ነዉ፡፡ ሌላዉ የስርዓቱ አስገራሚ ክህደት የሚገለጽበት አባባል "አማራዉ ተበደልኩ የሚለዉ የበላይነትን ስለለመደ እኩልነት በደል መስሎ ስለሚታየዉ ነዉ" የሚለዉ አባባል ነዉ፡፡ በዚህ አባባል ዉስጥ ያለዉን ጭካኔ፣ ጥላቻ፣ ፍርደ ገምድልነት ለማብራራት ራሱ አስቸጋሪ ነዉ፡፡ በጥቅሉ ግን በበደኖ፣ በአርባጉጉ፣ በአሶሳ፣ በመተከል፣ በወልቃይት ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ሁመራ፣ ጉራፈርዳ፣ አርሲ፣ ቤንሻንጉል፣ አጣዬ፣ ደራ የሚደረገዉ የአማራ ሞት፣ እንግልት፣ ስደት  የእኩልነት ማሳያ አለመሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለም፡፡

የዘር ማጥፋትን ወንጀል እንደ ፖለቲካዊ ዘይቤ የሚጠቀሙ መንግስታት ወንጀላቸዉን ሸምጥጠዉ መካዳቸዉ ወንጀሉን ለመቀጠል ፍላጎት እንዳላቸዉ ዋነኛዉ ምልክት ነዉ፡፡ ስለዚህ የአማራ-ጠሉ ስርዓት ክህደት የአማራ ህዝብ በደል እንደሚቀጥል ማሳያ ነዉ፡፡ ስርዓቱ በክህደቱ እየባሰበት የሚሄደዉ በአማራ ህዝብ ላይ ወንጀል ሳይፈጽም መኖር ስለማይችል ነዉ፡፡

## 3. ማድበስበስ

የአማራ ብሄርተኝነት ማደግ አማራ-ጠሉ ስርዓትና ተከታዮቹ በአማራዉ ላይ የሚያደርሱትን በደል ለመካድም በዝምታ ማለፍም አላስችል በማለቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስርዓቱ ከዝምታና ከመካድ ጎን ለጎን በተድበሰበሰ ሁኔታ ስለ በደሉ ለመግለጽ እየተገደደ መጥቷል። የማድበስበሱ ስልት በዉጤቱ ከመካዱና በዝምታ ከማለፉ ስልት የተለየ ነገር የለዉም። የአማራን ህዝብ በደል ለማድበስበስ ስርዓቱ ከሚጠቀምባቸዉ ስልቶች ዋነኛዉ ሞትና መፈናቀል መኖሩን በማመን ይጀምርና የሞቱት እና የተፈናቀሉት ግን አማሮች በማንነታቸዉ ተለይተዉ ሳይሆን ሁሉም ኢትዮጵያዉያን የተጎዱ መሆናቸዉን ለማስረዳት ይወተዉታል። አክሎም "ንጹሃን"፣"ዜጎች"፣ "ኢትዮጵያዉያን" ሲል የገለጻቸዉ ተጎጅዎች እንዲጎዱ ያደረገዉ አጋጣሚ የተፈጠረዉ ድንገተኛ ጠብ፣የመጠጥ ቤት ግጭት፣ጎጂ ባህላዊ ልማዳዊ ድርጊት አይነት ከብሄር ፖለቲካዉ አማራ-ጠል አጀንዳ ጋር እንደማይገናኝ ለማስረዳት ይሟሟታል።

የስርዓቱ የማድበስበስ ስልት የአማራ ህዝብ በዚህ ስርዓት ዉስጥ ፍትህ የማግኘት አንዳች እንጥፋጣፊ እድል እንደሌለዉ ግልጽ ያደረገ፣አማራዉንም በእጅጉ ተስፋ ያስቆረጠ ነገር ነዉ። ስለሆነም አማራዉ ጥያቄዎቹን አስመልሶ ፍትህ ርትዕ ማግኘት የሚችልበት ብቸኛዉ መንገድ ፍትህ ያሳጣዉን ስርዓት እንደ ህዝብ በጋራ ቆሞ መታገል ሲችል እንደሆነ ተግባብቶ ትግሉን አፋፍሟል።በደል እኩልነት የሚመስለዉ የጥላቻዉ ፖለቲካ መሪዎችም ለመብቱ የሚታገለዉን ህዝብ በመንግስት ገልባጭነት በመከሰሱ ዘልቀዉበታል።

## 4- ማስቀየስ

አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራ ህዝብ የደረሰበትን በደል በአደባባይ ተናግሮና ተደምጦ ተገቢዉን ፍትህ ርትዕ እንዳያገኝ ከሚያደርጉበት መንገድ እጅግ አደገኛዉ ለህዝብ ጥያቄዎች ያልተገባ ትርጉም በመስጠት የሚያስቀይስበት ዘዴዉ ነዉ። ይህ ዘዴ የአማራ-ጠሉ ጎራ ወደ ስልጣን ሲገሰግስ አማራዉን የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ሁሉ ብሄራዊ ጠላት አድርጎ ያቀረበበት የፖለቲካ ማጠንጠኛዉ ነጸብራቅ ነዉ።

ስርዓቱ ስልጣን ላይ ሲመጣ አማራ የሌሎችን ብሄረሰቦች እኩልነት የማይቀበል ጨቋኝ፣ ፀረ-ህብረብሄራዊ፣ ጨፍላቂ ወዘተ መሆኑን እያስረዳ ነበር። አማራው እንዲህ ያለ ምስል ተሰጥቶት ለሰላሳ አመታት እና ከዚያ በላይ በመቆየቱ ምክንያት የሚፈጸምበትን መንግስት-መር ወንጀል ለመናገር እና ለመደመጥ የሚችልበት ቀዳዳ አጥቶ ኖሯል።

የአማራውን በደል በመስማት ፈንታ አማራው የሚጮኸው ተበድሎ ሳይሆን ሌሎችን የሚጨፈልቅበትን ስልጣኑን በብሄረሰቦች ትግል ስለተነጠቀ ነው። ስልጣኑን በሃይል ለመመለስ እና የድሮውን ስርዓት በመዘርጋት ብሄረሰቦችን ለመጨቆን አቅዶ ነው ሲል በሞት ጥላ ስር እያለፈ ያለውን ህዝብ የህልውና ጥያቄ አጣሞ ያቀርባል። ስርዓቱ አክሎም የአማራ ህዝብ ጥያቄ አሃዳዊነትን በማምጣት ብሄረሰቦች በትግላቸው ያመጡትን የብሄረሰቦች እኩልነት በአማራ የበላይነት ለመተካት የታለመ እንደሆነ ይሰብካል። ይህ የስርዓቱ ፕሮፓጋንዳ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ሁሉ የአማራን ህዝብ ትግል እንዲፈሩና የህዝቡን እዉነተኛ የፍትህ ጥያቄዎች በተጠየቁበት መንፈስ መረዳ እንዳይችል ያደርጋል።

በመሆኑም የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች ማዳፈን የሌሎችን ብሄረሰቦች የእኩልነት መብት ከማስከበር ጋር የተቆራኘ ነገር እንዲመስል ሆኗል። በሌላ አባባል የአማራ ህዝብ ፍትህ ማግኘትና የሌሎች ብሄረሰቦች መብት መከበር አብረው የማይሄዱ ተቃራኒ (Mutually Exclusive) ነገሮች ሆነው ቀርበዋል። በመሆኑም የሌሎች ብሄረሰቦች መብት መከበሩ የሚረጋገጠው የአማራ ህዝብ መብት ሲነጠቅ ፣የመደመጥ መብቱንም ሲነፈግ ነው የሚል አደገኛ ግንዛቤ በሃገራችን ፖለቲካ ላይ በጉልህ ሰፍኗል። ይህን ግፈኛ አቋም ለመቀልበስ አማራው እንደ ብቸኛ መፍትሄ የወሰደው ለዘመናት በሰላም ብቻ ሳይሆን በልመናና ልምምጥ ሲጠይቀው የኖረውን መብቱን በመራራ ትግሉ የማስከበር አማራጭ ነው።

ህዝባዊ ትግልን እንደ መፍትሄ አድርጎ የተነሳው የአማራ ህዝብ እየሄደበት ያለው መንገድ እስከአሁን ከኖረበት የልመናና የልልምጥ መንገድ የተሻለው መንገድ ነው። ለዚህ አስረጅ የሚሆኑ ሁነቶች በሃገራችን ፖለቲካ እየታዩ ነው።

ከእነዚህ ሁነቶች አንደኛዉ የአማራ ጠሉ ጎራ የምሁራን ለወትሮዉ የአማራን ህዝብ ትግል ሲያጣጥሉ፣የፋኖን ስም ሲያጠለሹ ከኖሩበት ልማድ ወጥተዉ የአማራ ህዝብ ፍትሃዊ ጥያቄዎችን አንግቦ የተነሳ እንደሆነ ቢያንስ በአፋቸዉ መመስከር ላይ መድረሳቸዉ ነዉ። በተመሳሳይ በአማራ ህዝብ ጥያቄዎች ላይ ጆሮዉን ደፍኖ ሲያደናቁር፣ ሲክድ፣ ሲያድበሰብስ እና ሲያስቀይስ የባጀዉ ኦሮሞ ብልጽግና መራሹ ስርዓት የአማራ ህዝብ ትግል የማይቀለበስበት ደረጃ ላይ መድረሱን ሲረዳ ከአማራ ታጋዮች እና ልሂቃን ጋር በሰላም ለመነጋገር ፍቃደኛ መሆኑን በነጋ በጠባ እየወተወተ ይገኛል። እነዚህ አዳዲስ ነገሮች ከአማራ-ጠሉ ጎራ መምጣታቸዉ የአማራ ህዝብ መብቱን በትግሉ ለማስከበር የተያያዘዉ መንገድ ትክክለኛ መሆኑን ፍንጭ የሚሰጡ ናቸዉ። ሆኖም ከአማራ-ጠሉ ጎራ የሚመጣዉን ማንኛዉንም በጎ መሳይ መንገድ ሁሉ አማራዉ በከፍተኛ ጥንቃቄ (ጥርጣሬ) ማየት አለበት። ከዚህ ቀደም ይኸዉ ስርዓት አማራዉን ቁማር እንደበላዉ ያወራበት መንገድ የማስጠንቀቂያ ደዉል ሊሆን ይገባል።

የአማራ ህዝብ ጥያቄዎችን ከትክክለኛ ተፈጥሮአቸዉ ወደ ሌላ አቅጣጫ በማጣመሙ በኩል አሁን ክልሉን እየመራ ያለዉ፣እንደ ኦሮሞ ብልጽግና የሚቃጣዉ የአማራ ክልል መንግስት ቀላል የማይባል ሚና እየተጫወተ ይገኛል። የዚህ መንግስት አመራሮች በተለይ የባህር ዳር ከንቲባ፣የጎንደር ከንቲባ፣ርዕሰ መስተዳደሩና ምክትሎቹ በኢቲቪ ብቅ እያሉ የአማራ ህዝብ ጥያቄዎችን በማጣመሙ በኩል ከኦሮሞ ብልጽግና መኳንንት እንደሚበልጡ ለማሳየት ይሟሟታሉ። እነዚህ አስገራሚ ሰዎች ከአማራ ህዝብ ጥያቄዎች ቀዳሚዉ የአመራሩ የህዝብ አገልጋይ አለመሆን ስለነበረ አሁን ደግሞ እነሱን የመሰለ የህዝብ አገልጋይ አመራር ወደ ስልጣን እንደመጣ ሲናገሩ ሃፍረት ሺዉ ሳይላቸዉ ነዉ። ከኢህዴን እስከ አማራ ብልጽግና ክልሉን የሚመሩ መሪዎች የህዝብ አገልጋይ አለመሆናቸዉን የአማራ ህዝብ በአንድ ድምጽ የሚመሰክረዉ ነዉ። ይህ ማለት ግን የአማራ ህዝብ ሲፈልግ የባጀዉ አረጋ ከበደን እና ካቢኔዉን የመሰሉ መሪዎችን ነበር ማለት አይደለም፣የህዝብ አገልጋይ አመራር መፈለግ ማለት ወደ ኦሮሞ ብልጽግናነት የተቀየሩ መሪዎችን በባህር ዳር ጎልቱልኝ ማለት አይደለም።

ኦሮሞ ብልጽግናን እያስናቁ ያሉት የአማራ ክልል መሪዎች እንደሚደሰኩሩት ሁለተኛዉ የአማራ ህዝብ ጥያቄ የኑሮ ዉድነት ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህን ጥያቄ ለመመለስ አከራዮች የቤት ኪራይ እንዳይጨምሩና ተከራይ እንዳያስወጡ አድርገናል፤ በተጨማሪም የሸማች ማህበራትን ለማቋቋምና ለማጠናከር ስልሳ ሚሊዮን ብር መድበናል፣ ስለዚህ የአማራ ህዝብ ጥያቄዎች እየመለስን ክልሉንም እያረጋጋን ነዉ ይላሉ፡፡ የሚገርመዉ ነገር የባህርዳር ከንቲባ ይህን ዲስኩራቸዉን በኢቲቪ በሚያስሙበት ደቂቃ የሃገሪቱ ፓርላማ የአማራ ክልል ለስድስት ወራት የቆየበትን የአስኳቸይ ጊዜ አዋጅ ለአራት ወር እንዲያራዝም ዉሳኔ እያሳለፈ ነበር፡፡ እሳቸዉ እንደሚሉት ክልሉ የህዝብ አገልጋይ መሪዎችን ከሰየመና የህዝብ ጥያቄዎችን መልሶ ክልሉን ወደ መረጋጋት እየወሰደ ከሆነ  የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለምን ተራዘመ? የህዝብ አገልጋይ የተባሉት እርሳቸዉና አረጋ ከበደን የጨመረዉ አመራርስ መታጠቢያ ቤት ሳይቀር በመከላከያ ሰራዊት ታጅቦ የሚሄደዉ ለምንድን ነዉ? መልሱን ከእነዚህ ሰዎች መጠበቅ አይታሰብም፡፡

## አማራ-ጠሉ ስርዓት የአማራን ህዝብ የፍትህ ጥያቄዎች የሚያፍንባቸዉ ምክንያቶች

አማራ-ጠሉ ጎራ የተለያዩ መንገዶች በመጠቀም (በዝምታ፣ በክህደት፣ በማስቀየስ፣ በማጣጣም) የአማራ ህዝብን ጥያቄዎች መቀበል እንደማይፈልግ አረጋግጧል፡፡ ይህ የሆነበት በሶስት ዋነኛ ምክንያቶች ነዉ፡፡

## 1-የአማራ ህዝብን ጥያቄዎች መመለስ ራሱን ስርዓቱን ስለሚያጠፋዉ

በዚህ ሰነድ የመጀመሪያ ገጾች ላይ እንደተገለጸዉ የአማራ ህዝብ የሚያቀርባቸዉ ጥያቄዎች አማራ-ጠሉን ስርዓት ከስሩ የሚንዱ፣ ስርዓቱ የተመሰረተበት አማራ-ጠል እሳቤ ቀጥተኛ ተጻጻሪ ሃሳቦች(Anti Thesis) ስለሆኑ ስርዓቱ እነዚህን ጥያቄዎች መለሰ ማለት እራሱን አጠፋ ማለት ነዉ፡፡ በሌላ አባባል ከ1983ዓ.ም ወዲህ በሃገራችን በተመሰረተዉ የፖለቲካ ዘይቤ አማራ እና አማራ-ጠል ተብሎ በሁለት ፍጹም ተጻራሪ (Mutually Exclusive) እሳቤዎች የተከፈለ ነዉ፡፡

እነዚህ ተጻራሪ እሳቤዎች አብረዉ የማይቆሙ ብቻ ሳይሆኑ የአንዱ አሸናፊነት የሌላዉ ተሸናፊነት(መጥፋት) ሆኖ የሚተረጎምበት የተካረረ ቅራኔ ዉስጥ ያሉ ናቸዉ። ይህን በግልጽ የማይነገር የሃይል መስተጋብር አቶ ሌንጮ ለታ ከአንድ አመት አካባቢ በፊት በሰጡት ቃለ-ምልልስ በግልጽ አስቀምጠዉት ነበር።

በዚህ ቃለ-ምልልስ አቶ ሌንጮ ጠ/ሚ አብይ አህመድ ወደ ስልጣን እንደመጡ ሰሞን ኦሮሞ ያልደገፋቸዉ ለምን ነበር? የሚል መንፈስ ያለዉ ጥያቄ ሲቀርብላቸዉ የሰጡት መልስ "እኛ አብይን ወዲያዉ እንደመጣ ያልደገፍነዉ አማራ በጣም ስለደገፈዉ፣እነሱ የደገፉት ነገር ደግሞ ኢ-ዲሞክራሲያዊ ስለሆነና ለእኛ ስለማይበጅ ስለሆነ ነዉ።" ሲሉ እዉነተኛዉን የአማራ-ጠሉን ጎራ እሳቤ በቀጥተኛ ንግግር አስቀምጠዋል። አማራ-ጠሉ ስርዓት በአማራ ህዝብ ጥያቄዎች ላይ ፊቱን የሚያዞረዉ ለአማራ የሚበጅ ነገር ሁሉ ለኛ አይበጀንም፣ የአማራ ድል ሁሉ የኛ ሽንፈት ነዉ ከሚለዉ የደደረ ጥላቻ የወለደዉ እሳቤ የተነሳ ነዉ። ይህ አጠቃላይ እሳቤ ደግሞ አማራ-ጠሉ ስርዓት የቆመበት ዋነኛ አለት ነዉ። የአማራ ህዝብ የሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች ሌላዉን ኢትዮጵያዊ ሳይጎዱ አማራዉን የሚታደጉ ናቸዉ። ሆኖም ሌላዉን ባይጎዱ እንኳን አማራዉን እስከጠቀሙ ድረስ በአማራ-ጠሉ ጎራ በበጎ የሚታዩ አይደሉም።

የአማራ ህዝብ ጥያቄዎች አማራ-ጠሉ ስርዓት አማራዉን ሲያጠቃ የኖረበትን ፍላጻዎች ሁሉ የሚቀሙ ናቸዉ። አማራ-ጠሉ ስርዓት የተፈጠረዉ አማራዉን ለማጥቃት፣ለማሳደድና አንገት ለማስደፋት ስለሆነ ይህን የሚያደርግበትን የማጥቂያ ፍላጻዉን ከተቀማ ስርዓቱ የሚኖርበት ምክንያት አይኖረዉምና ይጠፋል። ስለዚህ የአማራ ህዝብ ጥያቄዎችን በመመለስ የመኖር ምክንያቱን የማጣት "አደገኛ" ተግባር አይፈጽምም። ስለዚህ የአማራ ህዝብን ጥያቄዎች ከመመለስ ይልቅ በዝምታ፣ በመካድ፣ በማድበስበስ፣ በማስቀየስና በማጣመም እድሜዉን ለማስረዘም ይሞክራል። እዉነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ስርዓቱ የአማራ ታጋዮች ጠመንጃ ከሚያነሱ ይልቅ ጥያቄያቸዉን በሰላማዊ መንገድ ቢያቀርቡ ለመመለስ ዝግጁ እንደሆነ ይወተዉታል። ይህን የሚለዉ የአማራ ህዝብ ጥያቄዎችን ራሱ በሚፈልገዉ መንገድ አጣሞ ተርጉሞ፣ላጣጣመዉ ጥያቄ በሚሰጠዉ መልስ አማራዉ ረክቶ እንዲቀመጥ ከመፈለግ አጉል ብልጣብልጥነት ስሌት ነዉ። ይህ አካሄድ ደግሞ በስርዓቱ አነጋገር (Convince and Confuse) ወይም ቁማር የመብላት ብልጠት ይተረጉማል።

## 2-የአማራ ህዝብ ጥያቄ የስልጣን ጥያቄ ስለሚመስለዉ

በብሄር ፖለቲካ ደንብ ስልጣን ለመያዝ ዋነኛዉ አስፈላጊ ነገር የተበድዬ ትርክትን ቀምሞ ማቅረብ ነዉ። በሃገራችን ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ስልጣን የያዘዉ አማራ-ጠሉ የብሄር ፖለቲካ ለስልጣን ያበቃዉ የተበድዬ ትርክቱን አጥብቆ በመያዙ ነዉ። በዚህ ተበድዬ ትርክት ዉስጥ በዳይ ሆኖ የቀረበዉ የአማራ ብሄር እንደሆነ የሚታወቅ ነዉ። አማራ-ጠሉ ስርዓት በዳይ ያለዉን የአማራ ብሄር የሚበቀልበት ጨካኝ ለበቅ ለአማራ ህዝብ ጥያቄዎች ዋነኛ ምንጭ ነዉ። አማራዉ በተጨባጭ የደረሰበትን በደል ጠቅሶ ለነጻነቱ የሚያደርገዉ ትግል በአማራ-ጠሉ ስርዓት የስልጣን ጥያቄ ተደርጎ ይተረጎማል።አማራ-ጠሉ ስርዓት ራሱ ስልጣን ላይ የወጣዉ እዉነቱንም ዉሸቱንም የደባለቀ የተበድዬ ትርክት እየሰበከ በመሆኑ የአማራ ህዝብም ተመሳሳዩን እያደረገ ይመስለዋል።በዚህ ላይ አማራ-ጠሉ ስርዓት በግልጽ "አማራ ወደ ስልጣን ድርሽ እንዳይል አደርጋለሁ" ሲል የሚናገር በመሆኑ የአማራን ህዝብ ጥያቄ መቀበልም ሆነ መመለስ አማራዉን ለስልጣን ማበጃጀት አድርጎ ይተረጉመዋል። ስለሆነም የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች ባለመቀበል ሁለት አላማዎችን ያሳካል-የአማራ ጠሉን ስርዓት ስልጣን ማስጠበቅ እና አማራዉን ከስልጣን አርቆ ማስቀመጥን።

## 3-ተጠያቂነትን ሽሽት

አማራ ጠሉ ስርዓት ስልጣን ከያዘበት 1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ አማራ ህዝብ ላይ ከአፓርታይድ እስከ ጄኖሳይድ የሚዘረጉ አሰቃቂ መንግስታዊ ወንጀሎችን ፈጽሟል። ስርዓቱ እነዚህን ወንጀሎች መንግስታዊ ባልሆኑ ታጣቂዎች ላይ ለማላከክ የሚሞክር ቢሆንም በዓለም ላይ የታዩ ልምዶችና ጥናቶች እንደሚያሳዩት አፓርታይድም ሆነ ጀኖሳይድ ረዘም ላሉ አመታት የሚቀጥለዉ ስልጣን በያዘ መንግስት ሲፈፀም ወይም ሲደገፍ ብቻ ነዉ። በዓለም ላይ የታዩ አሰቃቂ የዘር ማጥፋት ወንጀሎች ሁሉ ስልጣን በያዙ መንግስታት የተፈጸሙ ናቸዉ። በአማራ ህዝብ ላይ የተፈጸመዉ ዘር ማጥፋት ከዚህ አለማቀፋዊ ሃቅ የተለዩ ሊሆን አይችልም።

የአማራ ህዝብ የሚያነሳቸዉ የፍትህ ርትዕ ጥያቄዎች የዘር ማጥፋትን ጨምሮ ፈርጀ ብዙ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የፈጸሙ/ያስፈጸሙ የመንግስት ባለስልጣናትን በአለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች የሚያስጠሩ ናቸዉ፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተገቢዉን መልስ መስጠት ታዲያ ለአማራ-ጠሉ ስርዓት በራሱ ላይ የወንጀለኝነት ሰንሰለት ማጥለቅ በመሆኑ ሽምጥጦ መካዱን መርጧል፡፡

## የአማራ ህዝብ ፍትህ ርትዕ እንዳያገኝ የሚያግዱ ሃይሎች

የአማራ ህዝብ በደሉን የመናገርም ሆነ የመደመጥ መብቱን የተነፈገዉ በተለያዩ አካላት ነዉ፡፡ ከእነዚህ አካላት ዉስጥ ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸዉ፡-

1. አማራ-ጠሉ ስርዓት
2. የአማራ ልሂቃን
3. የ "ፌደራሊስት ሃይሎች"

እነዚህ የፖለቲካ ሃይሎች የአማራዉ ህዝብ በማንነቱ የሚደርስበትን ብሄር ተኮር በደል ተናግሮ የመደመጥና ፍትህ የማግኘት መብቱን(አብዛኞቹ አዉቀዉ ጥቂቶች ደግሞ ሳያዉቁ) ይነፍጋሉ፡፡ እነዚህን ሃይሎች ከነፖለቲካዊ ፍላጎታቸዉ ለይቶ ማወቁ የአማራ ብሄርተኝነት የሚታገለዉን ሃይል ለይቶ እንደ አመጣጡ ለመታገል ያግዘዋልና ወደ ማብራሪያዉ ልለፍ፡፡

## 1. አማራ-ጠሉ ስርዓት

ስልጣን ላይ ያለው አማራ-ጠል ስርዓት የአማራን ህዝብ የሚበድልባቸዉ እና በደሉ እንዳይሰማ የሚያፍንባቸዉን መንገዶች በዚህ ሰነድ በርካታ ገጾች በሰፊዉ ለመዳሰስ ስለተሞከረ አሁን እዚህ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ሆኖም የስርዓቱ መሪዎች ከትላንት እስከ ዛሬ በግልጽ መድረክ የአማራን ህዝብ በደል የካዱባቸዉና ህዝቡ እንዳይደመጥ ያገዱባቸዉን ተጨባጭ አጋጣሚዎች መግለጹ ከዚህ ቀደም ስለስርዓቱ ያነሳናቸዉን ትንታኔዎች ሙሉ ያደርጋሉ እና ወደዛዉ ልለፍ፡፡

አማራ-ጠሉ ስርዓት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ ስሩን በሰደደበት የሽግግር ዘመን በኦሮሚያ ክልል የአማራ ተወላጆች ከእስር ቤቶች ሳይቀር በሌሊት እያወጡ በአሰቃቂ ሁኔታ ይረሸኑ ነበር። ይህን ያደርጉ የነበሩ የኦነግ አባላት እና መሪዎች ሆነዉ ሳለ በሽግግር ምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ የኦሮሞ ህዝብ ይቅርታ ሊጠየቅ ይገባል ብለዉ ሲሞግቱ የነበሩትም ራሳቸዉ የኦነግ አባላት መሆናቸዉን በሽግግር ዘመኑ ቃለጉባኤ ላይ ሰፍሮ ይገኛል። በዚህ የሽግግር ምክር ቤት ዉስጥ ለአማራ ህዝብ የሚሞግት አንድም የአማራ ተወካይ አልነበረም። በኋላ ህገ-መንግስቱን ህዝባዊ ለማስመሰል በተጠራዉ "የህገ-መንግስት ጉባኤ" በሚባል ስብስብ ላይ ስለ አማራ ህዝብ እልቂት ጉዳይ፣ለም መሬቶቹን በዉንብድና ስለመነጠቁ ኢ-ፍትሃዊነት ለመጠየቅ የሞከሩት እንደሻለቃ አድማሴ ያሉ ሰዎች የመደመጥ መብታቸዉን ተነፍገዉ በአማራ-ጠሉ ስርዓት ተስባሰቢዎች ከፍተኛ የስድብ ዉርጅብኝ ይወርድባቸዉ እንደነበር ይሄዉ ለታሪክ የተቀመጠ ቃለ ጉበኤ ምስክር ነዉ።

የአማራ-ጠሉ ስርዓት መስራች የሆኑት አቶ መለስ ዜናዊ የሽግግር ምክር-ቤቱ ሰብሳቢም ነበሩ። አቶ መለስ በኦነግና ህወሃት የተባበረ ክንድ በተለይ በኦሮሚያ ክልል በአማራ ተወላጆች ላይ በወቅቱ ይደርስ የነበረዉን እልቂት በዝምታ ሲደግፉ ኖረዋል የዘር ፍጅቱ ጉዳይ የምክር ቤቱ መወያያ ርዕስ እንዲሆን ያደረጉት ከኦነግ ጋር የነበራቸዉ የፖለቲካ ሽርክና ወደ መሻካከሩ ሲቀየር ነበር። መሻካካሩ የመጣዉ አቶ መለስ በአምሳላቸዉ  የሰሩት ኦህዴድ ኦሮሚያን የማስተዳደር አቅም ላይ እንደደረሰ ሲያምኑ ክልሉን ከኦነግ ነጥቀዉ ለምስለኔያቸዉ ኦህዴድ ለመስጠት ሲሞክሩ ኦነግ በጄ ባለማለቱ ነዉ።

አቶ መለስ ኦነግን ከሸኙ በኋላ በዉል ተዳድለዉ በተቀመጡበት ወንበራቸዉ ላይ ሆነዉ በአንድ የፓርላማ ዉሏቸዉ በደቡብ ክልለ ጉራፈርዳ ወረዳ በወቅቱ የደቡብ ክልል ፕሬዚደንት በነበሩት አቶ ሽፈራዉ ሽጉጤ ትእዛዝ እየተገደሉ እና እየተፈናቀሉ ስላሉ አማሮች ጉዳይ ጥያቄ ሲቀርብላቸዉ እዛ አካባቢ አማራዉ ከመብዛቱ የተነሳ ምዕራብ ጎጃም እየመሰለ ስለሆነ የተደረገዉ ዘር ማጽዳት እና ዘር ማጥፋት ተገቢ እንደሆነ ለማስረዳት ሞክረዋል። አክለዉም " አማራ አለቀ፣አማራ ተፈናቀለ እያላችሁ አታጋግሉ" በማለት የአማራዉ ሞት በኦነግም በሌላዉም ቢደረግ ፍቃዳቸዉ እንደሆነ፣ ይህን በደል ብሎ ማዉራትም በአማራ-ጠሉ መንግስታቸዉ ትልቅ ጥፋት እንደሆነ መረዳት ለሚፈልግ ሁሉ አስረድተዉ አልፈዋል።

አማራዉ በደሉ እንዳይቆምም፣ ስለበደሉ እንዳይወራም ተግቶ የመስራቱ ሁለተኛ በደል የኦነግ መሪዎች ወይም የአቶ መለስ ግላዊ ፍላጎት ሳይሆን የአማራ-ጠሉ ስርዓት አጠቃላይ የፖለቲካ ፍላጎት እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል። ይህ መረዳት የአማራ ህዝብ ትግል ከአጠቃላይ ስርዓቱ ጋር እንጂ በየጊዜዉ ከሚቀያየሩ ግለሰቦች ጋር ብቻ እንዳልሆነ ያስረዳል። ይሄን ሃቅ አለመረዳት ግን ግለሰቦችን በመቀያየር ለዉጥ ለማግኘት የመሻት ቀቢፀ-ተስፋን በመሰነቅ ስህተትን መደጋገምን ያስከትላል። ለዚህ የቅርብ ጊዜ አስረጅ የሚሆነዉ ጠ/ሚ አብይ አህመድ አማራዉ በጅምላ ተፈጅቶ እንደ ቆሻሻ ነገር በፌስታል ተጠቅልሎ በስካቫተር በተቀበረበት በቤንሻንጉል ክልል ተገኝተዉ አማራዉ የሚወቀስበትን ስብሰባ መርተዉ መመለሳቸዉን ማስታወስ ነዉ። በተጨማሪ ጠ/ሚ አብይ በአንድ የፓርላማ ዉሎአቸዉ በወለጋ፣ በቤኒሻንጉል እና በሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች በአማራዉ ላይ ስለሚፈጸመዉ አሰቃቂ የዘር ፍጅት ሲጠየቁ "ለአማራ ህዝብ እረፍት ስጡት" በማለት ጠያቂዎቹን መልሰዉ የተዛለፉበት መንገድ የአማራን ህዝብ በተመለከተ አማራ-ጠሉ ጎራ ያለዉ አቋም ከአንድ ወንዝ የተቀዳ መሆኑን የሚያስረግጥ ነዉ። ጠ/ሚ አብይ አክለዉም "ማንም ቢሞት እኛ ዛፍ በመትከሉ እንቀጥላለን፤ ዛፉ አድጎ ለሚሞቱት ሰዎች ሬሳ ጥላ በመሆን ያገለግላል" ያሉት ንግግር በአሳፋሪነቱ በታሪክ ተመዝግቦ ይኖራል።

## 2. የአማራ ልሂቃን

የአማራ ህዝብ የሚደርስበትን በደል ተናግሮ እንዳይደመጥና ፍትህ ርትዕ እንዳያገኝ አጥብቆ የሚሰራዉ አማራ-ጠሉ ስርዓት ብቻ አይደለም። ይልቅስ ራስን የመናቅ የስነ-ልቦና ቀዉስ ያለባቸዉ የአማራ ልሂቃንም በዚህ ረገድ ከአማራ-ጠሉ ሰርአት ያላነሰ ሚና ይጫወታሉ/ሲጫወቱም ኖረዋል።እጅግ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ የአማራ ህዝብ ዘመናትን የዘለቀ በደል መነገሩን እና መደመጡን የሚቃወመዉ፣የሚተቸዉና የሚያወግዘዉ የአማራ ልሂቅ ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም። ይህ መሰረታዊ የስነ-ልቦና ችግር በዋናነት የሚመነጨዉ ኢህዴን/ብአዴን ከተሰራበት የፖለቲካ ስነልቦና ነዉ። ይህን ራስን የሚያስንቅ የፖለቲካ ስነ-ልቦና የቀመመዉ ደግሞ አማራን አዋርዶ መግዛትን እንደ ትልቅ የፖለቲካ ስኬት የሚቆጠረዉ ህወሃት ነዉ። ራስን የሚያስንቀዉ የፖለቲካ ስነ-ልቦና ራስን መናቅ፣ግብዝነት፣ግለኝነት፣ የስልጣን ጥም፣ ፈሪነት፣ ጨካኝነት፣ግዙነት የተባበሩበት ዉርደትን ከክብር የሚያስቆጥር መሰረታዊ የስብዕና ችግር ነዉ።

እራስን የሚያስንቀዉ ስነልቦና ችግር በብአዴን ሰዎች ብቻ ሳይቆም አብን ወደተባለዉ ፓርቲ የላይኛዉ አመራርም ጎራ ብሏል፡፡ ለዚህ ነዉ የአማራ ብሄርተኝነትን አንድ ደረጃ ከፍ ያደርጋል ተብሎ ተስፋ የተጣለበትን ፓርቲ የሚመሩት አመራሮች የአማራን ህዝብ በደል በማጋለጡ ላይ እንደ ደከሙ የሚያሳስቡ ደጋፊዎቻቸዉን "መንጋ" ሲሉ የዘለፉት፡፡ በመሰረቱ የአማራን ህዝብ መብት ለማስከበር የተመሰረተ ፓርቲ የተመሰረተበትን አላማ ለማስፈጸም በሚቀድመዉም በሚያሳስበዉም መኖር አልነበረበትም፡፡

የአማራ ህዝብ በደል እንዳይነገር/እንዳይደመጥ የሚከላከሉት የአማራ ልሂቃን ስልጣን የጨበጡ የብአዴን/አብን መሪ የአማራ ልሂቃን ብቻ አይደሉም፡፡ ይልቅስ በአማራ-ጠሉ ስርዓት ዉስጥ እጣ ፋንታ ያልነበራቸዉ፣እንደዉም ስርዓቱን አምርረዉ የሚቃወሙም የአማራ ልሂቃንም የአማራ ህዝብ በብሄር ማንነቱ የሚደርስበትን በደል መናገርን እንደ ዘረኝነት በመቁጠር ይቃወሙታል፡፡ አማራዉ እንደ ብሄር የሚደርስበትን በደል በብሄር ተደራጅቶ ማዉገዝ እና ማጋለጥ የኢትዮጵያ ሃገረ መንግስትን ያፈርሳል ብለዉ በጥብቅ ያምናሉ፡፡ በእነዚህ ቡድኖች አስተሳሰብ የአማራዉ ብቻ በብሄር አለመደረጃት የኢትዮጵያ  ሃገረ መንግስት ለማቆየት የሚያስችል በቂ ሁኔታ ነዉ፡፡ በአማራዉ ላይ በብሄሩ የሚደርስበት በደልም በኢትዮጵያዉያን ላይ የተቃጣ ጥቃት ተደርጎ መቆጠር አለበት ሲሉ ሳያወቁት የአማራ-ጠሉን መሰሪ ፍላጎት ይናገራሉ፡፡ በአማራ ህዝብ ላይ የተቃጣዉን ግልጽ ጥቃት "በዜጎች ላይ፣ በኢትዮጵያዉያን ላይ"፣ "በንጹሃን ላይ" የተቃጣ ጥቃት እያሉ መግለጻቸዉን "ዘረኞች" ሳይሆኑ "ሰብዓዊያን" የመሆናቸዉ ማሳያ እየመሰላቸዉ ይኩራራሉ፡፡ ስለአማራዉ ህዝብ በደል የሚሞግቱ የአማራ ተወላጆችንም "የአማራ-ጠሉን ጎራ የዘረኝነት መንገድ የተከተሉ ጠባቦች" አድርገዉ ለማዉገዝ ይዳዳቸዋል፡፡

አማራ ሆነዉ ሳለ በአማራ ህዝብ ላይ የሚደርሰዉን ብሄር ተኮር ጥቃት በኢትዮጲያዊነት መጋረጃ ጠቅልለዉ፣ ከመፍትሄዉ አርቀዉ መጣላቸዉንም "ከዘረኝነት አዘቅት" ወጥተዉ "በሰብአዊነት" የሞራል ከፍታ ላይ የጠቀመጡበት ማማ አደርገዉ ያስቡታል፡፡ እነዚህ የአማራ ልሂቃን የዘነጉቸዉ ወሳኝ ሃቆች ማንም ሰዉ በዘር ማጥፋት ፊት ገለልተኛ መሆን እንደማይችል፣ዘር ማጥፋትን በሌላ ስም መጥራት ደግሞ ዘር ማጥፋቱን እንደመደገፍ እንደሚቆጠር፣ዘር ማጥፋትን በስሙ አለመጥራት ለዘር ማጥፋት ወንጀል መደጋጋም አይነተኛ ግብዓት እንደሆነ ነዉ፡፡

ይህ ደግሞ እነዚህ የአማራ ልሂቃን ለእራሳቸዉ ከሰጡት "የሰብአዊነት ልዕልና" በእጅጉ የሚጣላ ነዉ።

## 3.የ "ፌደራሊስት" ሃይሎች

እነዚህ ሃይሎች የአማራ-ጠሉ ጎራ ስልጣን ያልያዙ ክንፎች ናቸዉ። የፖለቲካ አላማቸዉ መነሻዉና መድረሻ አማራዉ በድሎናል የሚለዉ ትርክት ነዉ። በመሆኑም የአማራ ህዝብ የሚደርስበትን በደል እንደ የጽድቅ ስራ የሚቆጥሩ እንጂ በነዉርነቱ እንዲገለጽ የማይፈልጉ ናቸዉ። እነዚህ የፖለቲካ ሃይሎች ብሄራቸዉን ወክለዉ ስልጣን ላይ ለመፈናጠጥ የሚቋምጡ፣አማራን ከማብጠልጠል የዘለለ የፖለቲካ ግንዛቤም ዘይቤም የሌላቸዉ፣የብሄር ፖለቲካን የኢትዮጵያ ዘላለማዊ የፖለቲካ ዘይቤ አድርገዉ በተለይ አማራዉን ሲያሳድዱ መኖር የሚፈልጉ ናቸዉ። የአማራዉ ልሂቅ በአማራዉ ህዝብ ላይ በብሄር ማንነቱ ሳቢያ የሚደርስበትን በደል ለመናገር ሲሞክር በአስቂኝ ሁኔታ አማራዉን በዘረኝነት ለመዉቀስ የሚሞክሩ ሃፍረተ-ቢስ ፖለቲካ የሚያራምዱ ወገኖች ናቸዉ። እነዚህ ሃይሎች አማራዉን በዳይ እንጂ ተበዳይ ሆኖ እንዲቀርብ ስለማይፈልጉ አማራዉ የህልዉና ጥያቄዎቹን ሲያነሳ "ነፍጠኛዉ ተመልሶ ሊመጣ እያንሰራራ ነዉ" በማለት በብቸኝነት የሚያዉቋትን የፖለቲካ እዉቀታቸዉን ይደጋግማሉ።
በአጠቃላይ ስልጣን ላይ ያለዉም ሆነ ለስልጣን ተስፋ የሚያደርገዉ የአማራ-ጠሉ ጎራ ስልፈኛ አማራዉ ለአመታት እየደረሰበት ያለዉን አሰቃቂ በደል እንዲናገርም ሆነ እንዲደመጥ በፍጹም አይሻም። ይህ ቡድን በአማራዉ ላይ እየተደረገ ያለዉ የትኛዉም ወንጀል መቀጠል ያለበት ተገቢ ነገር ነዉ ብሎ ስለሚያምን በዝምታ እንዲቀጥል እንጂ በወንጀልነቱ እንዲነገር አይፈልግም። በዚህ ረገድ አጋዥ አስተዋጽኦ የሚያደርገዉ ደግሞ ራስን በመናቅ የስነልቦና ቀዉስ ዉስጥ ከመዘፈቁ የተነሳ በወጣበት ህዝብ መከራ ላይ ፊቱን አዙሮ የተሳሳተ የሰብአዊነት ፍልስፍና የሚፈላሰፈዉ የአማራዉ ልሂቅ ነዉ። አማራ-ጠሉ ስርዓት እንዲህ ያለዉን የአማራ ልሂቅ ከጎኑ አሰልፎ "አማራ ማለት እርሱ/እርሷ ነዉ/ናት" በማለት ለህዝባቸዉ መከራ ማብቃት የሚሞግቱ የአማራ ልሂቃንን በዘረኝነት ይከሳል። አስቂኙ ነገር የአማራ ልሂቃንን በዘረኝነት የሚከሰዉ የአማራ-ጠሉ የብሄር ፖለቲከኛ የብሄር ፌደራሊዝሙ ሆነ የብሄር ፖለቲካዉ በሲቪክ የፖለቲካ አስተዳደር ይተካ ቢባል የማይስማማ መሆኑ ነዉ።

## አማራዉ ፍትህ ርትዕ ለማግኘት ያደረጋቸዉ ጥረቶች

አማራ-ጠሉን የፖለቲካ ሃይል በኢትዮጵያ የመሰረተዉና የሚመራዉ ስርዓት የአማራን ህዝብ በደል ለማድመጥም ሆነ ለማስቆም ፍላጎት እንደሌለዉ በተደጋጋሚ ተብራርቷል፡፡ ስርዓቱ በአማራ ህዝብ ፍትህ ርትዕ ጥያቄ ላይ ጆሮዉን የሚደፍንበት ዘይቤዉ ስርዓቱ ከአማራ ህዝብ ጋር ያለዉን ልዩነት የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነት ከመሆን አልፎ ሰብአዊ ልዩነት እስከሚመስል የሚደርስ መሆኑን የሚገልፅ ነዉ፡፡ እነዚህን የፖለቲካ ሃይሎች ከአማራ ህዝብ ጋር የሚለያቸዉ የፖለቲካ ልዩነት ብቻ ቢሆን ኖሮ ለሰላሳ አመታት በህዝቡ ላይ የሚደርሰዉን ሰብአዊ መብት ጥሰት ልክ እንዳልሆነ ሊረዱት እና እልባት ሊሰጡት ይገባ ነበር፡፡ የፖለቲካ ልዩነትን አንግቦ ለትግል የወጣ ቡድን ለትግል የወጣበትን የፖለቲካ ጥያቄ ካስመለሰ በኋላም ራሱንም ሃገርንም ወደ ማረጋጋት ይገባል፡፡የአማራ-ጠሉ ስርዓት "አማራ ጨቁኖኛልና ለእኩልነት እታገላለሁ" ሲል ወደ ትግል ሜዳ ገብቶ ስልጣን ጨብጧል፡፡ ስልጣን ከጨበጠ በኋላም አማራዉን ከሃገሩም ከክልሉም ስልጣን እንዲገለል በማድረግ ኢትዮጵያን በአማራ-ጠል የፖለቲካ ዘይቤ መምራት ጀመረ፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን አማራዉ ኢትዮጵያን የታደገ መስሎት ሁሉን ነገር በትዕግስት ሲከታተል ለረዥም ዘመናት በዝምታ አሳልፏል፡፡ ነገር ግን አማራ-ጠሉ ስርዓት ስልጣን ጨብጦ በአትዮጵያ በአጠቃላይ ፖለቲካ ላይ እንዲሆን የፈለገዉን ሁሉ ካደረገ በኋላ በቀጥታ የገባዉ ከጽንሰቱ ጀምሮ ጠላት አድርጎ የፈረጀዉን የአማራ ህዘብ በማንነቱ ነጥሎ በመጨፍጨፍ፣በማፈናቀሉና ማሳደዱ ተግባር ላይ ነዉ፡፡ ይህ የፖለቲካ ልዩነት ያመጣዉ እርምጃ ሊሆን አይችልም፡፡ የፖለቲካ ጥያቄ አለኝ ብሎ ወደ ትግል የገባና ስልጣን የጨበጠ አካል ጥላቻን ዘር ማጥፋትን የፖለቲካ ዘይቤዉ አድርጎ ለሰላሳ አመታት አይዘልቅም፡፡ የስርዓቱ እዉቀት አጠር ካድሬዎች ቀርተዉ ቀለም የዘለቃቸዉ፣በምዕራባዉያን ሃገራት የታወቁ ዩኒቨርሲቲዎች ህግን፣ሰብአዊ መብት፣ፖለቲካን ፍልስፍናን፣ታሪክን የመሰሉ የሰዉ ልጅን በክቡርነት የሚያስገነዝቡ ትምህርቶችን የተማሩና የሚያስተምሩ ምሁራን በአማራ ህዝብ ላይ የሚደረገዉን ዘግናኝ ጭፍጨፋ፣ማቆሚያ የሌለዉ መፈናቀል፣የዘወትር መሳደድ ሁሉ የፖለቲካ ስኬታቸዉ አድርገዉ የሚቆጥሩ መሆናቸዉን በተደጋጋሚ በተግባር አሳይተዋል፡፡

አማራ-ጠሉ ምሁራን አልፈዉ ተርፈዉ(በኦሮሚያ ክልል በተለይ) ኮሽ ባለ ቁጥር "ነፍጠኛዉን ንቀለዉ፣ ነፍጠኛ የዛሬም የነገም፣ የወደፊትም ጠላታችን ነዉ፣ ከነፍጠኛ ጋር ታክቲካል እንጅ ስትራቴጅክ የሆነ ወዳጅነት ሊኖረን አይችልም፣ የጋራ ታሪክም የለንም" የሚሉ ዘላለማዊ ጠላትነትን የሚሰብኩ አዕምሮ የጎደለዉ ሰዉ ንግግሮችንም በሚዲያ ሲያሰራጩ ኖረዋል። ይህ መማር ምንም ሊያግዘዉ የማይችለዉ፣ ልቦና የሚሰዉር፣ ማስተዋልን የሚቀማ ጥላቻ ከፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ብቻ የሚመነጭ ነዉ ብሎ ለማመን ያስቸግራል። የፖለቲካ ልዩነት የሰዉን ልጅ ለጭፍጨፋ በሚያዘጋጅ ንግግር አይገለጽም፤እንዲህ ባለ ሁኔታ የሚገለጸዉ የፖለቲካ ልዩነት ሳይሆን ሰብአዊነትን እስከመካድ የደረሰ ዳርቻ የለሽ ጥላቻ ነዉ።

አማራ-ጠሉ ጎራ ከአማራ ህዝብ ጋር ያለዉ ልዩነት ሰብአዊነትን እንኳን ለማክበር የሚቸገር፤በጥላቻዉ እየባሰ በሄደባቸዉ ሰላሳ አመታት የአማራ ልሂቅ የሚያደምጠዉ ባይኖርም ጥላቻ ያመጣበትን በደል አስረድቶ ፍትህ ለማግኘት ሞክሯል። እነዚህን ሙከራዎች በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

## 1-የአማራ ብሄር ተወላጅ ያልሆኑ ኢትዮጵያዉያን በደሉን እንዲያወሩለት መጠበቅ/ማበረታታት

የአማራ ልሂቃን ስለህዝባቸዉ በደል ሲናገሩ የብሄረሰቦችን መብት ለመጨፍለቅ፣የድሮዉን ስርዓት ለማምጣት ወዘተ የሚሉ ማሸማቀቂያዎች ከስርዓቱ ስለሚጠብቃቸዉ የሌሎች ብሄረሰብ ልሂቃን ስለ አማራዉ በደል እንዲናገሩላቸዉ መጠበቁ/ማበረታታቱን እንደ መፍትሄ ወስደዉ ኖረዋል። የአማራዉ ልሂቅ በአማራ-ጠሉ ስርዓት የማሸማቀቂያ ፕሮፖጋንዳ ምክንያት ድመፅ-ከል (Voiceless) በመደረጉ ሳቢያ ስለራሱ ችግር ሌሎች እንዲያወሩለት እስከመጠበቅ ቢደርስም የተጠበቀዉን ያህል ስለ አማራ ህዝብ በደል የሚናገር የሌላ ብሄር ተወላጅ ልሂቅ አልተገኘም።ከአማራ ብሄር ሳይወለዱ ስለአማራ ህዝብ በደል ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ከሞገቱ ሰዎች ቀዳሚዉ ***አቶ ታዲዎስ ታንቱ*** ሲሆኑ ሁለተኛዉ ሰዉ ***አቶ ኦባንግ ሜጦ*** ሶስተኛዉ ***ፕ/ሮ ሃይሌ ላሬቦ*** እና አራተኛዉ ***ዶ/ር ተድላ ወ/ዮሃንስ*** ናቸዉ። እነዚህ ሰዎች የሰብአዊ መብት ጥበቃ ጉዳይ የዘመናዊዉ አለም መግባቢያ ቋንቋ መሆን እንዳለበት የተረዱ ስለሆኑ በአማራ ህዝብ ላይ የሚፈጸመዉን የሰብአዊ መብት ጥሰት፣መገለል፣መሳደድ አጥብቀዉ አዉግዘዋል።

በመሆኑም አቶ ታዲዎስ ታንቱ ከአማራ ተቆጥረዉ እስር ቤት ተወርዉረዋል፡፡

ድምፀ-ከል(Voiceless) የሆነዉ የአማራ ህዝብ ሌሎች ኢትዮጵያዉያን ወገኖቹ ስለበደሉ እንዲናገሩለት የፈለገዉ ማንም ሰዉ በዘር ማጥፋት ፊት ገለልተኛ መሆን ስሌለበት ነዉ፡፡ በዘር ማጥፋት ወንጀለኛ ፊት ገለልተኛ መሆን ዘር ማጥፋቱን በሌላ መንገድ መደገፍ ነዉ፡፡ ሆኖም አማራዉ ያሰበዉን ያህል ወንድም/እህቶቹ የሆኑ ኢትዮጵያዉያን በደሉን በመናገር ሊያግዙት አልቻሉም፡፡ በመሆኑም የአማራ ህዝብም ከትግሉ በቀር መዳኛ እንደሌለዉ አዉቆ በደሉን ለማስቆም ትግል ጀምሯል፡፡ ይህን ኮስታራ ትግል ሲጀምር ደግሞ በደሉ ላይ ፊታቸዉን አዙረዉ የነበሩ ከአማራ ብሄር የማይወለዱ ልሂቃን ሰላም እንደሚሻል ሊመክሩት በመንግስት የቴሌቭዥን ጣቢያዎች መሰለፍ ይዘዋል፡፡ ይህን ሲያዩ የአማራ ህዝብ እስራኤላዉያን ከናዚ ጭፈጨፋ በኋላ ለዓለም ህዝብ ያቀረቡትን ጥያቄ ማቅረብ ይገባዋል፡፡ ይህ ጥያቄ የሚከተለዉ ነዉ፡-

> *"አቃጥለዉ ከጨረሱን መካከል ካልሆናችሁ የሚያቃጥሉንን ስታግዙ ነበር፤አልያም የእራሳችሁ ጉዳይ ብላችሁ በእልቂታችን ላይ ፊታችሁና አዙራችሁ ነበር"*

የአማራ ህዝብ ለኢትዮጵያዉያን ወገኖቹ ይህን ጥያቄ የሚያቀርበዉ በኢትዮጵያ ዉስጥ ያለአግባብ በሚበደሉ ህዝቦች ላይ ፊቱን አዙሮ ስለማያዉቅ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተመሳሳዩን ከሌሎች ህዝቦች ይጠብቅ ነበር፡፡ ይህን ማድረግ ያልቻለ ሰዉ ደግሞ የአማራ ህዝብ ህልዉናዉን ለማስበር፣ፍትህ ርትዕ ለማግኘት የሚያደርገዉን ትግል የሚያናጥብ "ምክር" ለመምከር ድፍረት ከየትም ሊያመጣ አይገባም፡፡

## 2-አማራ-ጠሉን ስርዓት መለማመጥ፡-

ይህ በዋናነት የኢህዴን/ብአዴን/ ፣የአማራ ብልጽግና ልሂቃን የሚዘወተር ዘይቤ ነዉ፡፡ እነዚህ የአማራ ልሂቃን የገዛ ክልላቸዉን ለማስተዳደር በአማራ-ጠሉ ስርዓት በግዙነት የተሰየሙ ናቸዉ፡፡ ሆኖም የአማራ ህዝብን ለመቅጣት የሚሰነዝረዉ ለበቅ በተዘዋዋሪ እነዚህን ግዙ ሹመኞችም ይለበልባል፡፡

ይኸዉም አማራ-ጠሉ ስርዓት በሃገሪቱ ዳርቻ የሚኖረዉን አማራ "ነፍጠኛ"፣ "ትምክህተኛ" ፣ "መጤ" እያለ ሲጨፈጭፍና ሲያሳድድ የአማራ ህዝብ ክልሉን በሚመሩ ግዙ ሹመኞች ላይ ቁጣዉን ያነዳል። የህዝቡ ቁጣ ደግሞ የምስለኔዉን ወንበር መነቅነቁ አልቀረም። ሆኖም አማራ-ጠሉ ስርዓት ለምስለኔ ግዙ አገልጋዮቹ ወንበር ተጨንቆ በአማራ ህዝብ ላይ የሚያነሳዉን የጭካኔ በትር አያስቀምጥም። በዚህ ምክንያት ከህዝባቸዉም ከወንበራቸዉም መሆን ያልቻሉ የብአዴን/አማራ ብልጽግና ግዙ መኳንንት ቢቸግራቸዉ የኦሮሞ ብልጽግና አሳዳሪዎቻቸዉን በባህርዳር ድረስ ጠርተዉ ካባ እስከማልበስ የደረሰ አሳፋሪ ልምምጥ ተለማምጠዉ ሞክረዉት ነበር።

ሆኖም የኦሮሞ ብልጽግና መኳንንት እጅግ አስቸጋሪ ጌቶች ሆኑባቸዉና በኦሮሚያ ክልል የሚኖሩ አማሮችን ማስፈጀትም ሳያቆሙ፣የባህርዳር ቅጥረኞቻቸዉ ወንበርም ነቅነቅ ሳይል፣ስለአማራዉ መሞትም ትንፍሽ እንዳይባል ቀጭን ትዕዛዝ ይልኩባቸዋል። ከዚህ ሲያልፍ የክልሉን ካቢኔ ከላይ እስከታች  እንዳለ ከስልጣን አንስተዉ በሌላ ይተካሉ። ይሄዉ የካቢኔ ቅየራ አሁን የአማራ ክልል መንበረ ስልጣን  ላይ የተሰየሙትን ሰዉዬ ዋና አድርጓል። የሰዉየዉ ሹመት የአማራ ብልጽግና ፓርቲ በካባ የጀመረዉ አሳፋሪ የልምምጥ ጉዞ ደረጃዉን አሳድጎ የኦሮሞ ብልጽግናን የመምሰል የተሟላ መሸጦነት ላይ መድረሱን የሚያስረዳ ነዉ።

## 3-ሁለገብ ህዝባዊ ትግል

ለበርካታ አመታት በደሉን በዝምታ ሲታገስ የኖረዉ የአማራ ህዝብ የተነፈገዉን ፍትህ በትግሉ ለማግኘት የተፋፋመ ህዝባዊ ትግል እያደረገ ይገኛል። የአማራ ህዝብ በዚህ ትግሉ የተገፈፈ መብቱን፣የተናቀ ማንነቱን፣የተዋረደ ሰብአዊ ክብሩን የሚያስመልስበት ትርጉም ያለዉ ድል ይፈልጋል።

# ክፍል ሦስት

## የአማራ ህዝብ ጥያቄዎች
## እና "ህብረ-ብሔራዊ አንድነት"

## 3.1 የአማራ ህዝብ ጥያቄዎች እና "ህብረ ብሄራዊ አንድነት"

የሃገራችንን ፖለቲካ ለሰላሳ ሶስት አመታት ሲዘወር የኖረዉ የብሄር ፖለቲካዉ ዋና ማጠንጠኛ አማራ-ጠልነት ነዉ። ስርዓቱ የሚመራበት አማራ-ጠል ርዕዮት ከስርዓቱ የምሁራን ክንፍ ይመነጫል። የአማራ-ጠሉ ስርዓት የጀርባ አጥንት የሆኑት ምሁራን ስለ አማራ ህዝብ ያሏቸዉ ከእዉነታ የራቁ እጅግ አደገኛ ምልከታዎች በጥናታዊ ጽሁፎቻቸዉ፣በመጽሃፍት፣በተለያዩ መጣጥፎች እና ጥናታዊ መጽሄቶች አማካይነት በሰፊዉ ተሰራጭተዋል። እነዚህ ምሁራን በአመዛኙ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚፅፉና በምዕራቡ አለም በስደት የሚኖሩ ናቸዉ።

በአንፃሩ የአማራ ምሁራንም በምዕራቡ አለም በብዛት የሚኖሩ ቢሆንም የህዝባቸዉን እዉነት በመግለጥ ረገድ በአማራ-ጠሉ ምሁራን ልክ አይተጉም። በዉጤቱም በምዕራቡ አለም የአካዳሚ፣ጋዜጠኞችና የተለያዩ ድርጅቶች የአማራ ህዝብ ጉዳይ አማራ-ጠሉ ምሁራን ባቀረቡላቸዉ ሁኔታ ብቻ እንዲረዱት ሆኗል።የምዕራቡ አለም የፖለቲካና የሲቪክ ተቋማት ደግሞ አቋማቸዉን የሚቃኙት ከአካዳሚዉ ጎራ ባገኙት እዉቀትና መረጃ ስለሆነ በአማራ ህዝብ ስቃይ ላይ ፊታቸዉን አዙረዉ ኖረዋል። የህዝቡን እዉነት በመግለፅ ረገድ የእራሱን የቤት ስራ ያልሰራዉ የአማራ ምሁር ጎራ ታድያ "ፈረንጅ አማራ አይወድም" ሲል ለራሱ ስንፍና ሌላ ስም ይሰጣል።

የአማራ-ጠሉ ምሁራን ጎራ በአማራ ህዝብ ላይ ያለዉን ጥላቻ ምሁራዊ ቀለም ቀብቶ የሚያቀርብበት መንገድ የናዚዝም እና ፋሺዝም አስተሳሰቦች መንግስት ከመሆናቸዉ በፊት በመላዉ ዓለም ምሁራዊ ስር (Intellectual roots) ለመትከል ያድርጉት የነበረዉን ሁኔታ ይመስላል። አማራ-ጠሉ ምሁራን በአማራ ህዝብ ላይ ሲሰነዝሩት የኖሩት ጥላቻን ሳይንሳዊ አድርጎ የማቅረብ ባህል በርካታ መጽሃፍት፣መመረቂያ ጽሁፎችንና የምርምር መጽሄቶች የተሰሩበት ነዉ። ይህንን በማጋለጡ ረገድ በአንድ የአማራ ምሁር ይበል የሚያስብል ስራ እየሰራ እንደሆነና በቅርቡ ለንባብ እንደሚበቃ ከወዲሁ ለመጠቆም እወዳለሁ።

ስለሆነም ለዚህ ሰነድ ፍጆታ የአማራ-ጠሉ ስርዓት ምሁራን (በተለይ የኦሮሞ ምሁራን) "ኦሮማራ" በሚለዉ ጥምረት የትሮይ ፈረስነት ወደ ስልጣን የመጣዉ መንግስት በሃገራችን ስልጣን ከያዘ በኂላ በሚዲያ የተናገሯቸዉ ንግግሮች ላይ ያተኩራል። ይህን በማድረግ የእነዚህ ምሁራን ንግግር መንግስት ከሚደሰኩርለት ህብረ ብሄራዊ አንድነት (የጋራ ትርክት) ጋራ ያለዉን ክፉ ጠብ ለማሳየት ይሞከራል። የአማራ-ጠሉ ምሁራን እሳቤ ሳይዉል ሳያድር ስልጣን በያዘዉ መንግስት የሚተገበር ስለሆነ ነገሩን በትኩረት ማየቱን አስፈላጊ ያደርገዋል።

"ኦሮማራ" በተባለዉ የአክራሪ ኦሮሞ ብሄርተኞች የትሮይ ፈረስ ተጭኖ ስልጣን የያዘዉ በተረፈ ኢህአዴግ ራሱን "የለዉጥ አመራር" በሚል የክብር ስም ይጠራል። ይህ ቡድን ስልጣን ላይ እንደወጣ ሰሞን የኦሮሞ ምሁራን ብቅ ብለዉ "ከአማራ ጋር የምንጋራዉ ምንም አይነት ስትራቴጂክ ፍላጎት የለንም፣ስልጣን ለመያዝ እስክንችል ድረስ ከእነርሱ ጋር ያሳየነዉ ህብረት የታክቲክ ጉዳይ ነበር" ሲሉ አማራ-ጠል ማንነታቸዉን በይፋ ገለጡ። እምብዛም ቀለም ያልዘለቃቸዉ ግን ደግሞ ስልጣን ላይ የተፈናጠጡ ወንድሞቻቸዉ ደግሞ ምሁራኑን ተከትለዉ "ባህር ዳር ተጉዘን፣ቁማር በልተን፣የሚደነገዘዉን አደንዝዘን፣የሚታለለዉን አታለን እና አስመስለን "convince & confuse" አድርገን ነዉ ስልጣን የያዝነዉ" አሉ። የካድሬዎቹን እንተወዉና የምሁራኑ አባባል ላይ ብናተኩር ከአማራዉ ጋር የምንጋራዉ ዘላቂ ጥቅም(strategic interest) የለንም ከሚለዉ ንግግራቸዉ በተጨማሪ "አማራ የወደደዉን ነገር ሁሉ ኢ-ዲሞክራሲያዊ ስለሆነ እኛ እንጠላዋለን" ሲሉ አከሉበት።

የኦሮሞ ምሁራን ይህን ሲሉ የአማራ ልሂቃን በአንጻሩ "ኦሮማራ" የሚለዉን ጥምረት ለሁሉም ኢትዮጵያዉያን የምትመች፣ ዲሞክራሲያዊት ሃገርን እዉን የማድረጊያ መንገድ አድርጎ ወስዶት ድጋፉን እየገለጸ ነበር። የኦሮሞ ምሁራን "ከአማራ ጋር የምንጋራዉ ስትራቴጂክ ፍላጎት የለንም" ሲሉ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን የማንበሩ ነገር እንኳን ከአማራ ጋር የሚጋሩት ስትራቴጂአዊ ግብ ሊሆን እንደማይችል እየተናገሩ ነዉ። በሌላ አባባል የኦሮሞ ምሁራን ዜግነትን እንኳን ከአማራ ጋር መጋራት አይሹም ማለት ነዉ። የኦሮሞ ምሁራን ይህን ያስባላቸዉ ዘወትር በአይነ ህሊናቸዉ ድቅን የሚልባቸዉ የኦሮሚያ ሪፐብሊክ ምስል ነዉ።

የኦሮሚያ ሪፐብሊክ የምትወለደዉ ከኢትዮጵያ ፍርስራሽ ዉስጥ እንደሆነ ሌላዉ የኦሮሞ ምሁር ቀደም ብለዉ ተናግረዉ ነበር፡፡ በመሆኑም ከአማራ ጋር የሚጋሯትን ኢትዮጵያ የተባለች ስትራቴጂክ ፍላጎት ያስረሳቸዋል፡፡

"ከአማራ ጋር የምንጋራዉ ስትራቴጂክ ጥቅም የለም" ሲል ቃል በቃል የተናገረዉ የኦሮሞ ምሁር አቶ ጃዋር መሃመድ ነዉ፡፡ ነገሩን እሱ ቃል በቃል ይበለዉ እንጅ በርካታ የኦሮሞ ምሁራን ሃሳቡን የሚያጠናክር ነገር ሳይናገሩ ዉለዉ አያድሩም፡፡አስገራሚዉ ነገር ታድያ አቶ ጃዋር መሃመድ ራሱ ዛሬ ላይ ስለ የብሄረ-ኢትዮጵያ አስፈላጊነት አማራን ሊመክር ብቅ ማለቱ ነዉ፡፡ ኢትዮጵያ የበርካታ ፖለቲካዊ ተዓምራት ምድር ብትሆንም የዚህኛዉ አስገራሚነት ላቅ ያለ ነዉ፡፡ ነገሩን የበለጠ አስገራሚ የሚያደረገዉ ደግሞ አቶ ጃዋር ይህን የመሰለ ፍጹም የሃሳብ ለዉጥ ያስደረገዉን ምክንያት ሲገልጽ ድሮ ስላልበሰለ ዛሬ ግን ሙክክ ብሎ በመብሰሉ እንደሆነ መናገሩ ነዉ፡፡

ነገሩን ወንድማችን ጃዋር ባስቀመጠበት የመብሰል ያለመብሰል ጉዳይ እንየዉ ከተባለ ሃገራችን ባልበሰሉ ፖለቲከኞች አንደበትና ብዕር መዘዝ አሳር መከራ የመቁጠሯ ነገር በዋለልኝ መኮንን ይብቃ ያልተባለ ክፉ እዳዋ እንደሆነ ተገንዝበን ማዘናችን አይቀርም፡፡ ሆኖም ተናጋሪዉ አቶ ጃዋር መሃመድ ከወጣትነቱ በማይመጣጠን ሁኔታ ጠብሰቅ ያለ የፖለቲካ እዉቀትና መረዳት ያለዉ ልጅ የመሆኑ፣ሃቅ የፖለቲካ እዉቀት መጀመሪያ የሆነዉን የሃገር ህልዉና አስፈላጊነት ዛሬ ገና ተረዳ ብሎ መቀበል ያዳግታል፡፡ ስለሆነም ትክክለኛዉን ምክንያት የመፈለግ ምርምር ዉስጥ መግባት ዳግመኛ "ቁማር ላለመበላት" ይረዳል፡፡ ወደ ትክክለኛዉ ምክንያት የሚመራን ፍንጭ ደግሞ በአቶ ሌንጮ ለታ እና በአቶ ሌንጮ ባቲ አንደበት ተገልጧል፡፡

አቶ ሌንጮ ለታ ከአንድ አመት በፊት በሰጡት ቃለምልልስ ጠ/ሚ አብይ ወደ ስልጣን እንደመጡ ኦሮሞ ያልደገፋቸዉ አማራ ስለደገፋቸዉና አማራ የደገፈዉና የወደደዉ ነገር ደግሞ ኢ-ዲሞክራሲያዊ ስለሆነ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ይህ ስለ ጠ/ሚ አብይ ድጋፍ ጉዳይ የተነሳዉ ነገር የኦሮሞ ፖለቲካ የተቃኘበትን ትልቁን ምስል የሚያሳይ ነዉ፡፡ የኦሮሞ ፖለቲካ ቅኝት አማራ የወደደዉን ሁሉ ይጠላል፣አማራ የጠላዉን ሁሉ ይወዳል፡፡ በተመሳሳይ አማራ ያነሳዉን ይጥላል አማራ የጣለዉ የመሰለዉን ነገር ደግሞ ያነሳል፡፡ አማራ ከጥንት ጀምሮ በልቡ አትሞት የኖረዉ የብሄረ-ኢትዮጵያ ርዕዮት በኦሮሞ ምሁራንና ፖለቲከኞች ዘንድ በእጅጉ ከመጠላቱ የተነሳ "መፍረስ የሚገባዉ የበሰበሰ ኢምፓየር" እስከመባል ደርሷል፡፡

ኢትዮጵያን በአማራ በኩል የሚጠላዉ የኦሮሞ ብሄርተኝነት ርዕዮት ሲያበሻቅጣት የኖረዉን ሃገር መንበረ ስልጣን እንደጨበጠ ሃገሪቱን በአማራ በንጹሃን ደም አከረፋት። ይህ ለኦሮሞ ልሂቃን፣ምሁራንና ፖለቲከኞች ችግር ያለዉ ነገር አይደለም፤ይልቁንስ የድል አድራጊነታቸዉና የባለስልጣንነታቸዉ መገለጫ ነዉ።

በሌላ በኩል የወገኖቹ ደም የከረፋዉ የአማራ ታጋይ ባልተለመደ መታወቂያዉ የአማራ ብሄርተኝነትን አንግቦ ለሰብአዊ ክብሩ መታገል ጀመረ። ይሄኔ የኦሮሞ ልሂቃን ብሄረ-ኢትዮጵያን ከአማራ እጅ እንዳስጣሉ እርግጠኛ ሆኑ። አማራ የጣለዉን በሚያስነሳቸዉ ክፉ አባዜያቸዉ መሪነት ሲያበሻቅጡት የኖሩትን የብሄረ-ኢትዮጵያን ርዕዮት አንስተዉ ስለ ዉበቱ ማዉራት ጀመሩ። ይህን አቶ ሌንጮ ባቲ ጠቅልለዉ ሲያስቀምጡት "ከዚህ በፊት ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሰርተናል፤አሁን ደግሞ ለመገንባት እንሰራለን" ብለዋል። የኦሮሞ ብሄርተኞች አማራ የጣለዉ የመሰላቸዉን የብሄረ-ኢትዮጵያ ርዕዮት አንስተነዉ ባልተለመደ ሁኔታ ስለ ዉበት ቁንጅናዉ ሲያወሩ፣ አማራ ያነሳዉ የመሰላቸዉንና ስንት አመት ዉዳሴ ማህሌት የቆሙለትን ንዑስ ብሄርተኝነት ማጣጣል ይዘዋል፤ያለምንም ሃፍረትም ለአማራ ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር ሊሰብኩት የካድሬ አፍ እየተዋሱ ነዉ። ይህን ሲያደርጉ አማራዉ ለብዙ ዘመናት በብሄረ-ኢትዮጵያ ፍቅር በመናወዙ ምክንያት የንዑስ ብሄርተኝነት ፖለቲካን ጥበብ መልመድ ባለመቻሉ የፖለቲካ ብልጫ እንደወሰዱበት እየተሳለቁ የፃፉትን ረስተዉታል።

አማራዉ በማንነቱ የተቃጣበትን አደጋ በማንነቱ ተደራጅቶ ለመመከት ቆርጦ መነሳቱ ከደሙ ጋር የሚዘዋወረዉን የብሄረ-ኢትዮጵያን ፍቅር አስጥሎታል ብሎ መደምደም ትልቅ ስህተት ነዉ። ይህ የአማራ ብሄርተኝነት ከሌሎች ንዑስ ብሄርተኞች የሚለይበት መለያዉ ነዉ። አማራ-ጠሉ የንዑስ ብሄርተኝነት ፖለቲካ የሚለይበት ዋናዉ ነገር ኢትዮጵያን ሳይጠላና ሳያበሻቅጥ የራሱን የንዑስ ብሄርተኝነት ጥቅም የሚያስከብር አይመስለዉም። ስለዚህ አማራም የብሄር ጥቅሙን ለማስከበር ሲነሳ ከእስትንፋሱ ጋር የተቆራኘዉን የብሄረ-ኢትዮጵያ ርዕዮት አዉልቆ ጥሎ፣እንደነሱ ሃገርን በመንደር የሚተካ ቀትረ-ቀላል ፖለቲካ የሚያራምድ ይመስላቸዋል።

አማራ እንደሌሎች ንዑስ ብሄርተኞች ኢትዮጵያ ዉብ ሆና የምትታየዉ ዙፋን ላይ ሆና ሲያያት ብቻ አይደለም፡፡ ይልቅስ በገዛ ሃገሩ በስደተኛ ካምፕ ተቀምጦ፣በሌሊት የተኩስ እሩምታ እየወረደበት፣በጅምላ እየተቀበረም፣አዲስ አበባ እንዳይገባ አማራነቱ ተከልክሎ ሁለት ሶስት ወራትን በረሃ ላይ እያደረም ኢትዮጵያን ይወዳታል፡፡ ስለሆነም አማራ ለትግል የወጣዉ መከራዉን ያበዛዉን ስርዓት ለመታገል እንጅ ኢትዮጵያን ለማጥፋት አይደለም፡፡ አማራ ኢትዮጵያ የተባለችዉን ብዙ የተደከመባትን ሃገር እና ዘረኛ የመንግስት ስርዓትን ልዩነት ጠንቅቆ ያዉቃልና ስለ ኢትዮጵያ መኖር አስፈላጊነት የሚመክረዉ የቁራ ጩኸት አያስፈልገዉም፡፡ የኢትዮጵያ መኖርን አስፈላጊነት አብዝቶ ሊናገር የሚገባዉ የኢትዮጵያ ጥቅም ገና ትላንት ለገባዉ የንዑስ ብሄረተኛ ጎራ እንጅ ለአማራ ህዝብ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ መኖር የሚረጋገጠዉ ደግሞ ኢትዮጵያን ምላስ ላይ ብቻ በማስቀመጥ ሳይሆን የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት በመጠበቅና በማስጠበቅ ነዉ፡፡

ወደ ዋናዉ ነጥባችን ስንመለስ ከዚህ ቀደም "ንዑስ ብሄርተኝነትን በማቀንቀን ኢትዮጵያን ለማፍረስ እንሰራ ነበር ዛሬ ደግሞ ኢትዮጵያን ለመገንባት እንሰራለን" የሚለዉ የኦሮሞ ብሄርተኝነት ልሂቃን ንግግር እዉነተኛ ምክንያቱን ወደ መመርመሩ እንገባለን፡፡ ይህን ስናነሳ የኦሮሞ ፖለቲከኞች አማራ የጠላዉን የመዉደድ የወደደዉን የመጥላት፣የጣለዉን የማንሳት፣ያነሳዉን የመጣል ላይ የተቃኘ የመባከን ፖለቲካ ዉስጥ የገቡት ለምንድን ነዉ? ወደ ሚለዉ ወሳኝ ነጥብ እንደርሳለን፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት አማራዉ በብሄረ-ኢትዮጵያ ርዕዮትም ሆነ በንዑስ ብሄርተኝነት መስመር ቢሰለፍ ስኬታማ እንደሚሆን ስለሚያዉቁ የአማራ ስኬት ደግሞ የነሱ ዉድቀት አድርገዉ ስለሚያስቡት ነዉ፡፡

የብሄረ-ኢትዮጵያ ርዕዮት ሃገር ከማስቀጠል ጀምሮ አያሌ ድሎችን እየተጎናጸፈ፣ቅኝ አገዛዝን ጨምሮ በርካታ መሰናክሎችን እያለፈ እዚህ የደረሰ ድል አድራጊ ርዕዮት ነዉ፡፡ ይህ ርዕዮት ሁሉም ኢትጵያዉያን ተባብረዉ ያቆዩት ኢትዮጵያዊን ርዕዮት ቢሆንም ለአማራ-ጠል ፖለቲካዉ ግን የአማራ ብቻ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ስለዚህ የጥቃት ኢላማ ተደርጎ ኖረ፡፡ ይህ ጥቃት በዋናነት አማራዉ ላይ በማነጣጠሩ አማራዉ ዘግይቶም ቢሆን በብሄር ተደራጅቶ መታገል ጀመረ፡፡ በዚህ ትግልም ቢሆን አማራዉ ዉጤታማ እንደሚሆን ጥርጥር የለዉም፡፡ በንዑስ ብሄርተኝነቱ ትግል አማራን ዉጤታማ ከሚያደርጉት ጉዳዮች አንዱ ሰፊ የህዝብ ቁጥር ያለዉ በመሆኑ ነዉ፡፡

የብሄረሰብን ቁጥር ዋና በሚያደርገዉ የብሄር ፖለቲካዉ መስመርም ቢሆን አማራዉን ከስልጣን የሚከለክለዉ ተአምር የለም፡፡

ይህን የሚያዉቀዉ አማራ-ጠሉ የብሄር ፖለቲካ ጎራ የዘየደዉ ዘዴ ሃገሪቱ በአጠቃላይ በብሄር ፖለቲካ እየተመራች ባለችበት ሁኔታ የአማራ ክልልን ብቻ በሲቪክ ፖለቲካ የመምራት ስዉር መንገድ ነዉ፡፡ በመሆኑም የሌላዉን ብሄረሰብ በብሄር መደራጀት የሚያበረታታ ህገ-መንግስታዊ ነገር ሆኖ እየተንቆለጳጰሰ የአማራ ብሄርተኝነት ግን በሃገር አጥፊነት፣በጽንፈኝነት፣በሃገር በታኝነት ወዘተ ይፈረጃል፡፡ ሌላዉ ብሄረሰብ የራሱን ችግር በእራሱ የክልል ፓርላማ፣በገዥዉ የፖለቲካ ፓርቲ ስር እነዲፈታ ሲደረግ የአማራ ክልልን ችግር ለመፍታት ግን በብልጽግና ፓርቲ ስር የተኮለኮሉ የብሄር ፓርቲዎች ካድሬዎች እንዲፈቱት ወደ አስራ አምስት የአማራ ክልል ከተሞች ይላካሉ፡፡ ይህ ማለት አጠር ተደርጎ ሲቀመጥ የአማራ ህዝብ እጣፈንታ በራሱ በአማራዉ ሳይሆን በብሄር ብሄረሰቦች ካድሬዎች ይወሰናል ማለት ነዉ፡፡ በጣም ሲያጥር ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸዉን እድልና የአማራን ህዝብ እድል ይወስናሉ ማለት ነዉ፡፡

የህብረ-ብሄራዊ አንድነት አዲስ ትርክት እየተባለ በብልጽግና መንግስት የሚቀነቀነዉ መርዝ ለበስ ፕሮፓጋንዳ በአማራ ህዝብ ሁኔታ ሲተረጎም "እጣ ፈንታህ ትላንት በጨቆኑህ ብሄረሰቦች ይወሰናል" የሚል ነዉ፡፡ በመሆኑም በህብረ ብሄራዊ አንድነት ስም የአማራ ክልልን ጉዳይ ብቻ የብሄር ብሄረሰብ ካድሬዎች እንዲያቦኩት አማራ ክልል ይጓዛሉ፡፡ የተያዘዉ ነገር እዉነት የህብረ-ብሄራዊ አንድነት ጉዳይ ቢሆን ኖሮ ሲዳማ ክልል የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ሃምሳ አምስት ብሄረሰቦች የገነቧትን አዋሳ ከተማን ማእከል ያደረገ ክልል ሲመሰረት ወደ አማራ ክልል አስራ አምስት ከተሞች የተጓዙት የብሄር ብሄረሰቦች ካድሬዎች አዋሳ ከተማ ተገኝተዉ ከህዝብ ጋር መምከር ነበረባቸዉ፡፡ ኦሮሞ ብልጽግና "አዲስ አበባ የኔ ነች" ብሎ መግለጫ ሲጽፍ የብሄር ብሄረሰብ ፓርቲዎችን ማስፈቀድ ነበረበት፣የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣የማእከላዊ ኢትዮጵያ ወዘተ ክልሎች ሲቋቋሙ የብሄር ብሄረሰቦች ካድሬዎች ጉባኤ በነገሩ ዙሪያ ለመምከር በየክልሎቹ እንደ ጨዉ መበተን ነበረባቸዉ፡፡

ሌሎች የሃገሪቱ ክልሎች በብሄር ፖለቲካ ቅኝት እየተዘወሩ የአማራ ክልልን ብቻ ለይቶ በሲቪክ ፖለቲካ የማስተዳደሩ እቅድ አማራዉን ሀገርም ክልልም የሚያሳጣ አደገኛ አካሄድ ነዉ፡፡ አሁን የአማራ ክልል ላይ የተሾመዉ የአረጋ ከበደ አስተዳደር ደግሞ ፖለቲካ በዞረበት ያልዞሩ፣ሰዉ ሲጠፋ የተመለመሉ ፍጥረታት በመሆናቸዉ ካቢኔያቸዉን "የሃገሪቱን ብሄር ብሄረሰብ ተዋጽኦ በጠበቀ መንገድ መስርቱ" ቢባሉ በአማራ ክልል ሰማንያ አምስት የካቢኔ አባላት ከመመስረት የማይመለሱ ናቸዉ፡፡ በአጠቃላይ ህብረ-ብሄራዊ አንድነት የሚለዉ ስብከት አማራዉ እንደብሄርም እንደ ዜጋም የማይታወቅበት አደናጋሪ ስርዓት በመፍጠር የተለመደዉን አማራን የማሳደዱ ስራ ማስቀጠያ ዘዴ ነዉ፡፡

የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች ለማድመጥ እንኳን ባለመፍቀዱ ይህ ስርዓት ለአማራ በጎ ነገር እንደማያመጣ አስመስክሯል፡፡ ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ ስለ ህብረ-ብሄራዊ አንድነት በመንግስት በኩል የሚሰበከዉ አማራዉ ፖለቲካዊ እጣ ፋንታ "አማራ ጠላታችን ፣ጨቋኛችን ነዉ" በሚሉ የብሄር ብሄረሰብ ካድሬዎች እጅ ዉስጥ በመክተት ጨዋታቱን ለመቀማት ነዉ፡፡ ይህ ማለት የተከሳሽ እጣ ፋንታ በከሳሽ እንዲወሰን የማድረግ ሙከራ ነዉ፡፡

አማራ-ጠሉ ስርዓት ስለ ህብረ-ብሄራዊ አንድነት ሌት ተቀን የሚያስደስኩረዉ አማራዉ ብዝሃነትን አይቀበልም የሚለዉን ክስ ለማስከትል እንጅ ስሙን የመሰለ ብዙሃን ኢትዮጵያዉያን ተከባብረዉ የሚኖሩበትን ፖለቲካዊ ስርዓት ለማምጣት እንዳልሆነ ምስክሩ ብዙ ነዉ፡፡ ህብረ-ብሄራዊ አንድነቱ የአማራን ህዝብ የሚጨምር ቢሆን ኖሮ የአማራ ህዝብ ሲፈናቀል ለጌዲኦ ህዝብ መፈናቀል ጊዜ የጠ/ሚዉ ካቢኔ ጌዲኦ ዞን እንደተገኘዉ የአማራ ተፈናቃዮችንም ጎብኝቶ መፍትሄ ይሰጥ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ከሶማሌ ክልል የተፈናቀሉ የኦሮሞ ተፈናቃዮች ለወደፊቱ የከተማ ፖለቲካ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ጭምር ታስቦ አዲስ አበባ ዙሪያና ሌሎች ከተሞች ቤት ተገንብቶላቸዉ እንዲሰፍሩ ሲደረግ አማራ ግን ከአዲስ አበባ ዙሪያ ህገወጥ ተብሎ ተፈናቅሏል፡፡ ይህን ያደረጉ የብልጽግና ካድሬዎች ወደ አማራ ክልል 15 ከተሞች በተጓዙ ጊዜ ስለጉዳዩ ሲጠየቁ ህጋዊ ማፈናቀል እንዳደረጉ ኮራ ብለዉ ተናግረዋል፡፡ እንደዚህ ባለ ይሉኝታ ቢስ ፖለቲካ ላይ የሚገነባ ህብረ-ብሄራዊ አንድነት ምን አይነት አዲስ ትርክት ነዉ??

አሰባሳቢ የጋራ ትርክት ማለት ደግሞ አሁን የምናደርገዉን ግፍ ሁሉ በታሪክ በተጠራቀመዉ ችግር ሳቢያ የመጣ ነዉ በማለት መርገምን ሁሉ በአማራ ነገስታት ጀርባ ላይ የመወርወር አባዜ አዲስ መልክ ነዉ። በዚህ የጋራ ትርክት ተብየዉ የሚሰበከዉ ሌላዉ ነገር ደግሞ ኦሮሞ ብልጽግና አስቦበት በአማራ ህዝብ ላይ የሚሰራዉን ወንጀል በህወሃት ላይ የማላከክ መሰሪነት ነዉ። ኦሮሞ ብልጽግና ወንጀሉን ሁሉ ጠቅልለዉ በህወሃት ላይ ለማላከክ የሚጠቀምበት መሰሪ አካሄድ በአማራ ህዝብ ላይ ያደረሰዉን ወንጀል እንዲሰራ ያደረገዉ ህወሃት ለረዥም ዘመን የዘራዉ ከፋፋይ ትርክት ነዉ በማለት እራሱን በህወሃት ዘመን ያልነበረ አካል አድርጎ ያስቀምጣል።ይህን የሚሉ የኦሮሞ ልሂቃን በህወሃት የስልጣን ዘመን የአኖሌ ሃዉልትን ለማሰራት በተቋቋመዉ ኮሚቴ ተሰግስገዉ ጥላቻን ሃዉልት ያደረጉ ሃፍረተ-ቢሶች ናቸዉ። አዲስ ትርክት የሚሉትን ያሰሩትን የጥላቻ ሃዉልት በማፍረስ ቢጀምሩት ምናልባት ስሚ ጆሮ ዘንበል ይልላቸዉ ሆናል። የተሰየሙበት ስልጣን ህዝብን ከመለያየት ስብከታቸዉ ያገኙት በረከተ-መርገም ነዉ። ስለሆነም የጋራ ትርክትን ለማዋለድ የሞራል ብቃቱ የላቸዉም። በብዝሃነት ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲመጣ ካስፈለገ በሁሉም ሰዉ ይሁንታ ወደ ስልጣን የመጣ መንግስት ያስፈልጋል። በተረፈ አማራ የጣለዉ የመሰለዉን ነገር እያነሳ፣አማራ ያነሳዉ የመሰለዉን እየጣለ የሚባክን፣ኢትዮጵያንም ስልጣን ላይ ሆኖ ሲያያት ብቻ የሚወዳት ጥቅመኛ አስተዳደር ሃገር የሚያጸና ትርክት ሊያመጣ አይችልም።

# መቋጫ

በሃገራችን ለሶስት አስርት አመታት ስልጣን ላይ እየኖረ ያለዉ አማራ-ጠል ዘረኛ ስርዓት ስልጣን ከያዘበት ዘመን ጀምሮ የአማራ ህዝብ ማቆሚያ በሌለዉ መንግስታዊ በደል ዉስጥ ይገኛል። ይህ ስርዓት ወደ ትግል ለመግባቱና ስልጣን ላይ ለመዉጣቱ ምክንያት አድርጎ የሚያቀርበዉ በሳይንሳዊ መንገድ ማስረዳት የማይችለዉን በአማራ ህዝብ ደረሰብኝ የሚለዉን በደል ነዉ። በዚህም ሳቢያ ፖለቲካን ከአማራ-ጠልነት ጋር መሳ የሚያደርግ ደመነፍሳዊነትን ሁነኛ የፖለቲካ ባህሉ አድርጎ ቀጥሏል። በስርዓቱ ባህል የፖለቲካ እዉቀትና ምጥቀት ማለት የመረረ አማራ-ጠልነት ነዉ። ስርዓቱን ከቀበሌ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትርነት የሚመሩ መሪዎች አበይት እዉቀታቸዉ አማራ-ጠልነት ነዉ። በመሆኑም በጥላቻቸዉ ምሬት ልክ በአማራ ህዝብ ላይ ሁለንተናዊ አሰቃቂ በደል አድርሰዋል። ይህ በደል በአማራ እናት ማህጸን ዉስጥ ካለ ጽንስ ጀምሮ እስከ አረጋዉያን ድረስ አማራ ለተባለ በአድራሻዉ ደርሶታል። ይህ በደል እርስ በእርሱ የሚመጋገብ፣እጅግ የተወሳሰበና መንግስታዊ መሰረት ያለዉ ነዉ።

በአማራ ህዝብ ላይ የደረሰዉ መንግስታዊ(ህገ-መንግስታዊ) በደል ህዝቡ ዘግይቶም ቢሆን በማንነቱ ተደራጅቶ ለትግል እንዲነሳ አስገድዷል። አማራዉ ለትግል ሲነሳ ሁለት ጥያቄዎችን አንግቦ ነዉ። እነዚህም፦ የህልዉና እና የፍትህ ርትዕ ጥያቄዎች ናቸዉ። አማራዉ እነዚህን በዉስጣቸዉ በርካታ ሃሳቦችን ያጨቁ ጥያቄዎች ደርዝ ባለዉ ሁኔታ በጽሁፍ ሰንዶ ለወዳጅም ለጠላትም አለማቅረቡ  በደል ያልደረሰበት ተደርጎ እንዲቀርብ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል።ሆኖም ስርዓቱ የአማራን ህዝብ በደል ሽምጥጦ የሚክደዉ በደሉ በጽሁፍ ተሰንዶ ባለመቅረቡ ብቻ አይደለም። ይልቅስ የአማራን ህዝብ መበደል፣ ማሳደድ፣ አንገት ማስደፋት ስርዓቱ የተመሰረተበት እና ስልጣን የጨበጠበት ዋነኛ አላማ በመሆኑ፣ የአማራን ህዝብ በደልና ጥያቄ እዉቅና መስጠት ስርዓቱን እራሱ በእራሱ እንዲያጠፋ የሚያደርግ ስለሆነ ነዉ። ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ ትልቁ ነጥብ አማራ-ጠሉ ስርዓትና የአማራ ህዝብ ፍላጎት አብረዉ የማይሄዱ(Mutually Exclusive) መሆናቸዉን ነዉ። ሌላዉ ቁም ነገር አማራ-ጠሉ ስርዓት ከአማራ ህዝብ ጋር አለኝ የሚለዉ ልዩነት የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ከመሆን አልፎ ሰብአዊ ልዩነት እስከመሆን የነጎደ እንደሆነ ነዉ።

የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነት ሰዉን ሳይሆን ሃሳብን የሚሞግት እና ለማሸነፍ የሃሳብ ፍልሚያ የሚደረግበት የጤናማዉ የሰዉ ልጅ ተፈጥሮ አካል ነዉ፡፡ በአንጻሩ ሰብአዊ ልዩነት ጠቡን ከሰዉ ጋር የሚያደርግ፣ጠላቱ ያለዉን ተበቅሎ የማይጠግብ፣ ጥላቻ ያበረረዉ፣ አረመኔነት የሚጋልበዉ አስፈሪ ፖለቲካዊ ስነልቦና ነዉ፡፡ ከአንድ ማህበረሰብ ጋር ያለዉን ልዩነት እስከ ሰብአዊ ልዩነት የለጠጠ እሳቤ ለሳይንሳዊ እሳቤ እና ምክንያታዊ ክርክር ፋታ የሚሰጥ ልቦና የለዉም፡፡ ስለሆነም ሩጫዉ ሁሉ ጠላቴ ያለዉን አካል ሁለንተናዊ ህልዉና ለማጥፋትና ለማግለል ነዉ፡፡ በአለማችን የተከሰቱ የዘር ማጥፋት ወንጀሎችን የአፓርታይድ የመድሎ ስርዓትን የወለደዉ እንዲህ ያለዉ ልዩነትን እስከ ሰብአዊ ልዩነት የሚለጠጥ ከአእምሮ ህመም የሚዋሰን ስሜት ነዉ፡፡ ይህ ስሜት "በራስህ ላይ እንዲደረግ የማትፈልገዉን በሌሎች ላይ አታድርግ " የሚለዉን ወርቃማ ህግ የሚያስረሳ ነዉ፡፡ በመሆኑም ጠላት የተባለዉ አካል ሲወጉት የሚያመዉ፣ቤት ዘግተዉ ሲያቃጥሉት የሚሰቃይ፣ሲተኩሱበት የሚሞት መሆኑን ያስረሳና በደል ሁሉ የሚገባዉ አድርጎ ያስመለክታል፡፡

አማራ-ጠሉ ስርዓት በአማራ ህዝብ ላይ እያዳበረ የመጣዉ የፖለቲካ ስነልቦና ልዩነትን ሰብአዊ ልዩነት እስከማድረግ እንደደረሰ ማሳያዉ ብዙ ነዉ፡፡ የዚህ ስርዓት ደጋፊና መሪ የኦሮሞ መኳንንት የጽሁፍም ሆነ የድምጽ ማስረጃ የማያቀርቡለትን በንጉሱ ዘመን ኦሮሞ ከአራተኛ ክፍል በላይ እንዳይማር ተብሏል የሚሉትን ነገር የትግል አጀንዳ አድርገዉ ኖረዉ ዛሬ ላይ በአቶ ሺመልስ አብዲሳ፣በጠ/ሚ አብይ አህመድ እና በአቶ ለማ መገርሳ የተነገሩ ማስረጃ የሚቀርብባቸዉን አማራ-ጠል ንግግሮች ተገቢ አድርገዉ በመዉሰድ በዝምታ ያለፏቸዋል ወይም አፍ አዉጥተዉ ይደግፏቸዋል፡፡ በሚዲያ ቀርቦ የአማራን ህዝብ ለዘር ማጥፋት ወንጀል የሚያጋልጥ ንግግር ማድረግም በኦሮሞ ልሂቃን የታጋይነት ዳርቻ ነዉ፡፡ በተጨማሪ አማራዉ ሲገደል፣ሲሳደድና ሲገለል ስለመኖሩ ሲናገር ለማድመጥ አለመፈለግና እንዲናገር ባለመፍቀድ ከአማራ ህዝብ ጋር ያላቸዉ ልዩነት ወደ ሰብአዊ ልዩነት ያወርዳሉ፡፡

የአማራ ልሂቃን ይሄን ሁሉ ተቋቁመዉ በአማራዉ ላይ የሚደርሰዉን በደል በአደባባይ ለማቅረብ ሲሞክሩ "የበላይነት ስለለመዳችሁ እኩልነት በደል መስሎ ስለሚታያችሁ ነዉ፣ የድሮዉን ስርዓት ልትመልሱ ፈልጋችሁ ነዉ፣ ስራ አጦች ስለሆናችሁ ሰዉ አግቶ ብር መቀበል ፈልጋችሁ ነዉ፣

ብሄረሰቦች በትግላቸዉ ያስመዘገቡትን ድል ልትቀለብሱ ነዉ፣ አሃዳዊነትን ልታመጡ ነዉ" በማለት ከዘር ማጥፋት ወንጀላቸዉ የበለጠ የሚያም ክህደት ያመጣሉ። የአማራ ህዝብ ትግል ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት በአሁኑ ወቅት እንኳን የአማራ-ጠሉ ስርዓት የወቅቱ መሪ ጠ/ሚ አብይ አህመድ የአማራ ህዝብ ጥያቄዎች የግዛት፣የመልካም አስተዳደር እና የህገ-መንግስት ማሻሻያ ብቻ ናቸዉ ሲሉ ጥር 28/2016 በዋለዉ የፓርላማ ቆይታቸዉ ፍርድ ገምድለዋል። በአማራ ህዝብ ስም ፓርላማዉን የወረሩ ብአዴናዉያን ይህ ሲባል ዝም ብለዉ ከመቁለጭለጭ በቀር ያደረጉት ነገር የለም።

የአማራ-ጠሉ ስርዓት ሁነኛ ማገር የሆኑት አቶ ሬድዋን ሁሴን አማራዉን ያገለለ የፕሪቶሪያ ስምምነት አድርጌ መጣሁ ባሉ ማግስት የአማራ ህዝብ በዚህ ስምምነት መገለል ልክ እንዳልሆነ ሲጠየቁ "የሚሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ" ሲሉ ስንሰማዉ የኖርነዉን ጥላቻቸዉን እንደማናዉቅ ሊነግሩን ሞከሩ ይህ አይነቱን የአማራ-ጠል ስርዓት መኳንንት በአማራ ህዝብ ላይ ያላቸዉን ተዝቆ የማያልቅ አስፈሪ ጥላቻ አንድ ሰዉ እንዲህ ሲል በአጭር ቃል ገልጾታል "እነሱ እኮ አንድ የአማራ ምስኪን ገበሬ ከጀርባዉ ተሰይፎ ወድቆ ቢያዩት አስከሬኑን በካልቾ እየመቱ "ተነስ አንተ ነፍጠኛ" ማለታቸዉ አይቀርም።"ይህ አባባል የስርዓቱ መኳንንት በአማራ ህዝብ ስቃይ ላይ ያላቸዉን ጨካኝ ልብና ድፍን ጆሮ በጥሩ ሁኔታ የሚገልጽ ነዉ።

ስልጣን ላይ ያለዉ አማራ-ጠል ስርዓት ምሁር ነኝ ባዩ ጋሻ አጃግሬዎቹ በአማራ ህዝብ በደል ላይ ጆሮአቸዉን ከመድፈናቸዉና በደላቸዉን እስከ ህይወት ፍጻሜ ለማሳለጥ ከመቁረጣቸዉ በተጨማሪ አማራዉ ለደረሰበት በደል የሚያደርገዉን ትግል አይነት፣ጥልቀትና ስፋት ለመቆጣጠር ይሞክራሉ። አማራዉ አለቅጥ ከበዛ የሰላሳ ሶስት አመት ትዕግስት በኋላ አሁን የያዘዉን ፍትሃዊ ትግል በተራ ሁከት እና ምክንያት አልቦ ግርግር ሊፈርጁ ይሞክራሉ። አማራ-ጠሉ ስርዓት ሃገርን የሚያክል ክቡር ነገር የማስተዳደር ከፍታ ላይ ተቀምጦ በህዝብ እዉነተኛ ጥያቄ ላይ መዘባበቱ ከመንደር በርጩማ አልፎ ሃገርን የማስተዳደሪያዉ ወንበር ላይ ለመቀመጥ ቁመናም ወርድም የሚጎለዉ ድንክዬ መሆኑን ያስመሰክራል።

ድንክየዉ የንዑስ ብሄርተኛ ስርዓት ኢትዮጵያን የማከል ግዝፈት ላይ ለመድረስ የማይችል፣ድኩም ስነልቦና እንዳለዉ ማሳያዉ ብዙ ቢሆንም ሁለቱን ማሳያዎች እንጥቀስ፡፡አማራ-ጠሉን ስርዓት አቶ መለስ በሚመሩበት ወቅት ኢትዮጵያን በምታክል ትልቅ ሃገር ላይ ተቀምጠዉ ለትግራይ የሚሆን የልማት እቅድ/ስትራቴጂ/ ለማዉጣት እጅጉን ይባትሉ እንደነበር የገዛ ባለቤታቸዉ ተናግረዋል፡፡ ኢትዮጵያን በአማራ በኩል የሚጠላዉን ዘረኛ ስርዓት የመምራቱን ተራ ከአቶ መለስ የተቀበሉት ጠ/ሚ አብይ አህመድ ወደ ስልጣን እንደመጡ የኢትዮጵያ ህዝብ "ሃገር የሚያሻግር ሙሴ መጣልን" እያለ ደስታዉን አጣጥሞ ሳይጨርስ "እኔን ብትነኩኝ የኦሮሞ ፈረሰኞች መንግስታችን ተነካ ብለዉ ከሱሉልታ አዲስ አበባ ለመድረስ ሩብ ሰአት አይፈጅባቸዉም" ሲሉ መንግስትነታቸዉ ለመንደራቸዉ ሰዎች ብቻ እንደሆነ ልብ ላለዉ ሁሉ ገና በጠዋቱ ግልጽ አደረጉ፡፡ ከእነዚህ ሁለት ማሳያዎች የምንረዳዉ አማራ-ጠሉ ስርዓት የኢትዮጵያን ብሄርተኝነት ማማ ለመንካት ከማይችል ድንክዬ የፖለቲካ ዘረመል የተፈጠረ ድኩም ስርዓት እንደሆነ ነዉ፡፡ ለዚህ ስርዓት ኢትዮጵያ ከአቅሙ በላይ ነች፡፡ ስለሆነም ከመንደሩ ሰዎች አልፎ የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ጥያቄ በእኩል ሁኔታ አድምጦ መፍትሄ ለማምጣት የሚያስችል የሞራል ከፍታም ሆነ የእዉቀት ስንቅ የለዉም፡፡ የአማራ ልሂቅ ትግሉን የሃገርን መንበረ ስልጣን ወደ መቆጣጠር ኢላማ ያሳደገዉ ይህ የስርዓቱን ጠባይ በዉል ስለተረዳ ነዉ፡፡ የአማራ ህዝብ በስርዓቱ በጠላትነት መፈረጅ ደግሞ አማራዉን ፊጽሞ ከዚህ ስርዓት ተስፋ እንዳያደርግ የሚያደርግ ትልቅ ምክንያት ነዉ፡፡

አማራ-ጠሉ ስርዓት በህወሃትም ሆነ በኦሮሞ ብልጽግና መኳንንት በሚመራባቸዉ ጊዜያት አማራን ከመጥላት ያለፈ የፖለቲካ እዉቀትም/ርዕዮትም ሆነ ፖለቲካዊ ግብ አልነበረም፡፡ ይህ የፖለቲካ ባህል በኦሮሞ ብልጽግና መኳንንት ዘመን ደግሞ አማራዉ የወደደዉን ሁሉ ወደ መጥላት፣አማራዉ የጠላዉ የመሰላቸዉን ሁሉ ወደ መዉደድ፣አማራዉ ያነሳዉ የመሰላቸዉን የመጣል የመባከን ፖለቲካ አንኳል፡፡ በመሆኑም አማራዉ የጠላዉ የመሰላቸዉን የብሄረ ኢትዮጵያ ርዕዮት መሬት ጥለዉ ሲረጋግጡት ከነበረዉ ትቢያ አንስተዉ ማሞካሸት ይዘዋል፡፡ ያላንዳች ሃፍረትም አማራዉን በንዑስ ብሄርተኝነት መክሰስ ይዘዋል፡፡ የብሄረ ኢትዮጵያ ርዕዮት ለኦሮሞ ብልጽግና መኳንንት ድንኳን እንደመልበስ እጅግ ሰፍቷቸዉ የሚታይ፣ ከኖሩበት ኢትዮጵያን የማበሻቀጥ ፖለቲካዊ ተክለሰዉነት ጋር የማይሄድ ሆኖ ይታያል፡፡

በአጠቃላይ የአማራ-ጠሉ ስርዓት ምሰሶ ሆነዉ የኖሩት የኦሮሞ ብሄርተኝነት ምሁራንና የኦሮሞ ብልጽግና መሪዎች የብሄረ-ኢትዮጵያ አክራሪ አፍቃሪዎች ሆነዉ ንዑስ ብሄርተኝነትን ሲያወግዙ ሲታይ ሂትለር የናዚ ስርዓትን ሲያማርር፣ ሞሶሎኒም የፋሺዝምን ተክለ-ርዕዮት ሲያብጠለጥል እንደ መስማት ያለ የለበጣ ነገር ነዉ። በብሄር ማንነታቸዉ ብቻ ወንበር ተሸላልሞ ጠብቋቸዉ እንደ ዶሮ ስልጣን ላይ የሰፈሩ የንዑስ ብሄርተኝነት ቀሳዉስት የብሄር ፖለቲካን በከፋፋይነት ሲያማርሩ መስማት " በማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚለሽ " የሚያስብል ነገር ነዉ። ነገሩ እዉነት ከሆነ ደግሞ የኦሮምኛ ቋንቋን ለመፃፍ ወደ ላቲን ፊደል ያስቀላወጣቸዉን የብሄረ ኢትዮጵያን ጥላቻ አስወግደዉ በኢትዮጵያ ፊደላት እንዲፃፍ ያደርጉ፣አኖሌ የተባለዉን የጥላቻ ሃዉልት ያፍርሱ፣አፈራርሰዉ የሚጣሉትን የራስ መኮንን በቦታዉ ይመልሱ፣የአድዋን ድል በዓል ኢትዮጵያዉያን ሁሉ በሚኒሊክ ሃዉልት ስር እንዲከበር በማድረግ ቀላሉን ፈተና ይለፉ።

የአማራ ህዝብ ያነሳዉ ጥያቄ የህልዉና እና የፍትህ ርትዕ ብቻ ሳይሆን ስልጣን ላይ ያለዉን ስርዓት ኢትዮጵያንን የማከል ብቃት ጭምር ነዉ። ስርዓቱ ከተፈጠረበት የንዑስ ብሄርተኝነት የፖለቲካ ዘረመል አኳያ ኢትዮጵያዊ ሆኖ፣ኢትዮጵያን አክሎ የኢትዮጵያዉያንን በአጠቃላይ (የአማራን ህዝብ ጥያቄ በተለይ) ይመልሳል ብሎ የአማራ ትግልን አያምንም። ትግሉ የስርዓት ለዉጥና የሃገር መንበር ስልጣንን የመጨበጥ አላማን አንግቦ የተነሳዉም ለዚህ ነዉ። ስርዓቱ የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች ለመመለስ ቀርቶ በዉል ለማጤን ፍላጎት እንደሌለዉ የጠ/ሩ የጥር ወር የፓርላማ ዉሎ አንድ ፍንጭ ይሰጣል። ጠ/ሩ በንግግራቸዉ "የአማራን ተፈናቃዮች ወደ ኦሮሚያ ለመመለስ ስንሞክር አትመለሱ እያሉ የሚመክሩ ሰዎች እንቅፋት ሆኑብን" ሲሉ አማረዋል። ጠ/ሚዉ ይህን ሲሉ ተፈናቃዮቹ እንዴት ካለ የሞት ጆፌ አምልጠዉ እንደመጡ ከራሳቸዉ ከተፈናቃዮች በላይ አዉቃለሁ ብሎ ሊያስረዳ የሚሞክር እንደማይኖር መረዳት አልፈለጉም።

እነዚህ ሰዎች ከኦሮሚያ ክልል ሲወጡ ያዩትን ሰቆቃ አዲስ አበባ፣ዋሽንግተን ዲሲ ወይም ባህርዳር/ጎንደር ከሚኖር ሰዉ መስማት አይጠበቅባቸዉም። ሲመለሱ የሚጠብቃቸዉንም ጠንቅቀዉ ስለሚያዉቁ ነዉ ወደ ኦሮሚያ አንመለስም የሚሉት። ይህን ለመረዳት አለመቻል ራሱ ችግሩን ለመፍታት የተሞከረዉን ሙከራ እዉነተኝነት ጥያቄ ዉስጥ የሚከት ነዉ።

“ተፈናቃዮቹን መልሻለሁ” ለሚል ፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ሲባል ብቻ ከሞት በተአምር አምልጠዉ የመጡ ሰዎችን ወደ ሞት ቀጠና ለመወርወር መሞከር የአማራ ታጋዮችን አጀንዳ ያስጥለኛል ተብሎ የተወጠነ የእንጀራ እናት መፍትሄ ነዉ። ተፈናቃቹን ወደ ቀያቸዉ የመመለሱ እዉነተኛ እርምጃ ሰዎቹ ሲመለሱ የአካባቢዉ የጸጥታ፣የደህንነት፣የአስተዳደርና አጠቃላይ የፖለቲካ ዉክልና ከማግኘታቸዉ ጋር በጥብቅ የሚቆራኝ ነገር ነዉ። ይህ ሁኔታ ቀድሞ ባልተሟላበትና ዋስትና ባላገኘበት ሁኔታ ትናንት ዘመዶቻቸዉ በአይናቸዉ ስር እንደ ዶሮ እየታረዱ በተጣሉበት ቦታ “ተመልሳችሁ ሂዱ” ሲባሉ ብድግ ብለዉ ይሄዳሉ ብሎ መታሰቡ ስርዓቱ ችግሮችን ለመፍታት ያለዉን ቅንነት፣ብቃት እና እዉቀት ጥያቄ ዉስጥ የሚከት ነዉ።

ሲጠቃለል የአማራ ህዝብን ጥያቄዎች ለመመለስ ቅን ልቦና፣ሰፊ እዉቀትና ኢትዮጵያን የሚያክል የፖለቲካ ስራት ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ የአማራ ህዝብ ጥያቄ የሚመለሰዉ እንደ አጠቃላይ በችግር ፈቺ የፖለቲካ ማእቀፍ/ስርዓት እንጂ በ “Convince & Confuse” የፖለቲካ ቀመር አሰልቺ ፕሮፖጋንዳ አይደለም። የአማራ ህዝብን ጥያቄዎች ለመመለስና ኢትዮጵያን ወደ ሰላሟ ለመመለስ ካስፈለገ ቢያንስ በዚህ ሰነድ የተነሱ ጥያቄዎችን ጥንቅቅ አድርጎ መመለስ ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ አማራ-ጠሉ ስርዓት የተሰራበት አማራ-ጠል ዉቅር አይፈቅድም። ስለዚህ ያለዉ ቀሪ አማራጭ የስርዓት ለዉጥ ነዉ። የአማራ ህዝብም የሚታገለዉም የስርዓት ለዉጡን እዉን ለማድረግ ነዉ።

መስከረም አበራ (ከቃሊቲ እስር ቤት)